# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቀጥር 227 ሚያዝያ 17 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# መገናኛ ብዙኃን የምክክር ሂደቱን ሲያደናቅፍ ከሚችል ዘገባ መቆጠብ እንዳለባቸው ባለሥልጣኑ አሳሰበ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- መገናኛ ብዙኃን የአገራዊ ምክክር ሂደቱን ሊያደናቅፍ ከሚችል ዘገባ መቆጠብ እንዳለባቸው የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን አሳሰበ።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሐመድ ኢድሪስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መገናኛ ብዙኃን የአካታች አገራዊ የምክክር ሂደቱን ከሚያደናቅፍ መንገድ ተቆጥበው መሥራት ይኖርባቸዋል።

በምክክር ሂደቱ ወቅት በሚካሄዱ ውይይቶች ላይ የሚነሱ ሃሳቦችን ለማንቋሸሽና ለመግፋት ከሚደረጉ ጥረቶች፤ በጽንፈኝነት የሚወጡ ሃሳቦችን ሌሎች ላይ ከማራገፍ እንዲሁም የአንድን አካል ሃሳብ ባልተገባ መንገድ ከመጠቀም የመቆጠብ ግዴታ አለባቸው ብለዋል።

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በሚፈጥራቸው ሁነቶች ላይ የሚቀርቡ አጀንዳዎችንና ሃሳቦች በማይጨፈልቅ መንገድ ዘገባ በመስራት ለምክክሩ ውጤታማነቱ መትጋት ይኖርባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ኮሚሽኑ የሚያወጣቸውን የሥነ ምግባር ኮድ ማክበር እንዳለባቸው ጠቁመው፤ ይህንኑ አስመልክቶ ከፍተኛ ሽፋን በመስጠት ለህብረተሰቡ ተደራሽ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው ዳይሬክተሩ አሳስበዋል።

ምክክሩን ውጤታማ ለማድረግ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ መረጃ አሰጣጥ ያስፈልጋል ያሉት አቶ መሐመድ፤ መገናኛ ብዙኃን ለጉዳዩ የቀረበ ባለሙያ መመደብና ለባለሙያው ተገቢ


መገናኛ ብዙኃን የምክክር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ- በግዛቸው ገብሬ

አቶ መሐመድ ኢድሪስ

# ‹‹ክስተቶችን ከማራገብ ይልቅ ኢትዮጵያ ከገባችበት ችግር እንድትላቀቅ መሥራት ከልሂቁ ይጠበቃል››

## - ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ- የታሪክ ተመራማሪ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት ክስተቶችን በማራገብ ወደ ጠርዝ ከመግፋት ይልቅ ኢትዮጵያ የገባችበትን ችግር ምክንያታዊ ሃሳብ በማቅረብና አገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን መስራት ከልሂቁ ይጠበቃል ሲሉ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ ተናገሩ።

ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እንደ ኢትዮጵያ ያለ በአብዛኛው ከ80 በመቶ የማይተናነስ ሕዝብ በግብርና ስራ የተሰማራ አርሶአደር ሕዝብ በመሆኑ በርካታ አገራዊ ጉዳዮች የሚቀነቀኑት በልሂቁ ክፍል ነው።

ይህ ክፍል የአገሪቱን እጣፋንታ በመወሰን ረገድ ትልቅ ሚና መሆኑን አመልክተው፤ ልሂቁ ሊገነዘብ የሚገባው ጉዳይ ያለችን አንድ አገር በመሆኑ በጊዜ ተባብሮ አሁን ከተጠናወታት በሽታ ማዳን ያስፈልጋል። ካልሆነ ለልሂቃኑም የማይመች ሁኔታ ሊፈጠር የሚችል መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ የሶሪያ ዜጎች በአዲስ አበባ ጎዳና ላይ የሚለምኑት ከጥቂት ዓመታት በፊት በጣም የተደላደለ ኑሮ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ የምሁራኑና የልሂቃኑ



አካል የነበሩ ናቸው። ኢትዮጵያውያን ከሶሪያዊያን መማር አለብን። የኢትዮጵያን ችግር ይፈታል ተብሎ የታለመው አገራዊ ምክክር ዳር እንዲደርስ ምሁራኑና ልሂቃኑ ያጋጠሙና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ክስተቶችን ማባባስ ሳይሆን በሰከነ መንገድ የሰላና የበሰለ ሃሳብ በማቅረብ ለውጤታማነቱ መስራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ለጊዜው ተመችቶኛል ብሎ ያለምንም ኃላፊነት ጉዳዮችን ወደ ጠርዝ የምንገፋበት ጊዜ አይደለም የሚሉት ፕሮፌሰር ሹመት፤ አደጋ ከተከሰተ ከአደጋው የማንተርፍበት ሁኔታ መኖሩን በመገንዘብ የሶሪያውያን እጣ ፋንታ እንዳይገጥመን መስራት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ችግር ከመጣ ከፍተኛ ሰለባ የሚሆነው ልሂቁ ክፍል መሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም ያሉት የታሪክ ተመራማሪው፤ አገሪቱ ልትሸከመው የምትችለው መከራ የተወሰነ ነው። አንድ ደረጃ ስንደርስ ልንመልሰው የማንችልበት ጫፍ ሊወስደን ስለሚችል የሚመጣውን አደጋ ያገናዘበ ምሁራዊና ልሂቃዊ አስተሳሰብ በመያዝ በምክክሩ ውጤት ለማምጣት መስራት ተገቢ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ምሁራን የልሂቁ አካል ቢሆኑም በምሁርነታቸው ስህተቶችንና ህጸፆችን በሚገባ በማቅረብ ሕዝብ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ አንዳንዴም ያዋጣል ብለው የሚገምቱትን የመውጫ መንገድ እንዲያመላክቱ ይጠበቃል ብለዋል።

መንግሥት ብቻ በመንቀፍ ውጤት አይገኝም ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ወደድንም ጠላንም የመንግሥት ሚና ወሳኝ በመሆኑ ትልቁ ትኩረት መሆን ያለበት በምን መንገድ ብናግዘው ሊሻሻል ይችላል የሚል ሃሳብ በመያዝ የጎደለውን እየሞሉ ተገቢውን አቅጣጫ ማስያዝ ተገቢ መሆኑን ጠቁመዋል።








# ከኢድ እስከ ኢድ የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ ለማስተዋወቅ ተገቢ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በኢድ እስከ ኢድ መርዓ ግብር የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ በውል ለማስተዋወቅ ተገቢ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ የታሪክ ምሁሩ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል አመለከቱ።

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፤በመርሀ ግብሩ ላይ ለመሳተፍ ከተለያዩ የዓለም አገራት የሚመጡ ኢትዮጵያውያን፣ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በቆይታቸው ስለ ኢትዮጵያ ነበራዊ ሁኔታ በቂ እውቀት እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ከወዲሁ ማመቻቸት ያስፈልጋል። በተለየ መልኩ ደግሞ ከኢትዮጵያ እስልምና


ከኢድ እስከ ኢድ የኢትዮጵያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# ኦሮሚያ በበጋ መስኖ 27 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል

## - በመኸር ምርት ዘመን ከ48 ሚሊዮን በላይ ኩንታል ስንዴ ለማምረትም ታቅዷል

ገመቹ ከድር



አዲስ አበባ ፡- በኦሮሚያ ክልል በሁለት ዙር የበጋ መስኖ ብቻ 27 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ለማምረት እየተሰራ መሆኑን ኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ ። በመኸር ምርት ዘመን 48 ሚሊዮን 259 ሺህ 89 ኩንታል የስንዴ ምርት ለማምረት መታቀዱም አመልክቷል።

በክልሉ ግብርና ቢሮ የበጋ ስንዴ ምርት ኢንሼቲቪ አስተባባሪ አቶ ጠሃ ሙሜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከክልሉ በበጋ መስኖና በመኸር ምርት ዘመን ከፍተኛ የስንዴ ምርት በማምረት እንደ አገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል። በበጋ መስኖ ብቻ 27 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለማምረት እየተሰራ ነው።

በበጋ መስኖ 350ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ ለመሸፈን ታቅዶ 355 ሺህ 106 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን አመልክተው፤በአሁኑ ጊዜም በበልግ ዝናብ የሚታገዝ ሁለተኛ ምዕራፍ የመስኖ እርሻ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑንና እስካሁንም 257 ሺህ 800 ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፍን እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል ።

እስከ በልግ መጨረሻ ድረስ አፈጻጸሙ እንደሚጨምር ገልጸው፤ ዕቅዱን እንደሚሳካም በመጀመሪያ ዙር የበጋ መስኖ የተመዘገቡ ዉጤቶች አመላካች መሆናቸዉን አስገንዝበዋል ።

በክልሉ የመኸር ምርት ዘመን ሳይጨምር በሁለት ዙር የበጋ መስኖ እርሻ ብቻ 27 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ምርት ለመሰብሰብ ጥሩ አፈጻጸም ላይ ይገኛል ብለዋል ።

አርሶ አደሩ የስንዴ ምርታማነት እንዲጨምር ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ግብዓቶችን እንዲጠቀሙ እየተደረገ መሆኑን አውስተው፤ በሁለቱም ዙር የበጋ መስኖ እርሻም 448 ሺህ 293 ኩንታል ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ግብዓቶች ለአርሶ አደሩ ማቅረብ መቻሉን አብራርተዋል ።

በቢሮዉ የክረምት ሰብል ልማት ዳይሬክተር አቶ በየነ ማሞ በበኩላቸዉ ክልሉ በዘንድሮ የመኸር ምርት ዘመን ብቻ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ ሰብል በመሸፈን 48 ሚሊዮን 259 ሽህ 89 ኩንታል ስንዴ ምርት ለማምረት ዕቅድ መያዙን ተናግረዋል።

ዕቅዱን ስኬታማ ለማድረግም ምርትና ምርታማነትን በሚያሳድጉ ግብዓቶች አጠቃቀም፣ አዘገጃጀትና በመስመር መዝራት ዙሪያ ላይ የግንዛቤ የማስጨበጫ ሥልጠናዎች ለአርሶ አደሩ በመስጠት ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል ።

የማዳበሪያ እጥረት እንዳይከሰት የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ አቅጣጫ መቀመጡን ጠቁመው፤ የስንዴ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚደረገው ርብርብ ሁሉም ወገን የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል ።

እንደ አገር የምግብ ዋስትና በአስተማማኝ መልኩ ማረጋገጥ የሚቻለው የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማት ሲጨምር መሆኑን አስታውቀዋል።

# ለአገራዊ ምክክሩ ሚዲያው የሚመራበት መመሪያ ሲዘጋጅ እንደሚገባ ተጠቆመ

ፍቃዱ ዴሬሳ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ሊደረግ በታሰበው አገራዊ ምክክር የሚዲያው ሚና ጉልህ በመሆኑ ሚዲያው የሚመራበት ዝርዝር መመሪያ ሰነድ ሊዘጋጅለት እንደሚገባ ተገለጸ። ሚዲያው አገራዊ ጥቅምና ሙያዊ ስነ ምግባርን ማዕከል በማድረግ ለሀገራዊ ውይይቱ የበኩሉን በጎ አስተዋፅኦ ማድረግ እንደሚገባውም ተጠቁሟል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ዶክተር ሳምሶን መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ አገራዊ ምክክር በማድረግ የተሳካላቸው በርካታ ሀገራት እንዳሉ ሁሉ ምክክሩ ሳይሳካላቸው የቀሩ አገራት አሉ። ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማ ሆነ ስኬታማ ላለመሆኑ ሚዲያው እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚጠቀስ ነው።

በማህበረሰብ ደረጃ የሚደረግ ውይይት በማህበረሰባዊ ስነ-ተግባቦት የሚቃኝ ስለሆነ ሚዲያው ይህን ተግባቦት በማቀላጠፍ ረገድ የሚጫወተው አዎንታዊ ሚና ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊወጣ እንደሚችል ተናግረዋል።

ሚዲያው የሰፊውን ማህበረሰብ ሃሳብና ፍላጎት ወደ ጎን በመተው የፖለቲካ ልሂቃን ሃሳቦች ላይ በማተኮር ማህበረሰቡ ላይ ተፅዕኖ ለማድረግ የሚጥር መሆን እንደሌለበት ጠቁመው፤ ሚዲያው የታችኛው ማህበረሰብ ፍላጎትና ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩ የማድረግ ተግባር ሊኖረው ይገባል። ይህም ማህበረሰቡ ለአገራዊ ምክክሩ አዎንታዊ ሚና እንዲጫወት ያደርገዋል ብለዋል።

“እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት ውስጥ የሚደረግ አገራዊ ምክክር ምን አይነት የሚዲያ ሞዴል ሊተገበር ይገባል ተብሎ ከወዲሁ ሊጤን ይገባል። ይህ ሲባል የሚዲያ ነፃነት መጋፋት ማለት ሳይሆን፣ ማንኛውም የሚዲያ ተቋም እንደሚያደርገው አገራዊ ጥቅሞችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ሊሰራበት ይገባል” ብለዋል።

በሀገሪቱ ውስጥ የሚስተዋሉ የሚዲያ ሁኔታዎች ሲቃኙ ሀገራዊ ፍላጎቶችን ከማንፀባረቅ ይልቅ



ዶክተር ሳምሶን መኮንን

የራሳቸውን ቡድናዊ ፍላጎቶች ማራመድ ላይ የተጠመዱ በመሆናቸው በአገራዊ ምክክሩ ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ጠቁመው፣ ሁሉም ሚዲያዎች ይዘታቸው አገራዊ ጥቅምና ሰላምን ታሳቢ ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ሚዲያውና የሚዲያ ሙያተኛው ሙያዊ ስነ-ምግባርን ማዕከል በማድረግ የአገራዊ ምክክር ሂደቶችን የሚተች፣ መንገድ የሚያሳይ፣ የታፈኑ ሃሳቦች እንዲወጡ የሚያደርግ፣ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት እንዲሁም በምክክሩ ጉዳዮች ዙሪያ ሽፋኖችን በመስጠት ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር ተናቦ ሊሰራ እንደሚገባውም አስገንዝበዋል።

አከራካሪ ሆነው የወጡ ጉዳዮችን በተገቢው በማጤን ሚዲያው ማህበረሰባዊ ኃላፊነት መከተል እንደሚኖርበት ጠቁመው፤ የሚዲያ ባለሙያዎችም ሙያዊ ስነ-ምግባርን በመከተል ሀገራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ዶክተር ሳምሶን ገልፀዋል።

ለህብረተሰቡ ሚዛናዊና ትክክለኛ መረጃ በማድረስ፣ አካታችና አሳታፊ ያለው፣ ሁሉንም ማህበረሰብ ተደራሽ የሚያደርግ እንዲሁም በማህበረሰቡ መካከል እኩልና ተመጣጣኝ የሆነ መረጃ ፍሰት እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ሚዲያዎች ሚናቸው የጎላ መሆን እንዳለበት ምሁሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ፍራንኮ ቫሉታ ለህገ ወጥ የውጭ ምንዛሬ ዝውውር እንዳይዳርግ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ፍራንኮ ቫሉታ ለሕገ ወጥ የውጭ ምንዛሬ ዝውውር እንዳይዳርግ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ሲሉ የፖሊሲ ጉዳዮች ባለሙያው አቶ አማንይሁን ረዳ አስታወቁ።

የፖሊሲ ጉዳዮች ባለሙያው አቶ አማንይሁን ረዳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ያለ ውጭ ምንዛሬ ፈቃድ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቅደው “ፍራንኮ ቫሉታ” አሁን ኢትዮጵያ የምትገኝበት ሁኔታ የተለየ ችግር የተከሰተበት ወቅት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደ አገር የገጠመውን የምርት እጥረት ለመቅረፍ ጊዜያዊ መፍትሄ የሚሰጥ ነው። ሆኖም ለህገ ወጥነት በር የሚከፍት በመሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

ፍራንኮ ቫሉታ የአጭር ጊዜ መፍትሄ ነው ያሉት ባለሙያው፤ ለአጭር ጊዜ መፍትሄ የምርት እጥረት ችግርን ለመቅረፍ በተለይ ምግብ ነክ እቃዎች ከውጭ በበቂ መጠን እንዲገቡና ሕዝቡን ለምሬትና ለብሶት እያደረገ ያለውን የዋጋ ንረት አቅርቦትን በማሻሻል ረገድ ሚና እንዳለው ገልጸዋል። ነገር ግን በዘላቂነት የአገሪቷን የምርት እጥረት የሚቀርፍ እንዳልሆነ፤ በጥቂቱም ቢሆን ለህገ ወጥ አሰራር ቀዳዳ መክፈት የሚችልበትና ህገ ወጥነት ኢኮኖሚው ውስጥ የጎላ ቦታ እየያዘ እንዲመጣ ሊያደርግ ስለሚችል መጠንቀቅ ያስፈልጋል ብለዋል።

ፍራንኮ ቫሉታ ለህገ ወጥነት በር የሚከፍት ቢሆንም የኑሮ ውድነቱ በዚህ ከተባባሰና ከቁጥጥር ውጪ ከሆነ ወደ ለየለት የኢኮኖሚ ቀውስ አልፎ ወደ ፖለቲካ ቀውስ ሊገባ ስለሚችል የኑሮ ውድነትን በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ ሊመከት የሚችል እርምጃዎች መውሰድ ተገቢ እንደነበር ባለሙያው ገልጸዋል። ይህንን ታሳቢ አድርጎ ፍራንኮ ቫሉታ መፈቀዱ ትክክለኛ ውሳኔ እንደሆነም ነው የተናገሩት።

እንደ ባለሙያው ገለጻ፤ ህገ ወጥነቱን ለመከላከል በፍራንኮ ቫሉታ የሚገቡ ምርቶች ቀጥታ የኑሮ ውድነትን ከማረጋጋት አንጻር ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉ ምግብና ምግብ ነክ የሆኑ ሸቀጦች መሆን መቻል አለባቸው። መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ፣ የህክምናና የመድኃኒት አቅርቦቶች ካልሆኑ በስተቀር የቅንጦት እቃዎችን በእንዲህ አይነት መንገድ ማስገባት መፈቀድ የለበትም።

ፍራንኮ ቫሉታ ለህብረተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎት ማሳደጊያ ብቻ መዋል እንዳለበት የጠቆሙት ባለሙያው፤



አቶ አማንይሁን ረዳ

ነጋዴዎች አገሪቷ የገጠማትን የመሠረታዊ ፍጆታ አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው መክረዋል። ፍቃዱ መሰጠት ያለበትም አገሪቷ ያላትን ውስን የውጭ ምንዛሬና የህብረተሰቡን መሠረታዊ ችግር ለሚቀርፉና ለህብረተሰቡ መሠረታዊ አቅርቦቶችን ለሚያሳድጉ ብቻ እንደሆነ ጠቅሰዋል። ምርት ወደ ውጪ ሲላክም ሆነ ከውጪ ሲገባ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የውጭ ምንዛሬ ከአገር እንዲወጣ፤ ወደ አገር ቤት መግባት ያለበትንም እንዲቀር እንዳያደርግ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ሲሉ አስገንዝበዋል።

አቶ አማንይሁን አክለውም፤ “የፖሊሲን ትክክለኛነት የሚያረጋግጠው ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ብቻ ነው። ህዝቡ ካለበት ችግር አንጻር ትክክለኛ ውሳኔ ነው። ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ከፍተኛ የምርት እጥረት አለ። ከውጭ ስናስገባ ደግሞ በመላው ዓለም በኮሮና፣ አሁን ላይ ያለው የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት፣ ከዛም ቀደም ብሎ በአሜሪካና በቻይና የንግድ ፍጥጫ ከፍተኛ የሆነ የአቅርቦት ሰንሰለት መናጋት አለ። በዚህ ምክንያት በዓለም ላይ ከፍተኛ የሆነ የምርት እጥረት አቅርቦት መስተጓጎል ባለበት ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ ተከስቷል” ብለዋል።

አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ፍራንኮ ቫሉታ በተወሰነ መልኩ የምርት እጥረትን ለመቅረፍ እንዲሁም የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር እንደሚያስችልና የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ አሊያም ባለበት ለማቆየትም እንደሚያግዝ አመላክተዋል።

በዚህ ወቅት እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ማረጋጋት እንዲቻል ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የሕፃናት ወተትና ሩዝ በፍራንኮ ቫሉታ በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ ተፈቅዶ እንዲገባ መንግሥት ማወጁ ይታወቃል።



# መንግሥት የዜጎችን ደህንነት ለማስከበር ፈጣን እርምጃ መውሰድ እንደሚኖርበት ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- መንግስት የዜጎችን ሰላምና ደህንነትን ለማስከበር ስርአትን የተከተለና ፈጣን እርምጃ መውሰድ እንደሚኖርበት የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ሊቀመንበር አቶ የሸዋስ አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤቱ ከዚህ በፊት በርካታ ጊዜ መግለጫ አውጥቷል። ኢዜማም ሀገሪቱ ያለችበት ሁኔታ አሳሳቢ እንደነበር በተደጋጋሚ ሲገልጽ ቆይቷል።ከዚህ አኳያ የዜጎችን መፈናቀል ለመታደግ ብሎም የዜጎችን ሰላምና ደህንነትን ለማስከበር መንግስት ስርአትን የተከተለና ፈጣን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት ቀድሞ ዜጎች ሳይጎዱ መድረስ አለበት ያሉት ሊቀመንበሩ፤ ሀገርንና ዜጎችን ከጥቃት መጠበቅ፤ በሰላም ወጥተው እንዲገቡና ስራቸውን በነጻነት እንዲሰሩ ማስቻል ቀዳሚ ስራው መሆን አለበት። የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ያውጣም መግለጫ ጥሩ ቢሆንም ስርአትን የተከተለና ፈጣን እርምጃን ተጋባራዊ ማድረግን የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ የሸዋስ ገለጻ፤ የዜጎችን ሰላም ለማስከበር መንግስት ከሕዝብ ጋር መስራት አለበት። ዜጎችን ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል እንዲችሉ በየአካባቢያቸው በማደራጀት ራሳቸውን ከፍ ሲልም ሀገራቸውን ፖሊስ ሆነው እንዲጠብቁ ማድረግ ያስፈልጋል። የተደራጀ ማሕበረሰብ ሀገሩን ይጠብቃል፤ መደበኛ የመንግስት ፖሊስ ሁሉም የሀገሪቷ ክፍል ሊደርስ ስለማይችል ህብረተሰቡን ማስተባበርና ማደራጀት እንደሚገባ ገልጸዋል።

በአደጉ ሀገሮች ያለው ተሞክሮና ልምድ ሀገሩን ፖሊስ ሆኖ የሚጠብቀው ዜጋው ነው ያሉት አቶ የሸዋስ፤ ለስራ በተንቀሳቀስንባቸው የውጭ ሀገሮች መታዘብ የቻልነው ጸጉረ ልውጥ ሰው ሲመለከት ዜጋው ማነህ? ከየት ነህ? ብለው ፓስፖርት ይጠይቃሉ። ጤነኛ ሰው ከሆነ በሰላም ይለቁታል፤ ስጋት የሚፈጥር መስሎ ከታያቸው ለፖሊስ ያመለክታሉ። ይህ ደግሞ ሀገርንና ዜጎችን ከደህንነት ስጋት ለመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው በእኛ ሀገርም ሊለመድ እንደሚገባው አሳስበዋል።

ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት፤ ብዙ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና በርካታ ቀበሌዎች አሏት ያሉት ሊቀመንበሩ፤ በመደበኛ የመንግስት የፖሊስ ኃይል ብቻ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ አይቻልም። ከቀበሌ ጀምሮ ሁሉም ዜጋ በሚኖርበትና በሚሰራበት አካባቢ የራሱን ደህንነት መጠበቅ አለበት። የአንዱ ግለሰብ ነጻነት በሌላኛው ነጻነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ተገንዝቦ ሁሉም ጎረቤቱን እንዲጠብቅ ማድረግ ከመንግስት ያስፈልጋል።

ለብቻ ሰላም ማጣት ለብቻ ደግሞ ሰላም ማግኘት የሚባል ነገር ስለሌለ መንግስት ካወጣው መግለጫ በተጨማሪ ከሌሎች ግብረሰናይ ድርጅቶችና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በጋራ በመሆን ማሕበረሰቡን ለሰላም ማደራጀት ቢቻልና የሰላም ንቅናቄ ቢደረግ ለውጥ ይመጣል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

# በኦሮሚያ ክልል ድርቁ ባስከተለው ጉዳት አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን እንስሳት መሞታቸው ተገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በተከሰተው ድርቅ ከ26 ቢሊየን ብር በላይ የሚገመቱ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን እንስሳት መሞታቸውን የክልሉ የአደጋና ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

በኮሚሽኑ የቅድመ ማስጠንቀቂያና አደጋ ስጋት ቅነሳ ዳይሬክተር አቶ ቤኛ ዱሬሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በስምንት ዞኖች በተከሰተው ደርቅ 14 ሚሊዮን የሚሆኑ እንስሳት ጉዳት ደርሶባቸዋል። ከ26 ቢሊየን ብር በላይ የሚገመቱ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን እንስሳት ሞተዋል።

በክልሉ የበልግና የመኸር ወቅት በተከታታይነት መጥፋቱ ስምንቱም ዞኖች ከፍተኛ ድርቅ እንዲከሰት አድርጓል ያሉት አቶ ቤኛ፤ በአጠቃላይ የምግብ እጥረትና የውሃ ችግር የገጠማቸውና ጉዳት ደርሶባቸዋል ተብለው በጥናት የተለዩት 14 ሚሊዮን ከብቶች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ለከብቶች መኖ ማቅረብ እጅግ ፈታኝ በመሆኑ በከብቶች፣ ፍየሎችና ግመሎች ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ቤኛ፤ጉዳት ከደረሰባቸው ከብቶች 10 በመቶ ለሚሆኑት መንግሥት የመኖ ድጋፍ ምላሽ እየሰጠ ነው። በተጨማሪም በምስራቅ ባሌና ጉጂ አካባቢዎች ድርቁ አሁንም ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ መሆኑን ገልጸዋል።

መጪው የበልግ ዝናብ የሚቀጥል ከሆነ ጉዳቱ የሚቀንስበት ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ ይጠበቃል ያሉት አቶ ቤኛ፤ እስካሁን የአየር ትንቢያ መረጃው እንደሚያመላክተው በምስራቅና በምስራቅ ደቡብ የኦሮሚያ አካባቢ ላይ የሚኖረው የአየር ሁኔታ ደረቃማ በመሆኑ ስጋት አሳድሯል ብለዋል።

በድርቁ ሳቢያ እስካሁን ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ ከብቶች ወድቀው በሰው ድጋፍ የሚነሱና የሚንቀሳቀሱ መሆኑን አውስተው፤ ድርቁ በክልሉ ብሎም በአገር ኢኮኖሚ ላይ ላይ ሊያስከተል የሚችለው ጫና ከፍተኛ መሆኑን አቶ ቤኛ ዱሬሳ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ቤኛ ገለጻ፤ በድርቁ ሳቢያ ሰዎች አስቸጋሪ የሆነ የምግብ እጥረት፣ የውሃ እጥረት፣ እንስሳት የመኖና የውሃ እጥረት ገጥሟቸዋል። ድርቁ በተለይም በቦረናና ምስራቅ ባሌ ላይ ጉዳቱ ከፍተኛ ነው። የክልሉ መንግሥት ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመተባበር ጉዳቱን የሚመጥን ምላሽ ለመስጠት እየተሰራ ነው። እስካሁን አጠቃላይ በክልሉ፣ የፌዴራል መንግሥትና ሕዝቡን በማስተባበር፣ የተለያዩ የግልና ለጋሽ ድርጅቶችን በማቀናጀት በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገ ነው።



ፎቶ ጸሃይ ንጉሴ

አቶ ቤኛ ዱሬሳ



# አቶ አህመድ ሽዴ ከአይ ኤም ኤፍ ማኔጂንግ ዳይሬክተር እና ከቢልና ሜሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን ሊቀመንበር ጋር ተወያዩ

አዲስ አበባ፤ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ገዢ ዶክተር ይናገር ደሴ ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም /አይ ኤም ኤፍ/ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ክሪስታሊና ጆርጊቫ ጋር ተወያዩ ።

በውይይታቸው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ማጠናከር በሚቻልበት እንዲሁም በግጭት እና በድርቅ ሳቢያ የተከሰቱት ችግሮች ለመፍታት በሚቻልበት ጉዳዮች ዙሪያ መክረዋል።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋሙ ውይይቱ ውጤታማ እንደነበርም በፌስ ቡክ ገፁ አስፍሯል።

በዋሺንግተን ዲሲ እየተካሄደ በሚገኘው በዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ዓመታዊ ስብሰባ ላይ እየተሳተፈ ያለውና በገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ የተመራው ልኡክ ከስብሰባው ጎን ለጎን ከተለያዩ አለም አቀፍ አካላት ጋር እየተወያየ ይገኛል።

በተመሳሳይ በአቶ አህመድ ሽዴ የተመራው ልዑክ ከቢል እና ሜሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን መስራች እና ሊቀመንበር ጋር ተወያየ

በአቶ አህመድ ሽዴ የተመራው የልዑካን ቡድን ከቢል እና ሜሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን መስራች እና ተባባሪ ሊቀመንበር ከሆኑት ሜሊንዳ ጌትስ ጋር ተወያየ።

በውይይታቸው ፋውንዴሽኑ በኢትዮጵያ በጤና፣ግብርና እና ዲጂታል ዘርፎች እያከናወናቸው ስላሉ ተግባራት መክረዋል።

በዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ዓመታዊ ስብሰባ ላይ እየተሳተፈ ያለው ልዑክ ከስብሰባው ጉን ለጎን ከዓለም ባንክ የምሥራቅና የደቡባዊ አፍሪካ አገራት ተወካይ ዳይሬክተር አስማን ዲዮን፣ከብሪታኒያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ሚኒስትር ቪኪ ፎርድ ጋር እንዲሁም ከሌሎች አለም አቀፍ አካላት ጋር በሁለትዮሽና በኢኮኖሚ ትብብር ጉዳዮች ላይ ተወያይቷል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ገዢ ዶክተር ይናገር ደሴ እና የገንዘብ ሚኒስትር ዲኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ጋር ወደስፍራው ማቅናታቸው ይታወሳል።

ዜና


ወይዘሮ ወሰኔ ይመር


ወይዘሮ ምስራቅ ባዩ


አቶ በለጠ ከለቻ

ፎቶ ገባቦ ገብሬ

# ከጎዳና ወደ ቤተ መንግሥት የተጠሩት የክብር እንግዶች አንደበት

**ጌትነት ምህረቴ**

ጊዜ ጣለኝ እንጂ በስራዬ መንግሥትንና ህዝብን አገልግያለሁ የሚሉት ወይዘሮ ወሰኔ ይመር፤ በአጋጠማቸው የጤና እክል ዛሬ የጎዳና ተዳዳሪ ሆነዋል። አንድ ልጃቸውን አገር ተወረረች ሲባል አዝምተዋል።መርቀው ልከዋል።እኝህን እናት ያገኘናቸው በአንድነት ፓርክ ውስጥ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከጎዳና ኑሮችን ወደ አንድነት ፓርክ ጠርቶ ምሳ ይጋብዘናል ብዬ አስቤ አላውቅም።ድሆችን የሚያስብ መሪ በህይወቴ አላየሁም።አምላክ አገራችንን ሰላም ያድርግልን የሚሉት ወይዘሮ ወሰኔ፤ እኔ ጎዳና ላይ እየኖሩኩ እንኳ አገር ሰላም እንድትሆን እፈልጋለሁ ብለዋል።

እኔ በጤናዬ ጊዜ ህዝብንና መንግሥትን አገልግያለሁ፤ አሁን በጤና ምክንያት የገቢየ አቅም እየተመናመነ ሄዶ ጎዳና ላይ ወጥቻለሁ ያሉት ወይዘሮ ወሰኔ፤ የፋሲካ በዓል ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ አንድነት ፓርክ ውስጥ በደመቀ ሁኔታ ማክበሬ ለእኔ ትልቅ ደስታ ነው።ምክንያቱም ሀብታም ይሁን ባለሥልጣን ለአምስት ዓመታት ጎዳና ስኖር የጋበዘኝም የደገፈኝም የለም ሲሉ ተናግረዋል።ትውልዱ አቅመ ደካሞችን መደገፍ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢማር ከሰው ባያገኘው የህሊና ዕርካታ ያገኛል ብለዋል።

ወይዘሮ ምስራቅ ባዩ ይባላሉ።ሁለት ልጆች አሏቸው። ባለቤታቸው ከሞተ 12 ዓመታት እንዳለፈ ያወሳሉ። በእነዚህ ዓመታት ሁለቱን ልጆች የማሳደጉ ተግባር በእሳቸው ትከሻ ላይ ነው የወደቀው።ቋሚ ስራ ደግሞ የላቸውም። ፈታኝ ዓመታት አልፈዋል።ባለፉት አምስት ዓመታት የሴፍትኔት ተጠቃሚ በመሆናቸው ቢያንስ መደጎሚያ የምትሆን ገቢ ማግኘት መጀመራቸውን ይናገራሉ።በዚሁ ሴፍትኔት ስራም ከጠዋቱ12 ሰዓት ጀምሮ እስከ 3 ሰዓት ድረስ ጎዳና እያጸዱ በሚያገኟት ገቢ ሁለት ልጆቻቸውን ያስተዳድራሉ።

በዓል ማክበር ለእኔ ቅጦት ነው የሚሉት ወይዘሮ ምስራቅ፤በጥገኝነት ከሚኖሩባት ደሳሳ ቤታቸው ተጠርተው አንድነት ፓርክ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተገኙበት የምሳ ግብዣ መጋበዛቸው በጣም ደስታ ተሰምቶኛል። ምክንያቱም ይህን ክብር አይቼው፣አግኝቼውም አላውቅም ሲሉ ገልጸዋል።ከዚህ በፊትም በዓልን ከአቅመ ደካማ አክስታቸው ጋር ያለችውን ዳቦም ቢሆን ተቃምሰን ነው የምናከብረው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሌሎች መንግሥታት አይተን የማናውቀውን የበጎነት ተግባር አሳይተውናል የሚሉት ደግሞ አዛውንቱ አቶ በለጠ ከለቻ ናቸው።ላለፉት 20 ዓመታት አስታዋሽ አላገኘሁም ።አሁን በጠቅላይ ሚኒስትሩ መጋበዝ ቀርቶ መጠራት ክብር ነው። አሁን አገራችንን ሰላም ያድርግልን። መጪው ጊዜ ጥሩ ይሆናል፤ እንተባበር እንደጋገፍ ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከአሁን በፊት በዓላትን በጎዳና ላይ ነው የማከብራቸው የሚለው የጎዳና ተዳዳሪው ሰለሞን አርአያ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ የፋሲካን በዓል ምክንያት አድርገው የምሳ ግብዣ ስላደረጉልን በጣም ደስ ብሎኛል። ያስደሰተኝ ደግሞ ምግቡ ሳይሆን እኛን ማሰባቸው ነው። በህይወቴ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ ገብቼ በዓል አከብራለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ብሏል።

አገራችንን ሰላም ያድርግልን ለዚህም ሁላችንም የአቅማችንን መስራት ይኖርብናል የሚለው ሰለሞን፤ የጎዳና ህይወት የሚለወጠው ሆነ በጎዳና ላይ ኑሮ ላይ ሰላም ማግኘት የሚቻለው አገር ሰላም ስትሆን ስለሆነ ለአገራችን ሰላም ሁሉም ጠበቃ መሆን እንዳለበት ተናግሯል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለጎዳና ተዳዳሪዎች፣ጧሪ ለሌላቸው አቅመ ደካማ አዛውንቶችና ቤተሰብ ለሌላቸው ህጻናት የፋሲካን በዓል ምክንያት በማድረግ ትናንት በአንድነት ፓርክ የምሳ ግብዣ አድርገዋል።

በምሳ ግብዣው የተሳተፉ ወገኖች 230 ሲሆኑ፤ በፋሲካ በዓል አንድነት ፓርክ ተጠርተው የምሳ ግብዣ የተደረገላቸው መሆኑ ያልጠበቁት መሆኑን በመግለጽ ጠቅላይ ሚኒስትሩን አመስግነዋል።

# ከኢድ እስከ ኢድ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጉባዔ ብዙ ነገር ይጠበቅበታል።

ኢትዮጵያ እንደ ክርስትና እምነት ሁሉ ለእስልምና እምነትም የማትረሳ ባለውለታ በመሆኗ ከተለያዩ የዓረብ አገራት ለሚመጡ እንግዶች የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንቅስቃሴዎች ማድረግ እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ በተለይ በዓረብኛ ቋንቋ ሃማኖታዊ ክንዋኔዎችን፣የቱሪስት መስህቦችን፣የኢንቨስትመንት አማራጮችንና በንግድ ዘርፎች እንቅስቃሴ ግንዛቤ የሚሰጡ መጽሔቶች ወይም መጽሐፎች አዘጋጅቶ ለመስጠት ከወዲሁ መታሰብ እንዳለበት አስገንዝበዋል። ለዚህ ደግሞ የእስልምና ጉባዔው ከውጭ ጉዳይ ጋር በመሆን የድርሻውን በአግባቡ እንዲወጣ ጠይቀዋል።

በመርሀ ግብሩ የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት ገጽታን የሚያጎሉ እንደ ነጃሺ መስጊድ፣የባሌ ሶፍ ዑመር፣የሐረርና የጅማ ታሪኮችን በደንብ በማስተዋወቅ በርካታ ቱሪስቶች እንዲመጡ ሰፊ እድል ይፈጥራል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ከዚህ አንጻር ከዓረቡ ዓለም ጋር ያለንን ወዳጅነት ከማጠናከሩ በተጨማሪ ከቱሪዝም የሚገኘው ገቢ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የሚኖረው ፋይዳ የጎላ መሆኑን አስረድተዋል።

በመካከለኛው ምስራቅ በጉልህ የሚታየውን የውሃና የምግብ ዋስትና ችግር ለመቅረፍ ኢትዮጵያ ካላት የተፈጥሮ ሀብት አኳያ ብቸኛ አማራጭ መሆኗ በአፍሪካ ህብረት ጉባዔ ለመዘገብ የሚመጡ የዓረብ አገራት ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጉዳይ መሆኑን ያወሱት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ በአገሪቱ ያሉ እምቅ የኢንቨስትመንት መስኮችን ለማስተዋወቅ ብሎ ኢትዮጵያ ለእስልምና ሃይማኖት የዋለችውን ውለታ ለማስረጽ ትልቅ ጉባኤ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግም አመልክተዋል።

እንደ ምሁሩ ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ እስልምና ጉባኤ የአገሪቱን ባለውለታነት ከመግለጽ አኳያ ሚናውን በሚፈለገው ልክ አልተጫወተም። ነገር ግን አሁን ግን ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሯል። በኢድ እስከ ኢድ መርሀ ግብር ከተለያዩ የዓለም አገራት የሚመጡትን እንግዶች የአምባሳደር ሚናቸውን በተገቢው እንዲጫወቱ በደንብ ማስታጠቅ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ለዓረቡ ዓለም ባለውለታ መሆኗ በትክክል ካለመገለጹ የተነሳ ዛሬ ላይ በተለያዩ ምክንያቶች በርካታ የኢትዮጵያ ዜጎች በአረብ አገራት መስራት ተከልክለው ወደ አገር እየተመለሱ መሆናቸውን የጠቀሱት ምሁሩ ኢትዮጵያውያን የተፈጠሩትን ቭዥታዎችን በማጥራት ጎን ለጎን ዜጎቹ በዓረብ አገራት መስራት የሚያስችላቸውን የሙያና የቋንቋ ክህሎታቸው ከማዳበር አንጻር በቂ ሥራ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል።

# መገናኛ ብዙኃን የምክክር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የሆነ የመረጃ ዕድል በመስጠት ከሕዝብ ጋር የተጣራ ዘገባ ማድረስ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የምክክር ኮሚሽኑም ለመገናኛ ብዙኃን ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በአስፈላጊው ሰዓት በማቅረብ ተደራሽ የመሆን ግዴታ እንዳለበት ጠቁመዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ መገናኛ ብዙኃኑ ህብረተሰቡን በውስጥ ሃሳብ ከማጠርና አስተሳሰቡን ከመገደብ መቆጠብ አለባቸው። ብዝሃነትን የሚቀበሉና ጽንፈኝነትን የማያራግቡ ሆነው ምክክሩን በአግባቡ ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል።

የምክክር ኮሚሽኑ በሚፈጥራቸው መድረኮችና አጀንዳዎች መሰረት ለውይይት ክፍት የሚያደርጋቸው ጉዳዮች ይኖራሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይህን መሠረት በማድረግ መገናኛ ብዙሃኑም በጽኑ ዲሲፕሊንና ራሳቸው አጀንዳ ከሚሰጡበትና አላስፈላጊ የጥብቅና ሚና ቆጥበው መዘገብ አለባቸው ብለዋል።

በአገራዊ ምክክሩ ላይ የሚተላለፉ ዘገባዎችን መሰረት በማድረግ የመገናኛ ብዙኃኑ አሰራር ቁጥጥር እየተደረገበት በየጊዜው ግብረ መልስ ይሰጥበታል ሲሉም ተናግረዋል።

መገናኛ ብዙኃኑም በሥራዎቻቸው ምክክሩ እንዳይሳካ የሚፈልጉ የውስጥና ውጭ ኃይሎችን እንዲሁም በልዩነታችን ላይ ተመሥርተው ግጭቶች ለመፍጠር የሚፈልጉ አካላትን መመከት እንዳለባቸውም ጠቁመዋል።

የአገር አንድነት ፈተና ሆነው ሊቀጥሉ የሚፈልጉ አካላትን ባለማበረታታት መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

አገራዊ ምክክሩ እንዲሳካ እንደሌሎች አገራዊ ፕሮጀክቶች በባለቤትነት መንፈስ መተባበር እንደሚያስፈልግ በመጥቀስ፤ ምክክር ኮሚሽኑ ላይ የሚሰነዘሩ ማንኛውንም ጥቃቶች በመመከት አዎንታዊ ሚና መወጣት እንደሚገባም ነው የገለጹት።

“ከማህበራዊ ሚዲያ ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ለመቅረፍ ጠንካራ ቁጥጥር ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ነው ያሉት አቶ መሐመድ፤ እንደ ተቋም እነዚህን የመገናኛ ብዙኃንና የማህበራዊ ሚዲያዎችን መቆጣጠር የሚያስችል ረቂቅ ሕግ ተዘጋጅቶ ጉዳዩ ለሚመለከተው የፍትህ ሚኒስቴር ቀርቧል። ይህም ረቂቅ መጽደቅ ሲችል ተግባራዊ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

በተጨማሪ የሀሰተኛና ጥላቻ ንግግርን በተመለከተ ለመገናኛ ብዙኃን፣ ለማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎችና ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረቶች መደረጋቸውንም አንስተዋል።

በከፋ ደረጃ የሚሰራጩ ሀሰተኛ መረጃዎችን በመከታተልና ለፍትህ አካላት ጥቆማ በመስጠት የሕግ ተጠያቂነት እንዲፈጠር ተቋሙ ጥረት እንደሚያደርግም ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕግና ጸጥታ የማስከበር ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥል!

ኢትዮጵያ ከማንም ከምንም ትቀድማለች። ሁሉም ዜጋ የህይወት መስዋዕትነት የሚከፍልላት ፤ ወጥቶ ወርዶ የሚደክምላት ከአንድ ሀገሩ ውጪ ሌላ ተለዋጭ ሀገር እንደሌለው ስለተረዳ ነው።

ስለሆነም ለሀገራችን ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ እያንዳንዳችን ሳንታክት እንሰራለን፣ እንለፋለን፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ለሀገራችን ስለሀገራችን የህይወት መስዋዕትነት ጭምር እንከፍላለን። ይሄንን እስካሁን በቆየንበት ዘመን ስናደርገው መጥተናል። አባት እናቶቻችን ይሄንኑ ሲያደርጉ ኖረው ሀገራችንን ከነሙሉ ክብሯ አስረክበውናል። አሁን ያለነው የታሪክ ባለአደራዎች ደግሞ ይሄንኑ አደራ እናስቀጥላለን እንጂ ሀገራችንን ለከፋፋዮች ፣ ሰላምና ደህንነቷን ለሚያውኩ፣ ኢኮኖሚዋን ለሚያቆረቁዙ አሳልፈን አንሰጥም።

የሀገርን ሰላምና ፀጥታ በማስከበር ዙሪያ በቀዳሚነት ኃላፊነት እና ግዴታ ያለበት መንግሥት ነው። ይሄንን ተግባሩን በብቃትና በታማኝነት መወጣት አለበት። ለሀገር ሰላምና ደህንነት ሲባል ሁሉም ዜጋ ከመንግሥት ጎን የመቆም የውዴታ ግዴታውን መወጣት ደግሞ ያስፈልጋል።

በሀገራችን በተለይም ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ የሀገርን ሰላም የሚያውኩ፣ የህዝብን ደህንነት ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ ፣ ዲሞክራሲን የሚያቀጭጩ ተግባራት እዚህም እዚያም ይታያሉ። ከሰላም ይልቅ ጥላቻን የሚሰብኩ ፣ ጦርነት የሚሰብቁ ፣ ሀገርን ለማፍረስ የሚሰሩ መኖራቸውን በተደጋጋሚ ጊዜ ከድርጊታቸው ለማየት ተችሏል። የእነዚህ ቡድኖች ዓላማ ሀገርን ማፍረስ ፣ በሀገሪቱ የተጀመረውን የዲሞክራሲ ሂደት ማጨናገፍ፣ ዜጎችን ማሰቃየት ሲሆን ከፍ ሲል ደግሞ ያለህዝብ ምርጫ የስልጣን ወንበር መቆናጠጥ ነው። ይሄ መቼም አይሆንም፤ እስካሁንም አልሆነም።

አንዴ በኑሮ ውድነት ፣ ሌላ ጊዜ የብሄር ግጭት በመቀስቀስ ፣ በአንዱ ሃይማኖት ላይ ሌላውን በማነሳሳት ፣ ህገወጥ ድርጊቶችን በማስፋፋት ፣ በመሬት ወረራ ... በሌላ በሌላውም የሀገርን ሰላም ለማደፍረስ እና ህዝቡ በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ይሄን የሴረኞች ሴራ ህዝቡ ሊያውቅና ሊነቃ ይገባል።

በተለያየ ጊዜ ስሙንና አይነቱን እየቀያየረ የሚመጣ የሰላም መደፍረስ፣ የሀገርን ሰላምና የህዝብን ደህንነት ስጋት ውስጥ የሚከት ተግባር መንግሥት በአንድ በኩል ሲከላከል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በምክር፣ በተግሳጽና ጎን ለጎን ህግን በማስከበር በሆደ ሰፊነት ሲያስተናግድ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ችግሩ እየሰፋ እንጂ እየጠበበና እየታረመ የሚሄድ አልሆነም። ትዕግስትን እንደፍርሀት የሚቆጥሩ ጸረ ሰላም ሀይሎች ዛሬም ከድርጊታቸው አልተቆጠቡም።

በመሆኑም መንግሥት ከዚህ ቀደም ከነበረው በተጠናከረ መልኩ ሕግን በሚተላለፉ ላይ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ መቀጠል አለበት። ማንኛውም አካል ፣ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የሃይማኖት ተቋም፣ ባለሥልጣን ከህግ በታች መሆኑን ማሳወቅ ይጠበቅበታል። ማንኛውም አካል ከሀገር በታች መሆኑን ሊረዳ ይገባል።

ሀገር ማንም በስሜት እና በቅዠት እየተነሳ የሚፈነጭባት ሳትሆን ለሁሉም እኩል፣ ሰላም የሰፈነባት፣ ደህንነቷ የተረጋገጠባት ሀገር እንድትኖረው ይፈልጋል ። ሀገራችን ብቸኛዋ መታወቂያችን በመሆኗ አክብረናትና አስከብረናት መኖር አለብን። ሀገር ተከብራ የምትኖረው ደግሞ በውስጥም በውጪም ያለው ጠላት አደብ ሲገዛ ነው።

በዚህም በዛም ሽብር የሚነዛው ጦርነት የሚቀሰቅሰው፣ ህዝብ የሚያፈናቅልና የሚገድለው አሸባሪ ቡድን በህግ አግባብ መገዛት ሲችል ብቻ ነው። ይሄንን ኃይል በየትኛውም መልክ አደብ ማስገዛት ደግሞ የመንግሥትም የሕዝብም ግዴታ ነው። መንግሥት ሀገርና ህዝብን ደህንነት የመጠበቅና የማስጠበቅ ህገ መንግሥታዊ ግዴታ አለበት። በመሆኑም ይሄንን ግዴታውን በብቃት ሊወጣ ይገባል።

መንግሥት በሀገራችን የታየው የዲሞክራሲ ጭላንጭል እየሰፋ እንጂ እየተዳፈነ እንዳይሄድ ችግሮችን ሁሉ በሆደ ሰፊነት ሲያልፋቸው ቆይቷል። አሁንም በትዕግስት እያለፋቸው ይገኛል። ሆኖም ግን የእስከዛሬው ትዕግስት በቂ ነው። ህዝብ እየተፈናቀለ እየሞተና በስጋት እየኖረ ፤ ህገወጥነት እያየለ፤ የኢኮኖሚ አሻጥር እየሰፋ፣ ሌብነት እየተባባሰ መቀጠል የለበትም።

ስለሆነም አሁን ላይ በቃ! ማለት ይገባል፣ ያስፈልጋልም። ማንኛውም አካል ከህግ በታች መሆኑን ማወቅ አለበት። ትዕግስት ፍራቻ አለመሆኑን ማሳወቅ ይገባል። በአጠቃላይ ሕዝብ በሀገሩ ኮርቶ ፣ በመንግሥት ተማምኖ በልበ ሙሉነት ኑሮውን እንዲመራ በሁሉም ዘርፍ ህግ የማስከበሩ ሂደት በቆራጥነት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# በቀን ያልተገደበ መልካምነትን ለሰው ልጆች ሁሉ እናድርግ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

የያዝነው ወር ከአጋማሹ በኋላ የሚያስተናግዳቸው ጥቂት ሀይማኖታዊና ህዝባዊ በአላት አሉ። እነዚህ በአላት ሲከበሩ የኖሩ ናቸው፤ ወደፊትም ሲከበሩ የሚቀጥሉ ይሆናል። ሚያዚያ አስራ አራት የስቅለት በአል፣ በአስራ ስድስት ትንሳኤ በሀያ ሶስት አለም አቀፍ የላብ አደሮች ቀን፤ በሀያ አራት ኢድ-አልፈጥር፣ ሀያ ሰባት ደግሞ የአርበኞች መታሰቢያ ናቸው። በእነዚህ ቀናት ደግሞ በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ብዙዎቻችን በህብረት ለመገናኘት እድሉ አለን። እስካሁንም በአብዛኛው ቀናቶቹን የምናሳልፈው በተለመደ የአብሮነትና አንድነት መንፈስ ነው።

ለዛሬው ጉዳይ የነገሬ ማጠንጠኛ ወዲህ ነው። በእነዚህ በዓላት ወቅት ቀን ቆጥረን ከምናደርጋቸው የአብሮነት ከበራ እና የዘመቻ ክንውን በወጣ መልኩ ሰፊው ህዝብ በቀን ያልተገደበ፤ በሁኔታዎች ያልታጠረ የመተሳሰብና የመረዳዳት ብቻ ሳይሆን፤ ሰዎችን ለችግር የማይዳርግ ተግባር በመፈጸም፣ ቢያንስ ለሙታን የሚሰጠውን ፍቅርና እንክብካቤ ለሕያዋን በመስጠት የሕዝብ አንዱ የታሪክ ገጽ ሊሆን ይገባል። በእርግጥ በርካታ ታሪኮች ስንሰማና ስናነብ እንደምንረዳው ሰፊው ህዝብ ታሪክ ተቀባይ እንጂ ታሪክ ሰሪ አይደለም። ታሪክ የሚሰራው ተሸናፊዎች ብልጣ ብልጥ የሚሏቸው በእኔ እይታ ደግሞ ጎበዝና ጀግኖች በሆኑ ግለሰቦች ነው።

ሰፊው ህዝብ ታሪክ የመስራት አጋጣሚ አግኝቶ ቢሆን እንኳ ታሪኩን የሚነግርለት አልያም የሚጽፍለት አይኖርም፤ ምን አልባት ጓደኞቹ ቤተሰቡና ታሪክ ሲፈጽም ያዩት ብቻ ደጋግመው ሊያወሩለት ይችሉ ይሆናል እንጂ። ይህ ደግሞ አንድ ትውልድ የመሻገር እድሉ ጠባብ ነው። ቢሻገር እንኳን ሌላ ማስረጃ አስካልተገኘ ድረስ አፈ-ታሪክን እንደ ሙሉ ታሪክ መቀበል ያዳግታል ወይንም ታሪክ ለማለት አያስደፍርም። ይህም ሆኖ ግን እኔ ህዝቤ እንዲሰራልኝ ለምመኘው ታሪክ ብቁ ነው ብዬ አምናለሁ። ብቻ ህዝቤ ታሪኬ በተናጠል ይመዝገብልኝ እንዳይለኝ እንጂ በቡድን ተጠቅሎ በዘመን ተለይቶ ሊከተብለት ይችላል።

እንደሚታወቀው የሰው ልጅ እንደማንኛው ፍጡር ከመሰሉ ጋር በማህበር ኖሮ በተናጠል የሚሞት ነው። እድል ልበለውና እድለኛ ከሆነ በአንዳንድ አጋጣሚዎች የኔ የሚላቸውን ጨምሮ ከብዙዎች ጋር ሊሞት ይችላል። ካልሆነ «ሞትና ሞሰብ የግል ጣጣ» ነው እንደሚባለው ከትልቁ የዘመን ስብሰባ ቀናችንን እየጠበቅን ብቻችንን ሹልክ እያልን እንሄዳለን። ተሰባስበን ስንኖር ብዙ የማያስማሙን ነገሮች እንዳሉ ያደባባይ ሚስጥር ነው። እንጣላለን፣ እንገፋፋለን ከፋ ሲል እንጫረሳለን። ስንሞት ግን ሁሉም ያዝንልናል ሰማይ ቤት አለ የሚባለው ቦታ ስንሄድም በምህረት የሚቀበለን እንዳለና ሁሉን ነገር እሱ እንደሚያዘጋጀው ይመሰክርልናል። እውነታውን ግን አይቶ የመጣ ስለሌለ ማረጋገጥ የሚቻል አይመስለኝም። እናም... እናም ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ በጥልቅ ሀዘን እየተቀባበለ በመሸከም ወደሰማይ ሄደ ከሚባለው ከማናውቀው ካላየነውና መቼም ከማናየው ነፍስ ተብያችን ለይቶ በጽኑ ፍቅር ይሸኛናል። ይሸኙናል ያልኩት ራቅ አድርጎ ይቀብረናል ላለማለት ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ ግን ብዙዎቻችን የማናስተውለው አንድ ክስተት በተደጋጋሚ ሲከወን ይታያል። አድልዎ ያለበት የስም ለውጥ። ይህ የስም ለውጥ ደግሞ በፍርድ ቤት ሳይቀር ተቀባይነት ያለው ነው። ጾታ አይለይም፤ እድሜ አይቆጥርም፤ ዘር.. ብሄር ሀይማኖት አይመለከተውም። ብቻ መሞቱ ከተረጋገጠ ማንም በስሙ አይጠራም ሬሳው አልያም አስከሬኑ እየተባለ ይጠራል። ማታ ታሞ ሲጠይቀው እከሌ... እከሊት እዝጌር ይማርህ... እግዜር ይማርሽ ያለ ሁሉ ወደማይቀርበት መሄዱን ሲሰማ አስከሬኑ መጣ? ማለት ይጀምራል። ይቺ አንድ ቀን ሁላችንም በክብር የምንጠራባት የማትቀር የማእረግ ስማችን ናት። በቃ ሁሌም ይሄው ነው የሚሆነው ጠቢባኑ እንደሚሉት «ህይወት በገንፎ ተጀምራ በንፍሮ ትጠናቀቃለች» መወለድ ካለ መሞት የማይቀር እጣ ፈንታ ነው።

ስለዚህ መወለድ ወይንም መሞት የማይቀር የተፈጥሮ ሂደት እንጂ የታሪክ አካል አይመስለኝም። በሁለቱ ኩነቶች መካከል የሚኖረን ግዜ ግን በወለዱንና በእንክብካቤ በሚያሳድጉን ወይንም በጥሩ እንክብካቤ በመንናጸፊያ አሳምረው ተንከባክበው በሚቀብሩን አይወሰነም። እንደየቆየንበት ዘመን ከተጠቀምንበት ክፋውንም ደጉንም ለማድረግ እድሉ አለን። በአብዛኛው የደግነት ታሪካችን ትዝ የሚለን ከላይ በተቀመጡት ሀይማኖታዊና ህዝባዊ በአላት ነው። በእነዚህ ቀናት መደጋገፉ መተባበሩ መጠያየቁ መረዳዳቱ ለጉድ ነው። ሌላ ቀን አይራቡ፣ ሌላ ቀን አይታረዙ ይመስል በችግር ውስጥ ያሉ ለበአል እንዳይጎድልባቸው የማንቆፍረው ድንጋይ የለም። አንዳንዶቻችን ሌሎቹ ቀናት ተመርጠው ለግፍና ለሀጢያት የተቀመጡ ይመስል በእነዚህ ቀናት የተከሰተውን አውግዘን ሌላውን ቀለል አድርገን እናየዋለን። በበአላት ፍቅርን ለመስጠት ከምጣደፈው ባላነሰ በአዘቦቱ ከክፉ ስራችን አንቦዝንም። በዚህም የተነሳ ካሉብን ችግሮች አብዛኛዎቹ በራሳችን የተፈጠሩ ወይንም በዝምታችን እዚህ የደረሱ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ባእድ ያልናቸው ክፉ አድራጊ ወራርያን አገራችንን ለቀውን ከሄዱ ድፍን ሰማኒያ አመት ሞላን። የሚገርመው ሰሞኑን ከሚከበሩት አንዱ በአል ይህን የምናዘክርበት ነው። ታዲያ የአንድንትን በዓል በልዩነት ውስጥ ሆነ ማክበር እንዴት ይሆናል?! እኛ ግን እስካሁን እንደ እብድ ውሻ ዘመን እየለየን በረባ ባረባው እንናከሳለን። ለክፉ ስራችን ደግሞ ግዜና ጉልበት ብቻ ሳይሆን ምክንያትም አናጣለትም፤ እንደ ባለሙያ ሴት እርሾ ትንሽ ትንሽ እያስቀረን ቀሪውን ለማቡካት እንጠቀምበታለን። አዲስ እህል አዲስ ውሃ ቢዘጋጅም እርሾው የከረመ ነው። ይኸው ዛሬ ብለን ብለን በኮመጠጠ እርሾ የመረረ ትውልድ ለመፍጠር በቅተናል።

ወደእኛ አገር ጉዳይ ስመጣ ግን ፍቅር የሚለው ነገር በሌላ ቢተረጎም ደስ ይለኛል። አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳየን ከአብዛኞቻችን የሚጠበቀው ደግ መሆን ወይንም ጥሩ መስራትና ፍቅር መስጠት አይደለም። ይህን ጥቂቶች ብቻ ቢያደርጉት ይበቃል። ከብዙዎቻችን የሚጠበቀው ክፉ አለመሆን ነው። ሰውን ማዳን ለህክምና ባለሙያዎች እንተው፤ እኛ ይህን ልንሰራ አይጠበቅብንም፤ ቢያንስ ግን መግደል እናቁም። መጠለያ ለመስራት ከመሯሯጣችን በፊት ማፈናቀላችንን እናቁም። በየሰፈሩ የተቸገረ ለመርዳት ብለን ገንዘብ ከምናወጣ ከቤት ኪራይ ጀምሮ አላግባብ የሚጨምረውን ዋጋ እንተው። የታመመ ለማሳከም ከመሮጥ ይልቅ ሰው ላለማሳመም እንትጋ። ይሄ ደግሞ በግዜ አይወሰንም፤ በቀን የሚገደብም አይለይም።

በተፈጥሮ ችግር አልያም በአጋጣሚ አደጋ የተጎዱትን ለመታደግ ጥቂት ልበቀናዎች ይበቃሉ። በቃ ይህው ነው። ሌላ ምንም አዲስ ነገር የለም። ይህን ማድረግ ትልቅ ታሪክ መስራት ነው ብዬ አምናለሁ። እናም ሰፊው ህዝብ ማን ይጽፍልኛል? ማን ያወራልኛል? አልያም ማን ይዘግበዋል? ሳይል «ለሬሳ» የሚሰጠውን ፍቅር ለህያዋን በማድረግ ደማቅ ታሪክ እንዲሰራ እፈልጋለሁ። በቀን በግዜ በቦታና በሁኔታ ያልተገደበ ፍቅር። ምን አልባት ከተሳካልኝ እኔም ለመጀመር አቅድ አለኝ። ደግ በመስራት ብቻ ሳይሆን ክፉ ባለመስራት ፍቅርን መስጠት።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ፋሽን ተኮር አልባሳት የሚሠሩና የሚያዘጋጁ ወጣቶች እየተፈጠሩ ነው

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በኢትዮጵያ አምራች ኃይል በብዛት፤ ለጨርቃ ጨርቅ ደግሞ ግብአት የሚሆን ጥጥ አላት። ሀገሪቱ ለጥጥ ምርት የተመቸችና ለዚህ ምርት ግብዓት የሚሆኑ የኢንቨስትመንት ስፍራዎችም አሏት። የጨርቃጨርቅ በተለይም የተዘጋጁ ልብሶችን ለሚያመርቱ ፋብሪካዎች የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተገንብተው ዝግጁ መደረጋቸውን ተከትሎም በርካታ የውጭ ኩባንያዎች አልባሳት እያመረቱ ለውጭ ገበያ እየላኩ ናቸው።

ለውጭ ገበያ የሚመረቱት አልባሳት የወቅቱን ፋሽን የተከተሉ እንደመሆናቸው ዘርፉ የፋሽን ኢንዱስትሪ በሀገሪቱ ይበልጥ እግሩን እንዲተክል የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው ማለትም ያስችላል። በኢንዱስትሪው ሰራተኞች ፤ አመራር አካላትና ሌሎች ከኢንዱስትሪው ጋር ትስስር ላላቸው አካላት በመንግሥት በኩል የሚሰጡ ስልጠናዎች ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው።

አቶ ባንቲሁን ገሰሰ ቀድሞ የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ልማት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሚባለው ተቋም የኮሚኒኬሽን ኃላፊ ሆነው ሰርተዋል፤ ተቋሙ አሁን በአዲስ አወቃቀር የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ልማትና ምርምር ማእከል በሚል እንዲጠራ ተደርጓል።

ከፋሽን ጋር በተያያዘ ላነሳንላቸው ጥያቄ አቶ ባንቲሁን እስከ አዲሱ አወቃቀር ድረስ ያለውን መረጃም ሰጥተውናል። እሳቸው እንዳሉት፤ የተቋሙ ተልዕኮ የሰው ኃይል ማብቃት ነው። ዘርፉን የሚደግፉ የቴክኖሎጂ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች ለማፍራት ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመቀናጀት ሲሰራ ቆይቷል። በእዚህም ፋብሪካዎቹ በቂ ገበያ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ድጋፍ ሲደረግላቸው ቆይቷል።

እንደሳቸው ገለጻ፤ በአጠቃላይ በጨርቃ ጨርቅ ዘርፉ ሲታይ በባህላዊ መንገድ ረጅም ጊዜ የቆየ የሥራ ልምድ አለ፤አሁን ባህላዊውን ወደ ዘመናዊ በመቀየር እንዲሁም ፋሽን ተኮር በማድረግ በገበያው ተወዳዳሪ ከመሆን አኳያ ብዙ እየተሠራበት ነው።

ከዘመን ዘመን ተሻግሮ ግዙፍ ገንዘብ ከሚንቀሳቀስበት ዘርፍ አንዱ የአልባሳት ፋሽን መሆኑን ጠቅሰው፣ በአልባሳት ፋሽን በኩል ሠፊ አቅም እንዳለ ይናገራሉ። ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አብዛኛው በጉልበት የሚሠራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያለውን ጉልበት በመጠቀም በጨርቃ ጨርቅ ሠፊ ሥራ ለመሥራት የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪው ከፍተኛ ሚና መጫወቱን ያስረዳሉ።

ከኢትዮጵያ ህዝብ 70 በመቶው ወጣት ነው ፤ ይህ ሀይል ለገበያውም ሆነ ለሥራው ትልቅ አስተዋፅኦ አለው የሚሉት አቶ ባንቲሁን፣ የተማረ ጉልበት ለመጠቀም ነው ኢንዱስትሪ ፓርኮች በሀገር ውስጥ እንዲቋቋሙ የተደረገው ይላሉ። ይህም ዘርፉ በከፍተኛ፣ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች በዘርፉ ተሰማርተው የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪው እንዲያድግ በማድረግ እና ዘርፉ ከባህላዊ አሠራር ጎን ለጎን ወደ ዘመናዊ አሠራር ስፌት ቅድና ፋሽን እንዲሸጋገር አድርጎታል ሲሉ ጠቅሰው፣ ኢንዱስትሪዎቹ ከ100ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠራቸውንም አስታውቀዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በነበሩት ባህላዊ አሠራሮች ለረጅም ጊዜ ጨርቃ ጨርቅን ተጠቅመን ቆይተናል። አሁን ግን ገበያውን ለማሸነፍና የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ፋሽን ተኮር አሠራሮች መከተል ሚና አለው። አልባሳት በፋሽን ከተሠሩ ገበያው የሚረባረብባቸውና ሰው በብዛት ለብሶ የሚታይባቸው ናቸው። የህንድ፣ የቻይና፣ የአሜሪካ እና የተለያዩ ሀገሮች ኩባንያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ እየገቡ በጨርቃ ጨርቅ ዘርፉ በተለያዩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኢንቨስት እያደረጉ ነው። በዚህም ወጣቶች የሥራ ዕድል እያገኙ፣ በዘርፉ እየተሰማሩ የቴክኖሎጂ ሽግግሩ እንዲሳለጥና አሠራሩ እንዲዘምን አድርገውታል።

በዚህም ከፍተኛ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ተናግረው፣ በጣም የዘመኑ የጨርቃ ጨርቅ ምርቶች ወደ ገበያው እየገቡ ነው። ኢንዱስትሪዎቹ በዘመናዊ መንገድ ልምዱን እንዲወስዱ እና የፋሽን አልባሳቱ እንዲዘምኑ ለማድረግ ከውጭ ረጅም ልምድ ያላቸው የተለያዩ ኩባንያዎች ሀገር ውስጥ ገብተው እንዲያመርቱ እየተደረገ ነው፤ በዚህም ቴክኖሎጂዎችን ወደ እኛ ሀገር የማሸጋገር እና ፋሽን ተኮር ፤ውድ ዲዛይን፤ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶች እንዲመረቱ እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ያብራራሉ።

አቶ ባንቲሁን እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርቶች በጣም ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው። ኢንዱስትሪዎች የጨርቃ ጨርቅና አልባሳቱ በጣም የዘመኑና ገበያውን የሚስቡ ሆነው እንዲመረቱ እንዲሁም ፋሽን ተኮር ሆነው እየዘመኑ በሀገር ውስጥም በውጭም ገበያ እንዲያገኙ ለማድረግ እየተሰራ ነው፤ ከባህላዊ መንገድ ወደ ዘመናዊ መንገድ ማሸጋገሩ በራሱ ለገበያ ያላቸውን አስተዋፅኦ የሚያጎላ ነው።

አሁን ወደ ማእከል የተቀየረው ተቋም በግዙፍ እና በጣም ፋሽን ተኮር የሆኑ አልባሳትን ለማምረት በሚያስችሉ መሣሪያዎች የተደራጀ መሆኑን አስታውሰው፣ ቢዚህም ለኢንዱስትሪ ሰራተኞችና መሪዎች ስልጠናዎች ይሰጣሉ፤ ሠልጣኞች ወደ ሥራ ከገቡ በኋላ ግብረ መልስ ይሰበስባል፤ በተሰጠው ሥልጠና መሠረት ደግሞ ፤ጥናትና ምርምር ይደረጋል፤ ግብአት ይሰበስባል ሲሉ ያብራራሉ። በግብአቱ መሠረት ደግሞ እንደገና የገበያ ክፍተቱ እየተለየ በቂ ዕውቀት ያልያዙ በደንብ ሥልጠና እንዲያገኙና ዕውቀትና ክህሎት የሌላቸው እየተለዩ ፤ዕውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ እንደሚደረግ ይገልጻሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ተቋሙ የተለያዩ አልባሳት የሚያመርቱ ለወጣቶች፣ ለወይዛዝርት ለኮረዶች ለጉብሎች የሚያገለግሉ መሣሪያዎች አሉት። ከፋሽን ጋር የሚሄዱ አልባሳት እንዲያመረቱ ከማድረግ አኳያ አጫጭር ሥልጠናዎች ይዘጋጃሉ። ሱፐርቫይዘሮችን ከፋብሪካዎቹ ባለሙያዎችን ፤አመራሮችን እያስመጣ በየጊዜው አጫጭር ሥልጠናዎችን አዘጋጅቶ ሥልጠና ይሰጣል። ባሉት የፕሮጀክት ፈንዶችም በኩል ሥልጠናዎች ይሰጣሉ።

ይህን ሁሉ ተከትሎም ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው ሰዎች ፋሽን ተኮር አልባሳት የሚሠሩና የሚያዘጋጁ ወጣቶች ኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጠሩ መሆናቸውን ነው የተናገሩት። በፊት በሙያው በቂ ክህሎት ያለው ሰው አልነበረም። በባህላዊ መንገድ ብቻ ሲሄዱበት ነበር። በዓለም ገበያ ውስጥ ገብቶ ማምረትና መወዳደር የሚችል ዕውቀትና ክህሎት የነበረው ሰው አልነበረም ይላሉ።

ይህ ሁኔታ ተቀይሯል፤ ከፋብሪካዎች ጋራ ቁርኝት በመፍጠር በየጊዜው ለባለሙያው ፣ ለኦፕሬተሩ ለሠራተኛው ለሱፐርቫይዘሩ ሥራ እየተሰጠ የሰዎችን አቅምና አጠቃላይ ክህሎታቸውንና አመለካከታቸውን የማሳደግ ሥራ በተከታታይ እየተሠራ መሆኑንም ነው የተናገሩት። በገበያ ትስስሩም ፋብሪካዎች ምርታቸውን ወደ ውጭ ሀገሮች መውሰድና መወዳደር እንዲችሉ ለማድረግ የሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች ተወዳዳሪ ሆነው በአነስተኛ ዋጋ አቅርበው ብዙ ምርት በመሸጥ ከፍተኛ ትርፍ የሚያገኙበት ስራ እየተሰራ እንደሆነም ይጠቁማሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ተቋሙ አጠቃላይ የማማከር አገልግሎት በመሥጠት፤በጨርቃ ጨርቅ አልባሳት በጥጥ ዘርፉ ዙርያ የተሰማሩ ፋብሪካዎቹንም እርሻዎቹንም ሁሉ በማካተት ለባለሀብቶቹና ለፋብሪካዎቹ ሙሉ ድጋፍ ይሠጣል። ድጋፎቹ ቴክኒካል እንዲሁም የኢንዱስትሪ ባህሉንና አመራሩን ለማሳደግ የሚያስችሉ ረጅምና የአጭር ጊዜ የአመራር ሥልጠናዎች ናቸው የሚሰጡት።

በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪው የሚሰማሩ ኦፕሬተሮች ባለሙያዎች ሱፐርቫይዘሮች ሁሉ እንዴት ተቀናጅተው ፋብሪካውን መምራት እንዳለባቸው ዕውቀትና ክህሎት የማስጨበጡ ሥራዎች ናቸው የሚሰሩት። ባለሙያዎቹም ሙሉ ዕውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው አጫጭር ሥልጠናዎች እያዘጋጁ ይሰጣሉ።

የስፌት፤ የሽመና አሠራር፤ የፊኒሺንግ ሥራዎች ቴክኖሎጂዎች፤ የምርመራና ላቦራቶሪ ሥራዎች እና የልብስ ስፌት የተለያዩ ዘመናዊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች መሣሪያዎቹን ተጠቅሞ በየጊዜው የዲዛይንና የፋሽን ሥራዎቹ ዘመናዊ እየሆኑ ከወቅቱ ጋር አብረው እንዲሄዱ የሚያደርጉ ሥልጠናዎች እየተዘጋጁ ለኢንዱስትሪ አመራሮች ባለሙያዎችና ለኦፕሬተሮችም በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ይዘጋጃል። በፋብሪካዎቹም ሄዶ ክፍተታቸውን በማጥናትና ክፍተታቸውን ለመሙላት የሚያስችሉ ሥልጠናዎችም ይሰጣሉ።

# ማረፊያ/ትዝብት

## ሽልንጎቹ የት ተሸሸጉ?

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

መቼም ሽልንጌን ስለሚባለው አጭር ልቦለድ ሳትሰሙ አትቀሩም፤ እኔ አንደኛ ደረጃ ተማሪ ሆኜ አማርኛ መጽሐፍ ላይ ማንበቤን አስታውሳለሁ፤ ስዕልም ነበረው። ገጸባህሪዋ ድሬዳዋ ባቡር ተሳፋሪውን እያነጋገረች ተስማምታ ፍራፍሬ ትሸጥና ሂሳቡን ሽልንግ ትጠይቀዋለች። ሽልንጌን አምጣ ትለዋለች፤ ተሳፋሪው ሰጥቼሻለሁ ይላታል። ሲከራከሩ ባቡሩ ይነሳል።

ሴትየዋ ሽልንጌን እያለች ትከተላለች፤ ባቡሩን ልትደርስት አልቻለችም፤ ሰውየው የሚወስደውን ወስዶ ከፍያለሁ ነው ያለው። እሷም ሽልንጌን እያለች እያለቀሰች በርቀት ብትከተለውም ባቡሩ ከአይኗ ተሰወረ። ያኔ ሽልንግ ትልቅ ዋጋ ነበረው፤ ይህን ጉዳይ ያነሳሁት የኔ ትልቅ ዋጋ የነበረው ሽልንግ ዛሬ አቅም አልባ ሆኖ የት ተሸሸገ ብዬ ነው።

አንድ የሳንቲምን ፋይዳ የሚያስረዳ ሌላ ታሪክ ላክል፤ በ1970ዎቹ ዓ.ም ይመስለኛል፤ ከአዲስ አበባ ወጣ ባለ አካባቢ፤ ከወደ አዲስ አበባ የመጣ እንግዳ በእንግድነት ለመጣበት ቤት ባለቤት ልጅ አንድ ብር/ ያኔ ባለወረቀት ነበር/ አውጥቶ ይሰጠዋል፤ ያ ልጅ ዛሬ ትልቅ ቦታ ደርሷል። ብሩን በደስታ ተቀብሎ ይደሰታል ሲባል፤ ልጁ ግን ከፋው፤ ብሩን አልፈልግም አለ፤ አለቀሰም፤ ውሰድ ተብሎ ቢለመን አሻፈረኝ በማለቱ ቀጠለ፤ ምነው ቢሉት እሱ የፈለገው ሳንቲም መሆኑን ገለጸ። ባለወረቀቱ ብር ገንዘብ አልመሰለውም። ሳንቲሞች ተሰጡትና ችግሩ ተፈታ። የሳንቲም ዋጋ እዚያ ድረስ ነበር። በሳንቲም ብዙ ነገር እንደሚገዛ ያውቅ ነበር።

በአገራችን ሳንቲም ትልቅ ስፍራ እንደነበረው ከታሪክም እንረዳለን። ኢትዮጵያ በዓለም ገንዘብን በመጠቀም ቀዳሚ ናት። በአክሱማውያን ዘመንም ሳንቲሞች ለግብይት አገልግሎት ይውሉ ነበር። በዘመኑ ባልደርስባቸውም፤ በቤተመዘክር ገብቼ ባልጎበኛቸውም፤ ዝናቸውን ለመረዳት ምስላቸውን ለማየት ከታደሉት ወገን በመሆኔ እጽናናለሁ።

በዳግማዊ ምኒሊክ ዘመን እንደገና ለግብይት የበቁት ሳንቲሞች የወረቀት ገንዘቦች፤ ነገሥታቱ በተቀየሩ ቁጥር እየተቀየሩ እየታተሙ ለግብይት ይበቁ እንደነበር ካነበብነውና ከሰማነው ታሪክ ልንረዳ እንችላለን። በደርግ ዘመን ብላቴና የነበርን የሳንቲሞች አቅም፣ ዋጋና ብዛታቸው በራሱ ይናገር ነበር። ዛሬ ግን አምስት፣ አስርና ሃያ አምስት ሳንቲሞቹ ደብዛቸው ከጠፋ ቆየ፤ ሽልንግን/ ሃምሳ ሳንቲምን/ ያህል ገንዘብ ተሸሽጓል፤ አፍረው ይሁን ፈርተው አይታወቅም፤ ኪሳቹ ይወቁዋቸው።

ከሦስት ዓመት በፊት አንዳንድ ብላቴናዎች (ህፃናት)፣ ወራዙትና (ወጣቶችና) ወይዛዝርት በታክሲ መሳፈሪያዎች የብር ሳንቲም የመዘርዘር ስራ ያካሂዱ ነበር። ሳንቲሞቹን በመዘርዘር ለራሳቸው የሥራ ዕድል በመፍጠር የተጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም፤ በዚህም አሁን ዋጋ አልባ ለሆኑት ሳንቲሞቻችን ጎንበስ ብለን ብናመሰግናቸው ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር።

ብላቴና ሳለን ወደ ትምህርት ቤትም በሉት መዝናኛ ቤት ስናመራ ሳንቲም ወድቆ እናገኝ ነበር። የወደቀችውን ሳንቲም ዋጋ ስለነበራት ቀድሞ ለማንሳት እንሻኮት እንገፋፋ ነበር። ከአምስት ሳንቲም ያነሰ ዋጋ የነበራት አንድ ሳንቲም ደግሞ ብዙ ጊዜ እርባና ቢስ ስለነበረች መንገድ ላይ ተጥላ እናገኛት ነበር። እያየናት እናልፋታለን። ብናነሳትም ምንም የሚገዛበት ስላልነበረች፤ ስስም ስለነበረች እንሳሳላት ነበር። ምንም ግን የመግዛት አቅም ስላልነበራት መልሰን እንጥላት ነበር።

የዛኔው አንድ ሳንቲም መጠኑ የከሳ፤ ክብደቱ የሳሳና የቀለለ ውበቱ ግን የሚያሳሳና ያማረ ነበር ማለት እችላለሁ። መልኩ ብርማ ይመስላል። የዛሬውን የአንድ ብር ሳንቲም ልክ የያኔው አንድ ሳንቲም ይመስለኝ ጀምሯል። መጠኑና ቁጥሩ ቢጎላም ክብደቱ ቢበዛም አንዲት ስንጥር አይገዛም። ብሮች ተሰባስበው ካልሆነ በቀር። የአንድ ብር ሳንቲም አቅሙን ያጣውና አቅሉን የሳተው፣ ያነሰው ከወረቀት ወደ ብረት ከተሸጋገረ ብዙም ሳይቆይ ነው።

እንመራመር ካልን እኮ ከወረቀት ይልቅ የሚከብደው ብረት ነው፤ አይደል እንዴ ጎበዝ? በሃሳብም እንተጋገዝ። ግን አንድ ብሩ ከወረቀት ወደ ብረት በተለወጠ ጊዜ ሕልውናው ተናወጠ ወይ ብዬ እጠይቃለሁ ለራሴ። ዋጋ የሚያወጡ የነበሩ ፈራንካዎች ዋጋ ሲያጡ ሌላ ምን ማለት ይቻላል?

እኔ የሳንቲሙ አንድ ብር ለሸገርም ለአገርም ችግር ይዞ የመጣ ይመስለኛል። በአንድ ብሩ ሳንቲም ምክንያት አምስት፣ አስር፣ ሃያ አምስት ሳንቲሞች ከገበያ ከወጡ ቆዩ፤ አንድ ሳንቲም ከገበያ ከወጣ መቼና መቼ፤ የሚገርመው እነዚህን ሳንቲሞች ሃምሳ ሳንቲሙም/ ሽልንጉም/ መከተሉ ነው። የሚደንቀው ደግሞ ከሳንቲሞቹ ብዙም ሳይቆይ መሆኑ ነው።

ምን ስለሳንቲሞቹ ታወራለህ ትሉኝ ይሆናል። ይሄው አንድ ብሩም ዳር ዳር እያለው ነው፤ ችግሩ ሳንቲም መሆኑ ላይ ይሆን እንዴ? በቅጡ እናስበው ካልን ይሄ መዘዘኛ አንድ ብር ከወረቀት ወደ ብረት ከተቀየረ በኋላ የባሕርይ ለውጥ አመጣ፤ አቅም አጣ፤ ፈላጊ አጣ፤ ቀስ በቀስ ደግሞ እንደ ተቀሩት ሳንቲሞች እሱም ከገበያ እንዳይወጣ እሰጋለሁ።

አሁን ደግሞ ሌላው ችግር የሆነው ለኔ ቢጤ እንኳ አራት ስሙኒ አይደለም ሃያ ስሙኒ ወይም ሽልንጎች በርከት አድርጋችሁ ብትሰጡዋቸው ከተቀበሉዋችሁ ፈገግ እያሉ ሳይሆን ጭፍግግ ብለው ነው። በታክሲም ላይ አራት ስሙኒ ሳንቲም ሆነ በርከት ያሉ ሽልንጎች ብትከፍሉ ረዳቱ ላይቀበል ይችላል፤ ገንዘብ ነው ተቀበል በትሉትም አይሰማም።

የአንድ ብሩን ሳንቲም አምጣ ብሎ ሊንጣጣ ይችላል። በሕግ መቀበል ግዴታ እንዳለባቸው ብናቅም ከላይ የጠቀስኩዋቸውን በክፍያ መልክ ሳንቲሞች ለመቀበል ፍላጎት የላቸውም። የአስር ሳንቲሙን በብዛት ለመክፈል ብታስቡም አልቀበልም ሊላችሁ ይችላል፤ ለዚያው ጭምት ከሆነ ነው፤ ዋልጌ ከሆነ ደግሞ በጸያፍ ስድብ ሲያሻውም ድብድብ ሊሰነዝር ይችላል።የኔቢጤ ከሆነም የጠቀስኩዋቸውን ሳንቲሞች በርከት አድርጋችሁ ብትሰጡት በንቀትና በአግራሞት ቀና ብሎ እንደሚያያችሁ አትጠርጥሩ።

ነገሩ እየከፋ መጥቷል፤ በታክሲ ላይም የአንድ እና ሁለት ብር መልስ ቢኖራችሁ ላይመልሱላችሁ ይችላሉ። የሶስት ብር መንገድ ተሳፍረው አምስት ብር ሰጥተው ሁለት ብር ይመለስልኛል ብለው ሲጠብቁ ረዳቱ ጭጭ ይሎታል፤ ሁለት ብርን እንደ ያኔው አንድ ሳንቲም እያዩት ነው።

አንድ ሚኒባስ ታክሲ 12 ሰው ይጭናል፤ ከእያንዳንዱ ተጓዥ ላይ አንድ ብር ቢያስቀር 12 ብር ያገኛል፤ ሁለት ብር ቢያስቀር ደግሞ 24 ብር ማለት ነው። እሱ ሲጠራቀም እንደሚጠቅሙ ያውቃል፤ እኛ ሲጠራቀም ይጠቅማል ብለን መልስ ስትጠይቅ ዝም ይሉናል፤ ረዳቶቹ የሚመልሱትም እያላቸው የለም ይሉናል፤ ሊዘረጥጡህ ይሞክራሉ፤ ይህን ስል አሁንስ አንድ ብር ሁለት ብር መልስ የሚጠይቅ መስመር ላይ መግባት እያስጠላኝ ነው ሲል የሰማሁት አንድ የታክሲ አሽከርካሪ ታወሰኝ።

ሁሉም የሳንቲም ቀበኛ ሆኗል፤ የአንበሳ የከተማ አውቶቡስ ቲኬት ቆራጮችም ዘንድ ስትሄዱ እንደዚያው ነው። ቲኬት ቆራጮች ሳንቲም የለንም የዕለት ተዕለት ምላሻቸው ከሆነኮ ቆየ። እናንተም የአንድ ብሩን ሳንቲም ካልያዛችሁ የሦስት ብሩን የአንበሳ የከተማ አውቶቡስ መንገድ አምስት ብር ወዳችሁ ፈቅዳችሁ ትከፍላላችሁ። ሳንቲሙ ሲታተም ለአገልግሎት እንዲብቃቃ ሳይሆን ቀርቶ ይሆን? አገልግሎት ሰጪዎችስ ሳንቲም የለንም ማለት ግን ይችላሉ ?

እናም የአምስት፣ አስር፣ ሃያ አምስት ሳንቲሞቹ ደብዛ መጥፋት ሲገርመን የሽልንጎቹም ደብዛ ጠፋብን፤ ይህን መንገድ የሳንቲም ብሮቹም እየሄዱበት ናቸው። ለዚያውም ራመድ ራመድ እያሉ። ግሽበቱ እንደ አገር ሊያጋጥም የሚችል ሊሆን ይችላል። ፍጥነቱ ግን የሚያም እየሆነ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎችም መንግስትም ቢመክሩበትና መፍትሔ ቢያመለክቱ የተሻለ ይመስለኛል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስም በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ኢኮኖሚውን ለአገራዊ ምክክርና እርቅ... !?

ስለቻይና በተነሳ ቁጥር ተደጋግሞ የሚጠቀስ የናፖሊዎን ቦናፓርት ነብያዊና አስገራሚ አባባል አለ፤ "ከእንቅልፏ ስትነቃ አለምን ስለምትገለባብጥ፤ ቻይናን ተዋት ትተኛ፤" የሚል። ቻይናም የናፖሊዎንን ትዕዛዝ የሰማች ይመስል ለ200 አመታት ሀሳቧን በኮንፊሺየስ ላይ ጥላ በሯን ዘግታና ኩራዟን አጥፍታ ለሽ አለች። ታዋቂው የቻይና ስትራቴጂካዊ አንሰላሳይ ሱን ዚ ደግሞ ሁሉም ጦርነት በድል ወይም በሽንፈት የሚጠናቀቀው ከመደረጉ በፊት ነው ይላል። ማርሽ ቀያሪው የቻይና ፕሬዚዳንት ዴንግ ዣውፒንግ በ1970 ዓ.ም ፤ "ድመቱ አይጧን እስካደነ ድረስ ጥቁር ሆነ ነጭ ግድ አይሰጠንም፤" በማለት፤ ከእርዮተ አለም ይልቅ ኢኮኖሚን ያስቀደመ ስትራቴጂ ቀየሰ። የቻይናን ገበያ በሒደት ለአለም ክፍት አደረገ። በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተን ዘመናዊነት አቀነቀነ። ነጮች እንደሚሉት ከዚያ በኋላ የሆነው ታሪክ ነው። ለዛውም እጅን በአፍ የሚያስጭን ታሪክ፤ ዴንግ ዣውፒንግ በድህነትና በኋላቀርነት ላይ ጦርነት ከመካሄዱ በፊት አሸነፈው።

የቻይና ኢኮኖሚ ለተከታታይ 30 አመታት በየአመቱ ዘጠኝ በመቶ ተመነደገ። ይህ በሰው ልጆች ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም። በእነዚህ አመታት 400 ሚሊየን ቻይናውያን ከድህነት አረንቋ ወጡ። የዜጋዋ የነፍስ ወከፍ ገቢ በሰባት እጥፍ አደገ። የ"The economisቱ" ጄፍሪ ሳችስ፤ "በአለም ታሪክ የቻይናን ያህል የተሳካ ኢኮኖሚያዊ እድገት ያስመዘገበ የለም፤" ያለው ለዚህ ነው። የቻይና የዕድገት ከአእምሮ በላይ ነው። ኢኮኖሚዋ በየስምንት አመቱ በእጥፍ አድጓል። በ1970 ዓ.ም ቻይና በአመት 200 የአየር ማቀዝቀዣዎችን ብቻ ነበር የምታመርተው። በ1997 ዓ.ም ግን ምርቷን ወደ 48 ሚሊዮን አሳደገችው። ዛሬ በአንድ ቀን ወደ ውጭ የምትልከው ምርት በ1970 ዓ.ም አመቱን በሙሉ ትልከው ከነበረው በብዙ ይበልጣል። ቻይናውያንን አጋምዶ የያዘው ይህ ኢኮኖሚያዊ ታምር ነው።

ኮንፊሽየስ፣ ርዕዮተ አለም ወይም ኮምኒዝም አይደለም። ከምንም ነገር በፊት ኢኮኖሚውን ማስቀደማቸው ከአሜሪካ ቀጥሎ 2ኛውን ግዙፍ ኢኮኖሚ እንዲገነቡ አስችሏቸዋል። ምንም እንኳ በዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ ከአሜሪካ በብዙ እጥፍ ያነሰና የዕድገት ጥራት ችግር ያለበት ቢሆንም። በማኦ የባህል አብዮት የተሰበረውን ቅስማቸውን ጠግነዋል። ፈጣኑ ዕድገት ከአሁኑ ፖለቲካዊ ለውጥን መጸነሱ ስለማይቀር የቻይና ኮምኒስት ፓርቲ የሲንጋፖርን፣ የስዊድንና የጃፓንን የሊበራል መንገድ አጥንቶ፣ ቀምሮና አላምዶ ለመተግበር አበክሮ ዕንቅስቃሴ ከጀመረ ከራረመ። ከዚህ የተረዳሁት የቻይና ኢኮኖሚያዊ ተአምር ያደሩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች ችግሮቿን በማያዳግም ሁኔታ ለመፍታት ቁልፍ መሆኑን ነው። ዛሬ አገራችን ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችና ቀውሶች የድህነታችንና የኋላቀርነታችን ውጤት ናቸው ብዬ አምናለሁ።

ውስን የሆነው ሀብት ደግሞ በመንግስት እጅ ስለሆነ ሁሉም በስስትና በመጎምዠት አይኑን ከመጣል አልፎ ባቋራጭ ለመቆጣጠርና ለመቀራመት ፖለቲካዊ ስልጣንን መያዝን እንደ ስልት ይከተላል። ሕወሓት፣ ሸኔ፣ የጉምዝ ታጣቂ፣ የአገው ሸንጎ፣ የቅማንትና ሌሎች አገራችንና ሕዝባችንን እረፍት የነሷት እንታገልለታለን ለሚሉትና በስሙ አስር ጊዜ ለሚምሉለትና ለሚገዘቱለት ሕዝብ ጥቅም ሳይሆን ለስልጣን ነው። ስልጣንን ይዞ በአቋራጭ የአገሪቱን ሀብት ተቆጣጥሮ የግላቸውንና የቡድናቸውን ጥቅም ለማሳደድ። መሬቱም፣ ማዕድኑም፣ በጀቱም፣ ሁሉም በመንግስት መዳፍ ስር ስለሆነ፤ የፖለቲካዊ ስልጣን በመያዝ ይሄን መዳፉን ፈልቅቆ ሀብትን ለመቆጣጠር ፖለቲካዊ ስልጣን የሞት ሽረት ጉዳይ ሆኗል። ሕወሓት በስልጣን ጥም ጢምቢራው እስኪዞር የሰከረው የትግራዋይን መብትና ጥቅም ለማስከበር ሳይሆን ለ27 አመታት ባካሄደው ዘረፋ ባለመጠርቃቱ ነው። እኩልነትንና ፍትሐዊነትን እንደወንጀል ቆጥሮ ይሄን ሁሉ ምስቅልቅል፣ እልቂትና ቀውስ ያመጣብን አልጠግብ ባይነቱ ነው። ሕገ መንግስቱና የፌደራል ስርዓቱ ሰበብና ሽፋን ነው። ሕወሓትን ጨምሮ ሌሎች የሽብር ኃይሎች ለስልጣን አራራቸው እንደሽፋን የሚጠቀሙባቸው ያሉብንን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮችን ነውና ተረባርቦ ፈትቶ ሰበብ ማሳጣትና እነዚህን ኃይሎች ከሕዝብ መነጠል ያሻል።

ሕወሓት የብሔር ብሔረሰቦችን ጥያቄ ወደፊት ያመጣው ለብሔረሰቦች መብት አሳቢና ተቆርቋሪ ሆኖ ሳይሆን፣ ከፋፍሎ ስልጣን ላይ ለመቆየት ነው። እንደ ቅኝ ገዥዎች ከፋፍሎ ለመግዛት ነው። ሕወሓትን ጥቁሩ ቅኝ ገዥ የሚያደርገው ይሄ ባህሪው ነው። አሁን ስራ ላይ ያለው ሕገ መንግስት እየተረቀቀ እያለ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ፤ ረቂቁን ለፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ሲያሳያቸው ለምን እንዲህ አደገኛና ከፋፋይ ሕገ መንግስት ማርቀቅ አስፈለገ ብለው ሲጠይቁት፤ መለስ በወቅቱ የሰጣቸው መልስ እንዲህ ካላደረግን ስልጣን ላይ መቆየት አንችልም የሚል አስደንጋጭ ምላሽ ነበር። ሕገ መንግስቱ ከፋፋይና አገርን አደጋ ላይ እንዲጥል ሆኖ የተረቀቀው የብሔር ብሔረሰቦችን ጥያቄ ለመመለስ ሳይሆን ሕወሓት ያለተቀናቃኝና ተፎካካሪ አገዛዝ ላይ ለማስቀመጥ ነው። ለዚህ አንዱንም የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ሳይመልስ የጨነገፈው። ጭቆናው የመደብ ነው ወይስ የብሔር የሚለው ክርክር እንዳለ ሆኖ፤ ኢጋርና አባል ድርጅቶች እያለ ይቆምር የነበረው ለዚህ ነው።

ይሄን ከፋፋይና እኩይ አላማውን ለማሳካት በፈጠራ ትርክት ላይ በመመስረት ጥላችን፣ ልዩነትን፣ ጥርጣሬንና በጎሪጥ መተያየትን ለ50 አመታት በጀት መድቦ መዋቅራዊና ተቋማዊ አድርጎ አራገበው። አቀነቀነው። ዛሬ እያጨድን ያለነው ይሄን ዘሩን ነው። በአገራችን አራቱ ማዕዘናት የሚያገረሹት ቀውሶች መነሻቸው ይሄ ክፉ ዘር ነው። ዛሬ በገዥው፣ በተፎካካሪና በተቃዋሚ ፖርቲዎች የምናስተውለው ውዝግብና መሳሳብ የዚህ ቅርሻ ነው። በብዙኃን መገናኛዎች የሚንበለበለው የጥላቻና የልዩነት ፍላጻ መነሻው ከሕወሓት መወጠሪያ (ደጋን) ነው። የምንገኝበት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ መነሻም ከሕወሓት የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ከስራቱና ከውቅሩ የሚመነጭ ነው። አሁን የምንገኝበት ሁለንተናዊ ቀውስ በእዳ ከሕወሓት የተላለፈልን ነው። ብልጽግናም ሌላው ባለዕዳ ነው። አሁን እየወረደብን ያለው የቀውስ ቋጥኝና ናዳ የብልጽግና ብቻ አድርገን ካየነው ችግሩን በቅጡ አልተረዳነውም ማለት ነው። ብልጽግና ተጠያቂና ተወቃሽ የሚሆነው አቅሙ የፈቀደለትን ያህል ጥረት አድርጓል ወይስ አላደረገም የሚለው ነው።

የተንሰራፋው ስራ አጥነት፣ በዋና ዋና መሠረታዊ ሸቀጦች ላይ 100 በመቶ እንዳለፈ የሚነገርለት የዋጋ ግሽበት፤ አልቀመስ ያለው የኑሮ ውድነት፤ ይሄን ተከትሎ የሚስተዋለው የሞራልና የቅስም ስብራት፤ በሰላም ወጥቶ መግባት ዋስትና ያጣው፤ በንጹሐን ላይ የሚፈጸም ጭፍጨፋና መፈናቀል፤ እየገነገነ የመጣው ሙስና፤ እንደ ሰደድ እሳት እየተስፋፋ ያለው ብልሹ አሰራር፤ አይን ያወጣው ዘረፋና ሙስና፤ እየተካረረ የመጣው ጎሰኝነት እና ሌሎች አገራዊና ሕዝባዊ ህመሞች መነሻዎች በርካታ ቢሆኑም የሕወሓት ባህሪና የተሳሳተ ርዕዮተ አለም ግን ዋነኛው ነው። ደረጃው ይለያይ እንጂ በአንድም በሌላ በኩል እኔም እናንተም ተጠያቂ ነን። አነዚህን ጎልቆ መሳፍርት የሌላቸውን ችግሮች ለመቅረፍ እንደየባህሪያቸው ፖሊሲና ስትራቴጂ ቢያስፈልጋቸውም፤ የሚሸከማቸውና ይዟቸው የሚነሳ አስማት (ማጂክ) ይፈልጋሉ። ይሄ አስማት ደግሞ ኢኮኖሚው ነው።

ኢኮኖሚው ችግሮቻችን የመፍቻ ዋና ቁልፍ (ማስተርኪይ) ነው። አሁን ከገባንበት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቅርቃር የመውጫ የማሪያም መንገዳችን ነው። አገርም ሕዝብም ሆኖ ለመዳን ፍቱን መድህኒታችን ነው። የኑሮ ውድነት፣ የዋጋ ግሽበት፣ ስራ አጥነት፣ ድህነት፣ ችጋር፣ ቸነፈር፣ ጠኔ፣ ርሀብ፣ እርዛት ብሔር ወይም ሀይማኖት የላቸውም። አማራም፣ ትግራዋይም፣ ኦሮሞም፣ ሶማሌም፣ አፋርም፣ ወዘተረፈ አይደሉም። ኦርቶዶክስ፣ እስላም፣ ክርስቲያን፣ ካቶሊክ፣ ዋቄ ፈናም አይደሉም። ያለልዩነት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ችግሮች ናቸው። ቢቀረፉ ሁሉንም ያለልዩነት እልል የሚያሰኙ፤ ባይቀረፉ በአንድነት ጥያቄ የሚሆኑ ናቸው። ከብልጽግና 1ኛ መደበኛ ጉባኤ በኋላ በተዘጋጁ ሕዝባዊ መድረኮች የተረጋገጠው ይሄ ጥሬ ሀቅ ነው። በዚህ ሰዓት ኢትዮጵያውያንን በአሉታም ሆነ በአንድነት የሚያቆማቸው በኢኮኖሚው ላይ በሚመዘገው ስኬት ወይም ውድቀት ነው። ሰንደቅአላማ፣ ሀገር፣ ብሔራዊ ጀግና፣ ታሪክ፣ ወዘተረፈ በ2ኛ ደረጃ የሚገኙ ናቸው። የዚህ ለውጥ አስኳል ኢኮኖሚው ነው። ሌሎች እሱን ተከትለውና በእነሱ ዙሪያ የሚመሠረቱ ናቸው። ሀቀኛና እውነተኛ ብሔራዊ መግባባትና እርቅ ላይ ለመድረስም ኢኮኖሚው ወሳኝ ሚና አለው። ቻይናን ይዞ የተነሳው፤ ሳይነጋገሩ ያግባባው፤ ሳይመካከሩ ያስታረቀው፤ ይቅር ያባባለው፤ አንድነታቸውን በጹኑ መሠረት ላይ ያቆመው፤ በኩራት ቀና ብለው እንዲራመዱ፤ ወዘተረፈ ያደረገው ኢኮኖሚው ነው። ብልጽግናም ሆነ መደመር ኢኮኖሚውን አስኳል ያደረገው፤ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ የቀረጸው ለዚህ ነው። ሆኖም በሙላት፣ በወጥነት፣ በእልህና በቁጭት መገለጥ ላይ ብዙ ስራ ይጠብቀዋል። የዚህ መጣጥፍ ማጠንጠኛ ችግሮቻችንን ሊወክላቸው በሚችል ሌላ አንድ ትልቅ ችግር ለመፍታት መሞከር ነው።

ወደ ለውጥ ኃይሉ ስንመጣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ከፍ ሲልም የፀጥታና የሕግ የበላይነት ችግሮችን በአንድ ላይ ለመፍታት መንቀሳቀሱ ትኩረቱን በታትኖታል። ጊዜውን፣ ጉልበቱን፣ ሀብቱን አባክኖታል። ስለሆነም በኢኮኖሚው (በጆከሩ) ላይ ማተኮር፣ መረባረብ አልቻለም። ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ማለትም የኑሮ ውድነቱ፣ ስራ አጥነቱ፣ ግሽበቱ፣ ከትልቅ መንግስትነት ወደ ትንሽ መንግስትነት ማለትም መንግስት በሒደት ኢኮኖሚውን ለገበያውና ለዜጋው ትቶ እሱ ድንበር፣ የሕግ የበላይነት፣ መልካም አስተዳደር፣ ወዘተ . ሲያተኩር ዜጋው መሰረታዊ ፍላጎቱን አሟልቶ በሂደት ጥሪት፣ ሀብት ሲያፈራ፣ ተስፋ ሲሰንቅ ወዘተ . በሂደት ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ቀውሶችን ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ያቀለዋል። ተስፋ ከሰነቀ፣ ስራ ካለው፣ በኑሮ ውድነትና በዋጋ ግሽበት ካልተማረረ፣ በየሰዓቱ በሚያሻቅብ የሸቀጥ ዋጋ ካልተራቆተ፣ የትርፍ ህዳግ ከተቀመጠለት እንደ አሸዋ ከበዛ ቀማኛ ደላላ ከተላቀቀ፣ ስለሚበላውም ሆነ ለልጆቹ ምሳ ስለመቋጠር ወዘተ . ሀሳብ ጭንቀት ከሌለበት እንዲሁም ከ5/11 ስሌት የተላቀቀ ሲቪል ሰርቫንት መፍጠር ከተቻለ ቁጭ ብሎ በተረጋጋ ሁኔታ ስለሰላም፣ ስለፍቅር፣ ስለእርቅ፣ ስለይቅርታ፣ ስለዴሞክራሲ፣ ስለፖለቲካ ፣ ወዘተ . ቢወራ መደማመጥ መቀባበል ይቻላል። ከዚህ በላይ ኢኮኖሚው በማንነት፣ በዘውግ ፖለቲካ፣ በሴራ ተረክ ተከፋፍሎ የሚገኘውን ዜጋ ድልድይ ሆኖ የማቀራረብ፣ የመገናኘት አቅም አለው።

ኢኮኖሚው ብሔር፣ ማንነት፣ ዘውግ የለውም። የኦሮሞውም፣ የአማራውም፣ የወላይታውም፣ ወዘተ . የጋራ ወኪል፣ የጋራ አካፋይ ነው። የጋራ ችግር ነው። ኢኮኖሚው እንደ ጆከር ዘር፣ ማንነት ሳይለይ ሁሉንም ወክሎ ሊያጫውት ይችላል። የአንድነት ሆነ የንኡስ ብሔር ኃይላትን ሊወክል ይችላል። የሊበራል ዲሞክራቱንም ሆነ ሶሻል ዲሞክራቱን አልያም "አብዮታዊ ዲሞክራቱን" ያለ ልዩነት ይወክላል። ብልጽግናን፣ ኢዜማን፣ አብንን፣ የእነ አቦ ቀጀላን ኦነግ፣ እናትን፣ ወዘተ. ከፍ ሲልም አገርን ሕዝብን ያለ ልዩነት ይወክላል። አዎ! በዚህ ወሳኝ ሰዓት የአገራችንን ዜጎች ለአንድነት፣ ለእርቅ፣ ለመነጋገር፣ ለመቀባበል፣ ለሰላም የሚያቀራርብ ለጊዜው (ታክቲካዊ) እና እጃችን ላይ የቀረን ካርድ ኢኮኖሚውና አኮኖሚው ብቻ ነው። ምንከተለው ፖለቲካዊ ስርዓት በማንነት ላይ የተመሰረተው ፌደራሊዝም ይሁን በግለሰብ መብትና ነፃነት የተዋቀረው ሊበራል ዴሞክራሲ ወይስ ራሱን ሶስተኛ አማራጭ ብሎ የሚጠራ ይሁን ኢኮኖሚው ሁሉን ወክሎ ማጫወት፣ መጫወት ይችላል።

በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራው የለውጥ ኃይል ወደስልጣን ከመምጣቱ ኢኮኖሚውን ወደለየለት ቀውስ ከመግባት የታደገ የማሻሻያ እርምጃዎችን ወስዷል። ከመድህኒት እና ሌሎች መሰረታዊ ሸቀጦች ግዥ ውጭ ከሶስት ወር በላይ የማይዘለውን የውጭ ምንዛሬ መጠባበቂያ በማሳደግ ኢኮኖሚውን ከኮማ ተላቆ ነፍስ እንዲዘራ ተደርጓል። እንደ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ችግር በጥናት በመለየትም ከውድቀት መታደግ ተችሏል። በማስከተልም በርካታ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እየተደረጉ ነው። በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ግብረ ኃይልም ቀጣይ ስራዎችን እያጠና ይገኛል። ይሁንና የኢኮኖሚው ችግር ትላንት የተፈጠረ ሳይሆን የበርካታ አመታት የተዛባ የአመራርና የፖሊሲ ችግሮች ድምር ውጤት ስለሆነ ከተዘፈቀበት መዋቅራዊና ተቋማዊ አረንቋ በቀላሉ ይወጣል ተብሎ አይታሰብም። ስለሆነም አገሪቱ በታሪኳ አይታው የማታውቅ ኢኮኖሚያዊ ችግር ላይ ወድቃለች።

ይሄው መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ችግር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ከመጣው የሕዝብ ብዛት ዕድገት፤ ከአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን፤ ከምርታማነት ባለበት መርገጥ፤ ከንግድ ስርዓቱ መረን የለሽነት፤ ከገበያ ስርዓቱ የተራዘመ ሰንሰለት፤ ከሕገ ወጥ ድለላ ወዘተ. ጋር አብሮ፣ አድሞ ኢኮኖሚውን ፅኑ ታማሚ አድርጎታል። በዚህ የተነሳ የኑሮ ውድነቱ በሰዓታት፣ በቀናት ልዩነት ጣራ እየነካ ነው። የብር የመግዛት አቅም በብርሀን ፍጥነት በሚባል ደረጃ እያሽቆለቆለ ነው። የስራ አጡ ቁጥር እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰ ይገኛል። የእነዚህ ሁሉ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሁሉ ድምር ቅርሻት የሆነ ፖለቲካዊ ቀውስ እንደ ሰኔ ዝናብ መጣሁ መጣሁ እያለ ሰማዩም እያጉረመረመ ነው። እስካሁን እዚህም እዚያም ያስተዋልናቸው ግጭቶች ለአመታት ሲቀነቀን ከኖረው የልዩነት ተረክ በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ቀውሱን ተከትለው የተከሰቱ ማህበራዊ ቀውሶች ለመሆናቸው ሞራ ገላጭ መሆን አይጠይቅም።

የተሳሳተው ፖለቲካዊ አመራር ለኢኮኖሚያዊ ቀውስ ዳርጎናል። ኢኮኖሚያዊ ቀውሱ ማህበራዊ መፍረክረክን አስከትሏል። መላ ካልተበጀለት በዚህ ይቆማል ተብሎ አይጠበቅም። ወደለየለት የፀጥታ፣ የደህንነት ስጋት ሊሸጋገር ይችላል። ይህ ከመሆኑ በፊት ከገጠመን ምስቅልቅል በጊዜ ለመውጣት መስራት አለብን። ከዚህ ለመውጣት ደግሞ ዜጋው፣ መንግስት፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሲቪል ማህበራት ከፖለቲካው ይልቅ ኢኮኖሚው ላይ በአንድነት ሊረባረቡ ይገባል።

**ሁሉም ነገር ወደ ኢኮኖሚው ግንባር!**

**መልካም ትንሳኤ!**

**ረመዳን ከሪም!**

**አሜን።**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ንብ ማነብ - ለሁለገብ የግብርና ልማት

ስምስም መንግሥቱ

ንብ ማነብ ከሰብል ልማትና ከሌሎች የግብርና ሥራዎች መካከል አንዱና የኢኮኖሚ ምንጭ ሆኖ አካባቢያዊና አገራዊ ፋይዳ እንዲኖረው ማድረግ የሚቻልበት ዕድል ሰፊ እንደሆነ ይታወቃል። ኢትዮጵያ ለማር ልማት ምቹ የሆኑና ዕምቅ ሀብቱ የሚገኝባቸው ሰፊ ቦታዎች መኖራቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይሁን እንጂ በትኩረት ባለመሰራቱና የንብ ማነብ ሥራውም ባለመዘመኑ ከማር ልማት እዚህ ግባ የሚባል ኢኮኖሚ ማመንጨት ሳይቻል መቆየቱ ቁጭት ያሳድራል። ሰሞኑን ለማር ልማት ምቹና ዕምቅ የሆነ ሀብት ካለባቸው የኢትዮጵያ ክፍል አንዱ በሆነው ኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ ዞን ተገኝተን እንቅስቃሴውን ለመቃኘት ዕድሉን አግኝተናል። በማር ልማቱ በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ ዞኖች ቡኖ በደሌ፣ኢሉ አባቦራ፣ እና ጅማ ዞኖች ከፍተኛ ድርሻውን እንደሚይዙም በቆይታችን ለመገንዘብ ችለናል። በነዚህ አካባቢዎች የማር ልማቱን ለማሳደግና አመራረቱንም ለማዘመን ይበል የሚባል ጥረት እየተደረገ ይገኛል። አካባቢው ከሰብል ልማት በተጨማሪ በቡና ልማትም የሚታወቅ በመሆኑ ከቡና፣ ከግራዋና ከተለያዩ ዕጽዋቶች ነው የማር ልማቱ የሚከናወነው።እንዲህ በአካባቢ የሚገኝ ፀጋን ጨምሮ በተለያዩ የፅዋት ዝርያዎች በአካባቢው በንብ ማነብ የማር ልማት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች በዘመናዊ የአመራረት ዘዴ ተጠቅመው ከተለያየ ዕጽዋት ያመረቱትን ማር ለሁለት ቀናት በተካሄደ የማር ፌስቲቫልና ባዛር ላይ አቅርበው በማስተዋወቅ የገበያ ትስስር ለመፍጠር አመቻችተዋል። ‹‹በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ›› እንዲሉ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ልማቱን በማሳደግ፣ የገበያ ትስስሩን በማስፋት እንዲህ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ እየተቻለ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በአካባቢው ላይ እሴት የተጨመረበት ምርትም ማቅረብ መቻሉ አንድ እርምጃ እንደሆነም በቆይታችን ለመረዳት ችለናል።


ፎቶ፡- ስምስም መንግሥቱ

በቡኖ በደሌ ዞን በደሌ ከተማ የማር ፌሲቲቫል በተካሄደበት ወቅት፤

በቡኖ በደሌ ዞን በደሌ ከተማ በተካሄደው የማር ፌስቲቫል ባዛርና ኤግዚቢሽን ላይ የማር ምርታቸውን ይዘው የቀረቡት በዘርፉ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው በማስተርካርድ ፋውንዴሽን የሚታገዘው ዓለም አቀፍ የሥነ ነፍሳት ምርምር ማዕከል ሞይሸ ፕሮግራም የተለያየ ድጋፍ ተደርጎላቸው በዘመናዊ የማር አመራረት ዘዴ ውጤታማ የሆኑ ወጣቶችና በግል ጥረታቸው ተምሳሌት (ሞዴል) የሆኑ አርሶአደሮች ናቸው። በንብ ማነብ ተደራጅተው ለውጤት የበቁት እነዚህ ወጣቶች ሞይሽ ላለፉት ሁለት አመታት በንብም ማነብ ላይ የክህሎት ሥልጠና፣ የንብ ዝርያ ማባዛት፣ የማር ቀፎ፣ ማር ሲቆርጡ በንብ እንዳይነደፉ የሚከላከሉበት አልባሳት፣ ማሩን ከሰፈፉ የሚለዩበት መጭመቂያና ማጣሪያ መሳሪያ፣ያጣሩትን ማር አሽገውና የምርት ማስተዋወቂያ ለጥፈው የሚያቀርቡበት ዕቃ በማቅረብ እንዲሁም ማር የሚያቀነባብሩበትን ቤት በመገንባትና የተለያየ ድጋፍ ያደረገላቸው ሲሆን፣ ዞኑ ደግሞ ንቦች የሚቀስሙትን ዕፅዋት ለሚያለሙበት መሬትና ማሩን የሚያቀነባብሩበት ቦታ አመቻችቶላቸዋል። በሞይሽና በዞኑ የጋራ ድጋፍ በማህበር ተደራጅተው በንብ ማነብ የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው ወጣቶች መካከል 60 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው።ባህላዊው ንብ ማነብ ቀፎ በዛፍ ላይ በመስቀል የሚከናወን በመሆኑ ለሴቶች ምቹ አይደለም።በመሆኑም ሴቶች ከንብ ማነብ ሥራ የራቁ ነበሩ። አሁን ላይ ያለው ዘመናዊ የንብ ማነብ ሥራ የልማቱ ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚም አድርጓቸዋል።

ስድስት ሴቶችና አራት ወንዶች ሆነው በማህበር ተደራጅተው በልማቱ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል ወጣት ፎዚያ አብዱርቃድር አንዷ ናት። ‹‹ልማቱ ገቢ ያስገኛል። ሥራውም አይከብድም። ቀደም ባለው ጊዜ ሴቶችን አሳታፊ ባለመሆኑ ሳንጠቀም ቆይተናል። አሁን ግን ሞይሽ ለሴቶች ቅድሚያ በመስጠት በስልጠና ከማብቃት ጀምሮ ላለፉት ሁለት አመታት ድጋፍ አድርጎልን ተጠቃሚ መሆን ችለናል። ድጋፉ ቀጣይነት ስላለው የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርገን ተስፋ እናደርጋለን። ››በማለት ያገኘችውን ጥቅም አስረድታለች። ከማር ልማቱ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ሞይሽ በስልጠና በማብቃት የሙያ ባለቤት እንዳደረጋትም ገልጻለች። እርስዋ እንዳለችው እርስዋን ጨምሮ የማህበሩ አባላት አብዛኞቹ ቤተሰብ በባህላዊ መንገድ ማር ሲቆርጥ እንጂ በንብ ማነብ ላይ ግንዛቤው አልነበራቸውም።በተለይ ደግሞ እሴት ጨምሮ የበለጠ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ክህሎት ያገኙት በሞይሽ ፕሮግራም በተደረገላቸው ድጋፍ ነው። የማር ልማቱ በሁለት መንገድ ይጠቅማቸዋል። አንዱ የተጠራውን ማር አሽገው ለገበያ በማቅረብ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተጣርቶ የቀረውን ሰፈፍ በመሸጥ ይጠቀማሉ። ወጣት ፎዚያ ዘመናዊ የማር ልማት ሥራ በአካባቢው ላይ መጀመሩን ትልቅ ለውጥ እንደሆነ አድርጋ ትወስዳለች። የማር ልማቱ ለማር ቀፎ ለሚያዘጋጅ፣ በማርቆረጣ ወቅት የሚለበስ ልብስ ሰፍቶ ለሚያቀርብ፣ ለተጠራ ማር ማሸጊያም ዕቃ ለሚያቀርብ የሥራ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ የአካባቢው ወጣቶች በተለያየ የሥራ ዘርፍ እንዲሰማሩ ዕድል እንደሚሰጥ ታምናለች። በዚህ መልኩ ተጠናክሮ ከቀጠለ ከአካባቢያቸው አልፈው አገራዊ ኢኮኖሚን በማሳደግ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው ወጣት ፎዚያ ተስፋ አላት። ምርት አምርተው ገበያ መውጣት ከጀመሩ ገና አጭር ጊዜ እንደሆነና የገበያ ትስስሩ እንዲፈጠርላቸው በዞኑ በኩል አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግላቸው ጠይቃለች።

የማር ልማትን ከሰብልና ከሌላ የግብርና ሥራ ጎን ለጎን በማከናወን ውጤታማ መሆን እንደሚቻል በግላቸው ከኢሉ አባቦራ መቱ ዞን ያዩ ወረዳ በማር ፌስቲቫሉ ላይ የተሳተፉት አርሶአደር ታሪኩ ቶለሳ አንዱ ማሳያ ናቸው። ከቡና አበባ ማር ምርታቸውን ይዘው ነው የቀረቡት። ምርታቸው በዋጋም ውድ ነበር። በግላቸው አምርተው በማቅረባቸውና ማሩም የቡና በመሆኑ እንደሆነ ምክንያት አቅርበዋል። አርሶአደር ታሪኩ እንደገለጹልን የማር ልማቱን የሚያከናውኑት በባህላዊ፣ በዘመናዊና የሽግግር ቀፎዎች በመጠቀም ሲሆን፣ በሁሉም አይነት 205 ቀፎዎች አሏቸው። ከቡና አበባ፣ ከግራዋና ከአደይ አበባ ዕፅዋት የሚያመርቱትን ማር ከአካባቢያቸው አልፈው ወደ ተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ገበያ ያቀርባሉ። በአንድ ባዛር ላይ ያገኟቸው የጀርመን ዜጎችም ደንበኛ በማድረግ ገበያ መፍጠር ችለዋል። ጀርመናዊያውያኑ በየአመቱ ኢትዮጵያ ሲመጡ የአርሶአደር ታሪኩን የማር ምርት ይገዛሉ።በስፋት አምርተው ማቅረብ ከቻሉና ሌሎችም አርሶአደሮች ተጨምረው በአገራቸው ጀርመን ገበያ እንደሚያፈላልጉላቸውም ቃል ገብተውላቸዋል። በተለያዩ አካባቢዎች የማር ፌስቲቫልና ባዛር ሲዘጋጅ ምርታቸውን ይዘው በመቅረባቸው ነው ገበያቸውን በማስፋት የገበያ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ የቻሉት።

አርሶአደር ታሪኩ በአመት ሶስት ጊዜ ያመርታሉ።ከዘመናዊ ቀፎ እስከ 250 ኪሎ ግራም፣ ከሽግግር ቀፎ 150 ኪሎ ግራም፣ ከባህላዊ ቀፎም በተመሳሳይ ያመርታሉ። ማር ብቻ ሳይሆን ሰፈፍም በመሸጥ ይጠቀማሉ። የማር ማቀነባበሪያ ማሽንም ገዝተው በማጣራት ነው ለገበያ የሚያቀርቡት። በሚኖሩበት ገጠር ውስጥ መብራት ባለመኖሩ ጀነሬተር በማስገባት የተሻለ ኑሮ ለመኖር ችለዋል። ከተማ ውስጥም ዘመናዊ ቤት ገንብተው ልጆቻቸው እየኖሩበት እንዲማሩ በማድረግ መለወጥ ችለዋል። ኑሯቸውን በገጠር ያደረጉት የማር ልማቱን ጨምሮ የግብርና ሥራቸውን ለማከናወን እንዲረዳቸው ነው።

አርሶአደር ታሪኩ ለሌሎች ተምሳሌት ሊሆኑ እንደሚችሉ ከሥራቸው ለመረዳት ችለናል።የማር ልማቱን የሚያከናውኑት የቀኑን የግብርና ሥራ ከጨረሱ በኋላ ነው። እርሳቸው እንዳሉት ማር ለማልማት ሌላው የግብርና ሥራ እንቅፋት አይሆንም። የማር ልማቱ በመኖሪያ ቤታቸው አቅራቢያ በመሆኑ ምሽት ላይ አስፈላጊውን እንክብካቤ ያደርጋሉ። ‹‹የማር ልማቱ የእርሻ ሥራ እንዳልሰራ አላደረገኝም››ይላሉ። ይህ ጥረታቸው አርሶ አደር ታሪኩን ሞዴል ተሸላሚ አድርጓቸዋል። በክልል፣ በሀገር አቀፍና በዞናቸው በተለያየ ጊዜ የማበረታቻ የሜዳሊያ ሽልማት አግኝተዋል።

እንደአለመታደል ሆኖ እንደ አርሶ አደር ታሪኩ የአካባቢያቸውን ፀጋ ተጠቅመው ሁለገብ ልማት በማከናወን ጠንካራ ገበሬዎች ጥቂት ናቸው። አርሶአደር ታሪኩ እንደነገሩን ያዩ ወረዳ በደን ልማት ትታወቃለች። ለንብ ማነብ የሚሆኑ የተፈጥሮ ዕፅዋቶች አሉ። ሰው የሚጠበቅበት ቀፎና ቦታ ማዘጋጀት ብቻ ነው። ‹‹የአካባቢያችንን ሀብት አልተጠቀምንበትም።ቀን መሥራት እንጂ 24 ሰአት መስራት የሚል ባህል አላዳበርንም›› ሲሉም ይገልጻሉ። እርሳቸው ልማቱን በማሳደግ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን ጠንክረው እንደሚሰሩና ሌሎችንም ለማነሳሳት ጥረት እንደሚያደርጉ ነው የተናገሩት።

በንብ ማነብ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን ወጣቶች በቅርበት የሚያግዙት በዓለም አቀፍ የሥነ ነፍሳት ምርምር ማዕከል (icipe) የሞይሽ ፕሮግራም የኦሮሚያ ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ አቶ ተሾመ ኩመላ እንደገለጹት፤ ድርጅታቸው አካባቢው ላይ ሙያዊና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ወጣቶቹን ተጠቃሚ ለማድረግና ብሎም የማር ልማቱ በአገር ኢኮኖሚ ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማስቻል ከሁለት አመት በፊት እንቅስቃሴ የጀመረው የአካቢውን እምቅ ሀብትና ለንብ ማነብ ሥራ ምቹነቱን በመለየት ነው። ፕሮግራሙ ለአምስት አመት የሚቆይ ሲሆን፣ በቀሪው ሶስት አመታትም አጠናክሮ ይቀጥላል። ፕሮጀክቱ በኦሮሚያ ክልል በአራት ዞኖች በስምንት ወረዳዎች ውስጥ በስፋት በማር ልማት ላይ ድጋፍ በማድረግ ልማቱ እንዲከናወን የሚያደርግ ቢሆንም። ሞይሽ በተጨማሪ ምሥራቅ ሸዋ ላይ በሀር ልማት ላይም በተመሳሳይ የክህሎትና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን በማብቃት የልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። በፕሮግራሙ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ወደ 14ሺ200 ወጣቶችን ተደራሽ ማድረግ ችሏል። የተደረገላቸውን ድጋፍ ተጠቅመው ወደ 188ሺ ኪሎ ግራም ማር አምርተው ለገበያ አቅርበዋል። ፕሮግራሙ በአምስት አመት ቆታው በንብ ማነብና በሀር ልማት አንድ መቶ ሺ ወጣቶችን ለመድረስ ወይንም የሥራ ዕድል ለመፍጠር ነው እየሰራ የሚገኘው።

የዓለምአቀፍ የሥነ ነፍሳት ምርምር ማዕከል (icipe) የሞየሽ ፕሮግራም የኦሮሚያ ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ አቶ ተሾመ ኩመላ እንደገለፁት፣ በክልሉ አራት ዞኖች ሰምንት ወረዳዎች ውስጥ ያለውን ሀብት ማዕከል በማድረግ ፕሮግራሙ ከሁለት አመት በፊት የተጀመረ ሲሆን፣ አምስት አመት የሚቆይ ፕሮግራም ነው። እስካሁን በተከናወነው ሥራ 14ሺ200 ወጣቶች ስልጠና አግኝተው ወደ ልማት ገብተዋል። ከነዚህ ውስጥ 60በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። በተደረገላቸው የቁሳቁስ ድጋፍና ባገኙት ስልጠና በሁለት አመት 188ሺ ኪሎግራም ማር አምርተው ተጠቃሚ ሆነዋል። ንብ በማባዛትም ክህሎት አግኝተዋል። በአጠቃላይ የተጣራና የታሸገ ማር በጥራት በማምረት በአካባቢው ላይ ማሳየት መቻላቸውን ገልጸዋል።

ከአንድ አመት በፊት የኦሮሚያን ምዕራብ ክፍል በማር እናጥለቀልቃለን በሚል ጅማ ከተማ ላይ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚደንት በተገኙበት የይፋ ሥነሥርአት ተካሂዶ እንደነበር ያስታወሱት የቡኖበደሌ ዞን ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳዊት ጅፋር፤ ከይፋ ሥነሥርአቱ በኋላ ዞናቸው የቤት ሥራ በመውሰድ ባደረገው እንቅስቃሴ ወደ29ሺ የንብ ቀፎዎችን በማምረት ለገበሬው በክላስተር በማዳረስ ወደ አራት ሺ ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል። የዞኑን እንቅስቃሴ የሚያግዙ እንደ ዓለምአቀፍ የሥነ ነፍሳት የምርምር ማዕከል ሞይሽ (ፕሮግራሙ) ያሉ ተቋማት የተለያየ እገዛ በማድረግ ላይ መሆናቸውንና ሞየሽ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን ወጣቶች ይዞ እያደረገ ያለው እገዛ ግን ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል። (ፕሮግራሙ) እገዛ ጥራት ያለው ማር እንዲመረት በማድረግ ጭምር በመሆኑ ውጤታማ ሥራ እየተሰራ ይገኛል።

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤ የግብርና ሥራው ሁለገብ እንዲሆንም የማር ልማቱ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል። የገጠሩ ማህበረሰብ መለወጥ የሚችለው በአካባቢው ያለውን ሀብት አሟጦ መጠቀም ሲችል ነው። የዞኑ ግብርና ቢሮውም ይህንኑ በማስገንዘብና አስፈላጊውን ድጋፍም በማድረግ ያለሥራ የባከነውን ጊዜ በማካካስ የአካባቢውን ማህበረሰብም ሆነ ብሎም አገርን ተጠቃሚ ለማድረግ እንቅስቃሴው ተጠናክሮ ይቀጥላል። ሀብቱ በሚገኝበት አካባቢዎች በክልሉ፣ በሞየሽና በግለሰብ አርሶአደሮች ጭምር እየተከናወነ ያለው የንብ ማነብ የማር ልማት የግብርናው ክፍለኢኮኖሚ አንዱ አካል መሆኑንም ያስመሰከረ እንቅስቃሴ በመሆኑ ይበል መልእክታችን ነው።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ትምህርት ቤቶች - የፈጠራ ስራዎች መፍለቂያ

ግርማ መንግሥቴ

እርግጥ ነው ታሪክን ወደ ኋላ፣ በተለይም በጣም ወደ ኋላ ሄድ ብሎ ላገናዘበ ብቸኛው የፈጠራ መፍለቂያ ስፍራ ትምህርት ቤቶችና ዘመናዊ ትምህርት ነው ብሎ መደምደም ያስቸግር ይሆናል። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ዘመናዊ ትምህርት የተጀመረበትና የሰውን ልጅ እስከ ዛሬ ድረስ ይዘውት የዘለቁት ሰው ሰራሽ ቅርሶች፣ መሳሪያዎች ወዘተ የተፈጠሩበት ዘመን የትና የት ልዩነት ስላለው ነው። እንደውም እንደ አንዳንድ ጥናቶች፣ በተለይም አርኪዮሎጂስቶች አካባቢ የተሰሩት እንደሚያሳዩት የሰው ልጅ የተራቀቀው ዛሬ ሳይሆን ያኔ፤ ድሮ ነው። ዛሬማ ያንን እንኳን ደግሞ መስራት አልተቻለም።

እንደ ባለ ሙያዎች ጥናታዊ ድርሳን ከሆነም እራሱ "ሥራ ፈጠራ" የሚለውም፣ ሰማይና ምድር ከተዘረጉበት ጊዜ ጀምሮ ሲሰላ፣ እድሜው ገና ለጋ ሲሆን፣ ከ"ሥራ ፈጠራ (ኢንተርፕረነርሺፕ)" ማሰልጠኛ ማኗል ላይ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው "የሥራ ፈጠራ ጽንሰ ሀሳብ የተጀመረው በ18ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን ከዚያን ጊዜ አንስቶ ይህ ቢዝነስ አስተሳሰብ ሲቀነቀን እስከ አሁን፣ እስካለንበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ደርሷል። ብዙዎች ይህንን ጽንሰ ሃሳብ ከግል ሥራ ፈጠራ (በግል ሥራ መጀመር) ጋር የሚያያይዙት ሲሆን፤ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ደግሞ ከዚህ ባለፈ ተጨማሪ ትርጉም እና ትንታኔ ይሠጡታል።" (ሥራ ፈጠራ ወይም ኢንተርፕረነር "አዲስና የተለየ የቢዝነስ ሃሳብ ወይም ዘዴ ይዞ የተነሣ" የሚል ብያኔን የያዘ መሰረተ ሀሳብ መሆኑንም ልብ ይሏል።)

አሁን አሁን "ለመንደሩ የኤሌክትሪክ ኃይል ያመነጨው ኢትዮጵያዊ ተማሪ" (በደቡብ ኢትዮጵያ ቦረና ዞን፣ በቱላ ድር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ አዳን ሁሴን)፣ "የራሱን አውሮፕላን ለመስራት ያለመው ኢትዮጵያዊው መምህር" (የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ መምህር አማኑኤል ባልቻ)፣ "ተራኪ የተባለ የመጻሕፍት ትረካ መተግበሪያ ፈጠሩ" (ናሆም እና አቤል)፣ "ከባቄላ እና ገብስ ለሕፃናት አልሚ ብስኩት ያዘጋጁት ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች" (የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የ4ተኛ ዓመት የፋርማሲ ተማሪዎችና በአንድ ዶርም ውስጥ የሚኖሩ አራት (ናኦል አዱኛ፣ ኪሩቤል እንግዳወርቅ፣ ሙሴ አብርሃም እና ዮሴፍ ታሪኩ) ተማሪዎች)፣ "በቆሎን ወደ ቢራ የቀየረው የዩኒቨርሲቲ ተማሪ" (በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የ4ኛ ዓመት የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ተማሪ ኤርሚያስ ዋቅሹማ)፣ "በኢትዮጵያ የተሰራ መኪና ለዓለም ገበያ ለማቅረብ የሚታትረው ወጣት" (የዩኒቨርሲቲ ተማሪው ሺሃብ ሱሌይማን)፣ "የአርሶ አደሮችን ሕይወት ለማቅለል ዘመናዊ ጎተራ የሠራችው ወጣት" (ደራርቱ ደረጀ፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የባዮ ሜዲካል ትምህርት ክፍል መምህርት)፣ "በኤሮስፔስ ዘርፍ አሻራዋን ለማሳረፍ እየሰራች ያለችው ኢትዮጵያዊት ወጣት" (ቤተልሄም ግርማ)፤ "በአውሮፕላንና ድሮን ፈጠራ ላይ የተሰማራው ወጣት" (ወጣት ብሩክ በቀለ) እና ሌሎች በርካቶች ለህዝብ የተገለፁበትና ስራዎቻቸውም ለእይታ የቀረቡበት ሁኔታ በስፋት ተስተውሏል። የዚህ ጽሑፍ አላማም ይኸው አይነት የወጣት ተማሪዎች ተሳትፎ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና እራሳቸውና አገራቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ይኖር ዘንድ ግንዛቤን መፍጠር ነው።

ከላይ የጠቀስነው ማሰልጠኛ ማኗል ላይ እንደሰፈረው ከሆነ ከፈጠራ ሥራ አኳያ የመንግስታት ሚና ከፍተኛ ነው። "በርካታ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች በመሰረታዊነት በአንድ ነገር ላይ ይስማማሉ፤ አንድ አገር ምጣኔ ሃብት ለማሳደግ እንዲሁም በርካታ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ሲያስብ ሁነኛው መንገድ የሥራ ፈጠራ ነው። አዳዲስ እና ጀማሪ የሥራ ዘርፎች በሥራ እድል ፈጠራ፣ በገቢ እድገት እንዲሁም በድህነት ቅነሳ በኩል ለአገራት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ መንግስታት ለእነዚህ አዳዲስ የሥራ ዘርፎች ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል።"

እዚህ ላይ "ፈጠራ" የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ስንጠቀምና እሱን ይዘን ዳር ለመድረስ ስንጣጣር መሰረታችን ከሚመለከተው አካል የተገኘው፤ "የአንድ ሰው አእምሮ እንቅስቃሴ ውጤት፣ የምርት እና የጉልበት ብቃትን የሚጨምር መሆኑ የሚታመንበት" የሚለውና "ሥራ ፈጠራ ማለት አዲስ እሴት የመፍጠር ሂደት ሲሆን ስጋትን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ግለሰብ ወይም የሆኑ የግለሰቦች ጥምረት በአግባቡ ያልተፈቱ ችግሮችን አዲስ ነገር በመፍጠር ወይም ባሉ ነገሮች ላይ ማሻሻያ በማድረግ ለገበያው ፍላጎት ምላሽ መስጠት ነው። በዚህ ፍቺ ውስጥ አራት ትልልቅ ሀሳቦችን ማየት እንችላለን። "እሴት መፍጠር"፣ "ስጋትን መቀበል"፣ "አዲስ ነገር መፈጠር" እና "ሂደት" የሚሉት ሲሆኑ፤ ማንኛውም የሥራ ፈጠራ እንቅስቃሴ ከእነዚህ አምዶች አንፃር መቃኘት ይገባዋል።" የሚለው የጽንሰ ሀሳቡ ብያኔ ነው። አንባቢም ጽሑፋችንን ከዚሁ አኳያ እንዲረዳልንና እያወዛገበ (የተገለበጠ ሁሉ ፈጠራ፤ ገልባጩም ፈጣሪ ነው የሚል) ባለው አተያይ እንዳይረዳን ማሳሰብ እንፈልጋለን።

"መንግሥት አዳዲስ አይነት ፖሊሲዎችና አዲስ አይነት ማበረታቻዎችን በመጠቀም የቱሪዝም ዘርፉ እንዲነቃቃ እየሰራ ነው። በዚህ ዘርፍ በጣም በርካታ እድሎችና አማራጮች አሉ" የሚለውን ተከትሎ "በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሥራ የሚፈልጉ ወጣቶች ባሉባት ኢትዮጵያ ተፈላጊነታቸው እየጨመረ ያሉና በርካቶችን ሊያሳትፉ ከሚችሉ የሥራ ዘርፎች" ተብለው በባለሙያዎች ከተዘረዘሩት መካከል የቱሪዝም ዘርፍ፣ የግብርና ዘርፍ፣ የዲጂታልና የአይሲቲ ዘርፍ፣ የማዕድን ዘርፍ፣ የሎጂስቲክስና የንግድ መጋዘን አገልግሎት እና የመሳሰሉት ይገኙበታል። በመሆኑም ወጣቶቻችንም ሆኑ ሥራ ፈጣሪዎች፣ ወይንም የፈጠራ ሰዎች ከወዲሁ በእነዚህ ላይ አተኩረው ቢሰሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ይታወቃልና እነዚህን መስኮች ልብ ማለት ያሻል ማለት ነው።

ፈጠራን ከመማር-ማስተማር ሂደት፣ ወይም ከትምህርት ተቋማት አኳያ ስንመለከት በዋናነት የሚከተሉት የፈጠራ አይነቶች ትኩረት ሲደረግባቸው የምንመለከት ሲሆን፤ እነሱም "ሳይንሳዊ ፈጠራ" (የመጨረሻው ምርት እውቀት ነው)፤ "የቴክኒክ ፈጠራ" (ቴክኒካዊ ወይም የቴክኖሎጂ እድገት ሲሆን፤ የመጨረሻው ምርት ማሽን ወይም ዲዛይን ነው፤ "አርቲስቲክ ፈጠራ" (ለዓለም ውበት መጨነቅ ሆኖ፣ ውበት የመፈለግ ፍላጎትና ተግባር ሲሆን፤ የመጨረሻው ምርቱም የሥነ-ጥበብ (ግጥም፣ ሥዕል፣ ቅርፅ) ነው)፤ እና "የጋራ ፈጠራ" (የሥነ ጥበብ ስራዎች፣ ትርጓሜያቸውን ... ይመለከታል)፤ ስነ-ልቦናዊ ፈጠራ (ዕውቀት የማስተማር ልዩ ስልት ሆኖ፣ ቀዳሚ ዓላማው አዲስ ነገር ማስተማር ነው)።

ትምህርት ሚኒስቴርም "የተማሪዎችን የፈጠራ ውጤቶች በአግባቡ መምራት የሚያስችል ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጀ" በሚል ርእስ በድረ-ገፁ ላይ ባስነበበው ዜና "በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና፣ በጥበብና ሂሳብ ዘርፍ የሚቀርቡትን የተማሪዎችን የፈጠራ ሥራዎች ከዚህ በፊት ከነበረው አሰራር ይበልጥ አጠናክሮ ለማስቀጠል ረቂቅ መመሪያ" አዘጋጅቻለሁ ማለቱ ከላይ ካቀረብነው አንቀፅ ጋር ሲተያይ ተደጋጋፊ እንጂ የተለየ ሆኖ አይገኝም። በተደጋጋሚም "ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል የቀሰሙትን እውቀት ወደ ችግር ፈቺ የፈጠራ ውጤት ለመቀየር በትኩረት መሰራት እንደሚገባ"ው አፅንኦት ሰጥቶ ሲናገር መሰማቱም (መሬት ላይ ያለውን ባናውቅም) ተስፋ ሰጪ ነው።










እነዚህ የፈጠራ አይነቶች ናቸው እንግዲህ ፈጠራን ከትምህርት ተቋማት ጋር አያይዘን እንድናነሳ ያደረጉን። በእነዚሁ ተቋማትም ሲዘወተሩ የሚታዩትም በዋናነት እነዚሁ ናቸው። ለምሳሌ ያህልም የሂሳብና የሳይንስ ትምህርት ፈጠራዎችን በቴክኖሎጂ አሰራር በመደገፍ ለተማሪዎች ፍላጎትና ዝንባሌ አጽንኦት የሚሰጡ መሆናቸው በእኛው አገር ታምኖበት እየተሰራ ይገኛል።

እንደ አገርም "ጀነሬሽን አንሊሚትድ የተሰኘ ድርጅት ከኢትዮጵያ የሥራ ክሂሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፣ አምስት ከተሞችን የሚያሳትፍ የሥራ ፈጠራ ውድድር ሊያካሂድ መሆኑን አስታወቀ። [...] ጥምረቱ በዓለም 1 ነጥብ 8 ቢሊዮን የሚሆኑ ወጣቶች የፈጠራ ሥራዎች የሚያዳብሩበት ክህሎታቸውን በመገንባት፣ ከተለያዩ የሥራ ዕድሎች ጋር በማገናኘት ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ማድረግ ትልቁ ዕቅዱ መሆኑን ሚስ ኢቭ ተናግረዋል። የተለያዩ የንግድ ሥራ ሐሳብ ላላቸው ወጣቶች ከውድድሩ በኋላ ሥራ ማስጀመሪያ የገንዘብ ድጋፍ እስከ 100ሺህ ብር ይሰጣቸዋል።" የተባለውንም ማስታወሱ ተገቢ ሲሆን፤ "ውድድሩ በአለም አቀፍ ደረጃ መሆኑን፣ ከ35 በላይ በሚሆኑ አገሮች እንደሚካሄድ፣ በኢትዮጵያ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ዘላቂ የልማት ግቦችን ስኬታማነት የሚያፋጥኑ ሐሳቦችን ወደ ተግባር መቀየር የሚያስችላቸው ነው።" መባሉንም አለመርሳት ተገቢ ነው። "በኢትዮጵያ አሁን አሁን ወጣቶች የተለያዩ አስደናቂ የፈጠራ ስራዎችን በመስራት ሲያቀርቡ ይታያል። ያም ሆኖ በገንዘብ እጥረት ሳቢያ ብዙዎቹ ወደ ተግባር ሲሸጋገሩ አይታይም።" የሚለውም ቁልፉ ጉዳይና አስቸኳይ መፍትሄን የሚሻ ነው።

ጉዳዩን በተናጠል፣ ማለትም ከተማሪዎችና መምህራን አኳያ መመልከቱ እያልን ያለነውን ምሉእ አያደርገውም። ምሉእ ይሆን ዘንድ ከግለሰብ ፈጣሪዎችም ባለፈ እንደ ተቋም በተቋም ደረጃ የፈጠራ ባለቤት መሆን ይቻላል፤ መፍጠርም እንደዛው። ለዚህ ደግሞ "የደብረ ብርሃን ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የገብስና ስንዴ መውቂያ ማሽን አዘጋጅቶ ያቀረበ ሲሆን፣ ከአካባቢው ተፈጥሯዊ አቀማመጥ አንፃር የአርሶ አደሮችን ጊዜና ጉልበት የሚቆጥብ ነው። መሣሪያውን በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ በማቅረብና አርሶ አደሮች በማሽኑ እንዲገለገሉ በማድረግ ሰፊ ሥራ መሠራት እንዳለበት አዘጋጆቹ ገልጸዋል።" የሚለው የወቅቱ መረጃና ፈጠራው ምን ያህል የአካባቢውን አርሶ አደሮች ችግር እንደፈታ ሲነገር የነበረ መሆኑ ነው። ይህንንና የመሳሰሉትን ስናይ ተስፋ ሰጪ ምልክቶች እየታዩ መሆኑን እንረዳለንና፣ ይህ ወደ ኋላ እንዳይመለስ ጠንክሮ መስራትን ይጠይቃል።

እንደwhat-is-entrepreneurial-ability ማብራሪያ አንድ ጥሩ ሥራ ፈጣሪም ይሁን የፈጠራ ሰው የሚከተሉትን መሆንና ማድረግ እንዳለበት ይመከራል። እነሱም፣ ኃላፊነት የሚሰማው፣ ገለልተኛ፣ ታታሪ፣ በራስ የመተማመን፣ አፍቃሪ ሰው፣ ሥነ ምግባራዊ፤ ጠንካራ ፍላጎት፣ የተረጋጋ ስሜት ባለቤት፣ የአመራር ባሕሪያትን የተላበሰ፤ ደንበኛ-ተኮር፤ ከሰዎች ጋር መግባባት የሚችል፣ ቡድን መምረጥ፣ ሌሎችን ለቡድን ስራ ማነሳሳት፣ የቡድን ሥራን መቆጣጠር (መምራት)፤ ለፈጠራ፣ ለአዳዲስ ሀሳቦች እና ለአቀራረብ ክፍት መሆን፤ የሌሎችን አስተያየት ማዳመጥ፣ ለጉዳዩ ፍላጎቶች፣ ለቡድን ሲባል የራስን ጥቅም መሥዋዕት ለማድረግ ዝግጁ መሆን፤ መተንተን፣ ማቀድ፣ መተንበይ መቻል፤ ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ መኖር፤ እንደ ደንበኛ (ገዢ) ማሰብ መቻል፤ በሕጋዊ ጉዳዮች ላይ እውቀት ያለው ሆኖ መገኘት።

ባጠቃላይ፣ ከላይ በወፍ በረር እንደ ተመለከትነው ፈጠራ ለአለማችን እዚህ መድረስ የአንበሳውን ድርሻ እንደ ተጫወተው ሁሉ ወደ ፊት ስለ መገስገሷም ወሳኙ እሱው ነው። በተለይ ለእንደኛ አይነት አገራት የ"ፈጠራ"ም እንበለው የ"ሥራ ፈጠራ" የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ነውና ፋታ የሚሰጥ አይደለም። በኋላ ቀር አሰራርና እጅ እግር በሌለው ችግር እግር ከወርች ታስሮና ይሄንን ሁሉ ሥራ አጥ ወጣት ይዞ ሥራ ፈጠራን ችላ ማለት የጤና አይደለምና እዳው ገብስ አይደለም። ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር "የኢትዮጵያን የሥራ ዕድል ፈጠራ አጀንዳ መምራት" የሚለውና "እስከ 2022 20 ሚሊዮን የሥራ እድሎች" በማለት ያስቀመጠው ግብ ይሳካ ዘንድም የሁሉም ወገን ርብርብ ያስፈልጋል እንላለን።

# ወቅታዊ

# ‹‹በራስ አገዝ ፕሮጀክቶች ራሳችንን ማቋቋም ካልሞከርን በስተቀር በሠብዓዊ ዕርዳታ ሥም ሰፊ ችግሮች ይከተላሉ››

-አቶ መርሐፅድቅ መኮንን

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዋና የህግ አማካሪ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

በዚህ አምድ በአገራዊ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች የሚዳሰሱበት ነው። በዛሬው አምዳችን ለበርካታ ዓመታት መንግስታዊ የሥራ ኃላፊነትን በአግባቡ ሲወጡ ከቆዩት በጠቅላይ አቃቤ ህግ ማዕረግ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዋና የህግ አማካሪ አቶ መርሐፅድቅ መኮንን ጋር ቆይታ አድርገናል። ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ያለችበት ሁኔታ በህግ ዓይን ቃኝተዋል፤ የመፍትሄ ሐሳቦችንም ሰንዝረዋል፤ እርቀ ሠላም ኮሚሽን በሥራ ስኬታማ እንዲሆን መከወን ስለሚገባቸው ጉዳዮች፣ በክልሎች መካከል የሚስተዋለው መስተጋብር እንዲሁም በቀጣይ አገሪቱ ሰላማዊ ሆና እንድትቀጥል ሊደረጉ ስለሚገቡ ጥንቃቄዎችን ጠቁመዋል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰብዓዊ ዕርዳታ እና የተረጋጋ መንፈስ ለመፍጠር ሲባል ወደ ትግራይ የሚወስዱ መንገዶች መከፈታቸውና የአየር በረራ መፈቀዱን በህግ ዓይን እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** ሲካሄድ የነበረው ጦርነት በህግ ማስከበር ዘመቻው በአብዛኛው የአገር ውስጥ ጦርነት በመሆኑ ከፍተኛ ሰብዓዊ ቀውስ አስከትሏል። ከፍተኛ ንብረት ወድሟል፤ የአገሪቱን ኢኮኖሚ አዳክሟል፤ የህብረተሰቡን ኑሮ አመሰቃቅሏል። በተለይ ደግሞ ጦርነት ይካሄድባቸው የነበረባቸው አካባቢዎች ክፉኛ ተጎድተዋል። ምናልባት ባለበት ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ አገሪቱን ወደ ለየለት ከፍተኛ የመጠፋፋት ሁኔታ ይዞ እንደሚሄድና በማንኛውም ወጪ፤ ኪሳራ እና መሥዕዋትነት ሠላም መረጋጋጥ እንደሚገባ ይታመናል። ይህ እኛ ዜጎቿ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የውስጥ ለውስጥ ጦርነት ለረጅም ጊዜ መቀጠል እንደሌለበት ሲመከርበት የቆየ ነው። አሁንም ቢሆን ስስ የሆነ የግጭት መገታት ቢኖርም ይህም ቢሆን ትንሽ ተስፋ የሚሰጥ ስለሆነ ወደ ሰብዓዊ እርዳታ ማተኮር ይገባል የሚል ነው። በውስጣዊና ውጫዊ ጫና የተነሳ መንግስት ይህን አቋም ወስዷል። ነገር ግን ግን በአሸባሪ ሕወሓትና ፌደራል መንግስት መካከል የተደረገ ሥምምት ነው ለማለት ሁለቱም ተፋላሚ ወገኖች ተደራድረው በጋራ ተኩስ ማቆም አለባቸው። ቀደም ሲል የተናጠል ተኩስ አቁም ስምምነት ወስዶ የነበረው የፌደራል መንግስት ነው።

አሸባሪ ኃይል ግን ይህንን እንደ አጋጣሚ በመቁጠር ለመደራጀት እና ወደ መሐል አገር ገብቶ ከፍተኛ ጥፋት ለማድረስ ምክንያት ሆኗል። ጥቃቱ የደረሰባቸው ኃይሎችና የፌደራል መንግስት በመጨረሻ ወደ መጣበት እንዲመለስ አድርገውታል። ግን ግልጽ መደረግ ያለበት ጦርነት በግልጽ ቆሟል ብሎ አፍ ሞልቶ ለመናገር የሚያስችል ሥምምነት ተደርሷል ማለት አያስችልም። አሸባሪ ኃይሉ ግን በጉዳዩ የተስማማ መስሎ ቀርቧል፤ ተቋርጦ የነበረው ሰብዓዊ እርዳታም በአየርም በየብስም ወትሮ ከነበረው በተሻለ እንዲደርስ እየተደረገ ነው። ግን መታወቅ ያለበት በጦርነቱ የተጎዱ ሰዎችንና አካባቢዎችን ሙሉ ለሙሉ እያዳረሰ ነው ማለት አይቻልም። እነዚህን አካባቢዎችን በማለፍ ወደ ትግራይ እየተጓጓዘ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ዓለም አቀፍ ተቋማት ፕሮፓጋንዳ ብቻ ሳይሆን ዕርዳታ ጭምር ወደ ትግራይ ያደላ እንጂ የአማራና አፋር ክልል ጉዳትን ከግምት አላስገቡም። ይህ ከሞራል እና ከሰብዓዊነት ህግ አኳያ አግባብ ነው?**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው። ይህን ጉዳይ አንስተን ወደ ብያኔ ከመሄዳችን በፊት የትኩረቱ መነሻ ምንድን ነው ብለን ማየት አለብን። ሰፋ ያለው ድምጽ የሚሰማው በአብዛኛው የጦርነቱ መነሻ ትግራይ ነው በሚል በአብዛኛው ትግራይ ክልልን ማዕከል ያደረገ ነው። መላው የትግራይን ክፍል በከፍተኛ ደረጃ የጦርነቱ ገፈት ቀማሽ ነው ብለው እንዲያምኑ ያደረጋቸው ምክንያት አለ። የትግራይ ክልልን ሲመራ የነበረው ሕወሓት ነው። ከዚህም አልፎ በማዕከላዊ መንግስት ላይ ላለፉት ሦስት አስርት ዓመታት ከፍተኛውን ሥልጣን ይዞ ቆይቷል። በዚህ ወቅት ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ወደ ተሳሳተ መንገድ የሚወስዱ ሰፋፊ የውሸት ትርክቶችን በመቅረጽ ራሱን በዲፕሎማሲ ያጎለበተ አንዳንድ ጊዜም በምዕራቡ አለም ላሉ ኃያላን አገራት ራሱን በማስገዛትና በቀጣናው በተለይም በምስራቅ አፍሪካ ራሱን ወኪል በመመስል የአካባቢው ፖሊስ ሆኖ ለመቆየት ሲሠራ እንደነበር ይታወቃል።



ፎቶ፡ ከፋይል

በዓለም አቀፍ ደረጃ በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ የሰገሰጋቸው ኃይሎች አሉ። ይህ እንግዲህ የሰብዓዊ እርዳታ ተሚጋች ድርጅቶችን ጭምር ያካትታል። በዚህ የተነሳ ለዚህ ቡድን ያላቸው ልብ ስስ ነው። በተለይም ደግሞ በአሜሪካ አስተዳደር በተለይም በውጭ ጉዳይ ዲፓርትመንት በቀድሞ አስተዳደር ውስጥ ያሉ እንደ ሱዛን ራይዝ፣ ጃንዳይ የመሳሰሉት የሕወሓትን አይዶሎጂ የሚደግፉ እና በመስክ ድረስ ሄደው ጓደኛ ያደረጓቸው ሰዎች ያሉበት ነው። እንግዲህ ትግራይን ከኢትዮጵያ በራቀ መልኩ እንዲያውቁ እና የሕወሓትን የማጭበርበር ሥራ በከፍተኛ ደረጃ አቅፎ ያቆየ ኃይል ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ከፌደራሉ መንግስት ርቆ ክልሉን ማስተዳደር በጀመረበት እና ‹‹ዲፋክቶ ስቴት›› ለመመስረት ሙከራ አድርጎ በሚመራበት ወቅት የተበዳይነት ስሜትን ይዞ በመቅረብ ጉዳዩን የሚያጮሁለት ብዙ ነበሩ። በዚህም የተነሳ ትኩረት ለማግኘት ችሏል። በአሁኑ ወቅትም ሰብዓዊ ዕርዳታ አማራ እና አፋር ክልልን አልፎ ወደ ትግራይ ክልል እንዲሄድ መደረጉ ይህም ብቻ ሳይሆን አሸባሪው በአማራ እና አፋር ክልል የተወሰኑ ወረዳዎችን ተቆጣጥሮና ኮሪደሩን ዘግቶ ዕርዳታ አመላላሽ ተሽከርካሪዎችን እየወጋ እና እያስቆመ ባለበት ሁኔታ ብሎም ዕርዳታ በአየር ብቻ እንዲሄድለት ሙከራ እያደረገ ባለበት ሁኔታ ይህ ለምን ሆነ ከተባለ ከላይ ያልነው ምክንያት ዋንኛው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ከሞራል፤ ህግ እና ከሰብዓዊነት አኳያ አግባብ ነው?**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** ከህግ አኳያ ሠብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት የሚመራባቸው ዓለም አቀፍ መርሆች አሉ። በዋነኝነት ይህ የአገር ውስጥ ግጭት በመሆኑ የሚፋናቀሉ ወገኖች በሚኖሩበት ወቅት ለእነዚህ ዜጎች ዕርዳታ የሚቀርብበት ሁኔታ አለ። በመጀመሪያ ለመሰል ችግር ቅድሚያ ኃላፊነት የሚወስዱት የአገር ውስጥ መንግስታት ናቸው። ነገር ግን ይህ ማድረግ ካቃታቸው ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድጋፍ መጠየቅና መፈለግ የተለመደና የሚፈቀድ ነው። ይህ እንዴት ይፈቀዳል ከተባለ 1998 ዓ.ም እንደ ዓለም አቀፍ ባህል ህግ ወይንም ልምድ የሚወሰደው የወጣው የውስጥ መፈናቀልን ለማገዝ የወጣ መሪ መርሆች አሉ። በዚህ ውስጥ አንቀፅ 24 ላይ ማናቸውም ዓይነት የሚደረጉ ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ አራት መርሆችን መከተል አለበት ይላል።

የመጀመሪያው ሰብዓዊነት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ዕርዳታ ሲሰጥ ለየትኛውም መወገን የለበትም፤ ወይንም ዕርዳታ አቅራቢው ከየትኛውም ወገን ገለልተኛ መሆን አለበት። ሦስተኛው የዕርዳታ መመዘኛው ፍላጎት ነው። ነገር ግን አዛውንት፤ ሴቶች፤ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እያለ የፍላጎት ቅደም ተከተል ሊኖር ይችላል። አራተኛው ደግሞ አለማዳላት ነው። ይህ ለማንኛውም አካላት ማዳላት የለበትም የሚለውን መርህና ሐሳብ የያዘ ነው። ከዚህም በተጨማሪ መሰል ሰብዓዊ ዕርዳታዎች ለወታደራዊ ድጋፎች እንዳይውሉ ጥንቃቄ መደረግ አለበት የሚል ነው።

በመሰረቱ የራሳችንን እቅድ አውጥተን ተፈናቃዮቻችን ማቋቋም ካልቻልን በመሰል እርዳታ መቀጠል አንችልም። የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አካል ነን። ዓለም አቀፉ ተቋማት ችግራችን ሊጋሩ ይገባል። ዞሮ ዞሮ መሰል ዕርዳታዎችን

# ‹‹በራስ አገዝ ፕሮጀክቶች ራሳችንን ማቋቋም ካልሞከርን በስተቀር በሠብዓዊ ዕርዳታ ሥም ሰፊ ችግሮች ይከተላሉ››

-አቶ መርሐፅድቅ መኮንን

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዋና የህግ አማካሪ



ፎቶ፡ ከፋይል

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

በዚህ አምድ በአገራዊ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች የሚዳሰሱበት ነው። በዛሬው አምዳችን ለበርካታ ዓመታት መንግስታዊ የሥራ ኃላፊነትን በአግባቡ ሲወጡ ከቆዩት በጠቅላይ አቃቤ ህግ ማዕረግ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዋና የህግ አማካሪ አቶ መርሐፅድቅ መኮንን ጋር ቆይታ አድርገናል። ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ያለችበት ሁኔታ በህግ ዓይን ቃኝተዋል፤ የመፍትሄ ሐሳቦችንም ሰንዝረዋል፤ እርቀ ሠላም ኮሚሽን በሥራ ስኬታማ እንዲሆን መከወን ስለሚገባቸው ጉዳዮች፣ በክልሎች መካከል የሚስተዋለው መስተጋብር እንዲሁም በቀጣይ አገሪቱ ሰላማዊ ሆና እንድትቀጥል ሊደረጉ ስለሚገቡ ጥንቃቄዎችን ጠቁመዋል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰብዓዊ ዕርዳታ እና የተረጋጋ መንፈስ ለመፍጠር ሲባል ወደ ትግራይ የሚወስዱ መንገዶች መከፈታቸውና የአየር በረራ መፈቀዱን በህግ ዓይን እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** ሲካሄድ የነበረው ጦርነት በህግ ማስከበር ዘመቻው በአብዛኛው የአገር ውስጥ ጦርነት በመሆኑ ከፍተኛ ሰብዓዊ ቀውስ አስከትሏል። ከፍተኛ ንብረት ወድሟል፤ የአገሪቱን ኢኮኖሚ አዳክሟል፤ የህብረተሰቡን ኑሮ አመሰቃቅሏል። በተለይ ደግሞ ጦርነት ይካሄድባቸው የነበረባቸው አካባቢዎች ክፉኛ ተጎድተዋል። ምናልባት ባለበት ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ አገሪቱን ወደ ለየለት ከፍተኛ የመጠፋፋት ሁኔታ ይዞ እንደሚሄድና በማንኛውም ወጪ፤ ኪሳራ እና መሥዕዋትነት ሠላም መረጋጋጥ እንደሚገባ ይታመናል። ይህ እኛ ዜጎቿ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የውስጥ ለውስጥ ጦርነት ለረጅም ጊዜ መቀጠል እንደሌለበት ሲመከርበት የቆየ ነው። አሁንም ቢሆን ስስ የሆነ የግጭት መገታት ቢኖርም ይህም ቢሆን ትንሽ ተስፋ የሚሰጥ ስለሆነ ወደ ሰብዓዊ እርዳታ ማተኮር ይገባል የሚል ነው። በውስጣዊና ውጫዊ ጫና የተነሳ መንግስት ይህን አቋም ወስዷል። ነገር ግን ግን በአሸባሪ ሕወሓትና ፌደራል መንግስት መካከል የተደረገ ሥምምት ነው ለማለት ሁለቱም ተፋላሚ ወገኖች ተደራድረው በጋራ ተኩስ ማቆም አለባቸው። ቀደም ሲል የተናጠል ተኩስ አቁም ስምምነት ወስዶ የነበረው የፌደራል መንግስት ነው።

አሸባሪ ኃይል ግን ይህንን እንደ አጋጣሚ በመቁጠር ለመደራጀት እና ወደ መሐል አገር ገብቶ ከፍተኛ ጥፋት ለማድረስ ምክንያት ሆኗል። ጥቃቱ የደረሰባቸው ኃይሎችና የፌደራል መንግስት በመጨረሻ ወደ መጣበት እንዲመለስ አድርገውታል። ግን ግልጽ መደረግ ያለበት ጦርነት በግልጽ ቆሟል ብሎ አፍ ሞልቶ ለመናገር የሚያስችል ሥምምነት ተደርሷል ማለት አያስችልም። አሸባሪ ኃይሉ ግን በጉዳዩ የተስማማ መስሎ ቀርቧል፤ ተቋርጦ የነበረው ሰብዓዊ እርዳታም በአየርም በየብስም ወትሮ ከነበረው በተሻለ እንዲደርስ እየተደረገ ነው። ግን መታወቅ ያለበት በጦርነቱ የተጎዱ ሰዎችንና አካባቢዎችን ሙሉ ለሙሉ እያዳረሰ ነው ማለት አይቻልም። እነዚህን አካባቢዎችን በማለፍ ወደ ትግራይ እየተጓጓዘ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ዓለም አቀፍ ተቋማት ፕሮፓጋንዳ ብቻ ሳይሆን ዕርዳታ ጭምር ወደ ትግራይ ያደላ እንጂ የአማራና አፋር ክልል ጉዳትን ከግምት አላስገቡም። ይህ ከሞራል እና ከሰብዓዊነት ህግ አኳያ አግባብ ነው?**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው። ይህን ጉዳይ አንስተን ወደ ብያኔ ከመሄዳችን በፊት የትኩረቱ መነሻ ምንድን ነው ብለን ማየት አለብን። ሰፋ ያለው ድምጽ የሚሰማው በአብዛኛው የጦርነቱ መነሻ ትግራይ ነው በሚል በአብዛኛው ትግራይ ክልልን ማዕከል ያደረገ ነው። መላው የትግራይን ክፍል በከፍተኛ ደረጃ የጦርነቱ ገፈት ቀማሽ ነው ብለው እንዲያምኑ ያደረጋቸው ምክንያት አለ። የትግራይ ክልልን ሲመራ የነበረው ሕወሓት ነው። ከዚህም አልፎ በማዕከላዊ መንግስት ላይ ላለፉት ሦስት አስርት ዓመታት ከፍተኛውን ሥልጣን ይዞ ቆይቷል። በዚህ ወቅት ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ወደ ተሳሳተ መንገድ የሚወስዱ ሰፋፊ የውሸት ትርክቶችን በመቅረጽ ራሱን በዲፕሎማሲ ያጎለበተ አንዳንድ ጊዜም በምዕራቡ አለም ላሉ ኃያላን አገራት ራሱን በማስገዛትና በቀጣናው በተለይም በምስራቅ አፍሪካ ራሱን ወኪል በመመስል የአካባቢው ፖሊስ ሆኖ ለመቆየት ሲሠራ እንደነበር ይታወቃል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ የሰገሰጋቸው ኃይሎች አሉ። ይህ እንግዲህ የሰብዓዊ እርዳታ ተሚጋች ድርጅቶችን ጭምር ያካትታል። በዚህ የተነሳ ለዚህ ቡድን ያላቸው ልብ ስስ ነው። በተለይም ደግሞ በአሜሪካ አስተዳደር በተለይም በውጭ ጉዳይ ዲፓርትመንት በቀድሞ አስተዳደር ውስጥ ያሉ እንደ ሱዛን ራይዝ፣ ጃንዳይ የመሳሰሉት የሕወሓትን አይዶሎጂ የሚደግፉ እና በመስከ ድረስ ሄደው ጓደኛ ያደረጓቸው ሰዎች ያሉበት ነው። እንግዲህ ትግራይን ከኢትዮጵያ በራቀ መልኩ እንዲያውቁ እና የሕወሓትን የማጭበርበር ሥራ በከፍተኛ ደረጃ አቅፎ ያቆየ ኃይል ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ከፌደራሉ መንግስት ርቆ ክልሉን ማስተዳደር በጀመረበት እና ‹‹ዲፋክቶ ስቴት›› ለመመስረት ሙከራ አድርጎ በሚመራበት ወቅት የተበዳይነት ስሜትን ይዞ በመቅረብ ጉዳዩን የሚያጮሁለት ብዙ ነበሩ። በዚህም የተነሳ ትኩረት ለማግኘት ችሏል። በአሁኑ ወቅትም ሰብዓዊ ዕርዳታ አማራ እና አፋር ክልልን አልፎ ወደ ትግራይ ክልል እንዲሄድ መደረጉ ይህም ብቻ ሳይሆን አሸባሪው በአማራ እና አፋር ክልል የተወሰኑ ወረዳዎችን ተቆጣጥሮና ኮሪደሩን ዘግቶ ዕርዳታ አመላላሽ ተሽከርካሪዎችን እየወጋ እና እያስቆመ ባለበት ሁኔታ ብሎም ዕርዳታ በአየር ብቻ እንዲሄድለት ሙከራ እያደረገ ባለበት ሁኔታ ይህ ለምን ሆነ ከተባለ ከላይ ያልነው ምክንያት ዋንኛው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ከሞራል፣ ህግ እና ከሰብዓዊነት አኳያ አግባብ ነው?**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** ከህግ አኳያ ሠብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት የሚመራባቸው ዓለም አቀፍ መርሆች አሉ። በዋነኝነት ይህ የአገር ውስጥ ግጭት በመሆኑ የሚፈናቀሉ ወገኖች በሚኖሩበት ወቅት ለእነዚህ ዜጎች ዕርዳታ የሚቀርብበት ሁኔታ አለ። በመጀመሪያ ለመሰል ችግር ቅድሚያ ኃላፊነት የሚወስዱት የአገር ውስጥ መንግስታት ናቸው። ነገር ግን ይህ ማድረግ ካቃታቸው ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድጋፍ መጠየቅና መፈለግ የተለመደና የሚፈቀድ ነው። ይህ እንዴት ይፈቀዳል ከተባለ 1998 ዓ.ም እንደ ዓለም አቀፍ ባህል ህግ ወይንም ልምድ የሚወሰደው የወጣው የውስጥ መፈናቀልን ለማገዝ የወጣ መሪ መርሆች አሉ። በዚህ ውስጥ አንቀፅ 24 ላይ ማናቸውም ዓይነት የሚደረጉ ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ አራት መርሆችን መከተል አለበት ይላል።

የመጀመሪያው ሰብዓዊነት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ዕርዳታ ሲሰጥ ለየትኛውም መወገን የለበትም፤ ወይንም ዕርዳታ አቅራቢው ከየትኛውም ወገን ገለልተኛ መሆን አለበት። ሦስተኛው የዕርዳታ መመዘኛው ፍላጎት ነው። ነገር ግን አዛውንት፤ ሴቶች፤ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እያለ የፍላጎት ቅደም ተከተል ሊኖር ይችላል። አራተኛው ደግሞ አለማዳላት ነው። ይህ ለማንኛውም አካላት ማዳላት የለበትም የሚለውን መርህና ሐሳብ የያዘ ነው። ከዚህም በተጨማሪ መሰል ሰብዓዊ ዕርዳታዎች ለወታደራዊ ድጋፎች እንዳይውሉ ጥንቃቄ መደረግ አለበት የሚል ነው።

በመሰረቱ የራሳችንን እቅድ አውጥተን ተፈናቃዮቻችን ማቋቋም ካልቻልን በመሰል እርዳታ መቀጠል አንችልም። የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አካል ነን። ዓለም አቀፉ ተቋማት ችግራችን ሊጋሩ ይገባል። ዞሮ ዞሮ መሰል ዕርዳታዎችን

## ሕወሓት ጦርነቱን የጀመረው ለራሱ የገዘፈ ምስል በመስጠት ነው



ለማድረግ ሲገባም አገሪቱን የሚከበሩ ህጎችና ግዴታዎች አሉ፤ አገሪቱን ከሚያስተዳድር መንግስት ጋር በመናበብ ነው።

አሁን የሚታየው ግን ከዚህ በተቃራኒ አይደለም። ጦርነቱ ትግራይ ተጀምሮ በትግራይ ላይ አልተጠናቀቀም። አሸባሪው ኃይል እስከ ሰሜን ሸዋ ድረስ መጥቶ መሰረተ ልማቶችን አውድሟል፤ የግለሰብ ቤቶችና ንብረቶች ወድመዋል፤ ተዘርፈዋል፤ ሴቶችና ህፃናት በከፍተኛ ደረጃ ተጎሳቅለዋል፤ ተደፍረዋል። በአማራ እና አፋር ክልል ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊ ቀውስ ተከስቷል። ከሞተው እና ከቆሰለው በተጨማሪ በርካቶች ከቀያቸው ተፈናቅለው በመጠለያ ውስጥ ናቸው። አንዳንዶች ደግሞ በባዶ ሜዳ ላይ ናቸው።

ለአብነት ዋግኽምራ አካባቢ ያለውን ማየት ይቻላል። የዓለም አቀፍ ተቋማት ማገዝ ነበረባቸው። ግን በየብስና በአየር በቂ በረራ የተፈቀው እርዳታ ይግባ የሚለውና ዓለም አቀፉ ተቋማት ጩኸታቸው ወደ ትግራይ ብቻ ያደላ ነው። ይህ ሁሉ ጫና መንግስት መሥራት ከሚገባው በላይ እንዲሰራ ጫና ውስጥ ወድቋል። ይህ ዓለም አቀፍ መርህን የሚጣረስ ነው።

በመርህ 25 ላይ እንደተቀመጠው ማንኛውም ሰብዓዊ ዕርዳታ ለጦርነት ዓላማ አለመዋሉን ማረጋገጥ አለበት የሚለው ተጥሷል። ወደ ትግራይ ክልል የሚጫኑ ሰብዓዊ ዕርዳታዎች ለህዝብ በትክክል መድረሳቸው አጠራጣሪ ነው። ትግራይ ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን ናቸው ሰብዓዊ እርዳታ ቢደርስ የሚከፋው ያለ አይመስለኝም። መከተል የሚገባቸውን መርሆች መከበር አለባቸው። ሰብዓዊ ዕርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች መድሃኒቶችና ሌሎች ሰብዓዊ ቁሶች ለጦርነት ዓላማ እየዋሉ በቀጥታም ለሕወሓት ዓላማ ማስፈፀሚያ መሆናቸው ተረጋግጧል።

ለአብነትም የዓለም ምግብ ድርጅት የጫኑ በርካታ ተሽከርካሪዎችም ሳይመለሱ ቀርተዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳያው ሰብዓዊ ዕርዳታ ሰብዓዊነት፤ አለማዳላት፣ ገለልተኝትን የሚሉ ዓለም አቀፍ መርሆችን የተቃረነ ነው። ዓለም አቀፍ ተቋማት በተለይም ደግሞ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዩማን ራይትስ ዎች የሚባሉትም የትግራይ ወራሪ ኃይሎች በአፋር እና አማራ ክልል ሴቶችን ሲደፍሩ፣ ትምህርት ቤቶችን ሲያቃጥሉ፣ ንብረት ሲያወድሙ፣ ህዝብ ሲያሰቃዩ፣ ህፃናትን ሲገድሉ፤ ተቋማትን በከፍተኛ ደረጃ ሲዘርፉ፣ በቡድኑ የደረሱ ከፍተኛ ሰብዓዊ ጥሰቶችን አስመልክተው መግለጫ ሲያወጡ ነበር። ነገር ግን በየጊዜው አቋማቸውን ሲቀያይሩ ነበር። በሰብዓዊነትም ሆነ በሰብዓዊ መብቶች የሚወሰዱት አቋም አስተማማኝ አይደለም። በመሆኑም በራስ አገዝ ፕሮጀክቶች ራሳችንን ማቋቋም ካልሞከርን በስተቀር በሠብዓዊ ዕርዳታ ሥም ሰፊ ችግሮች ይከተላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት ቀደም ሲል የተናጠል ተኩስ አቁም ሥምምነት አድርጎ ከትግራይ ክልል ሲወጣ ወራሪ ቡድኑ ራሱን በማደራጀት አማራ እና አፋር ክልልን መልሶ ወሯል። አሁንም የፌደራል መንግስት ከአንድ ወገን ብቻ ኃላፊነት መወሰዱ ችግር አያመጣም?**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** ጥያቄዎቹና ስጋቶቹ ትክክል ናቸው። መንግስት መሰል የተናጠል ዕርምጃ ሲወስድ በዘፈቀደ የሚወስድ አይመስለኝም። በመሰረቱ የመጀመሪያው የተናጠል ተኩስ ማቆም ሥምምነት ሲባል አይገባኝም። ሥምምነት የሁለት ወገኖች ድርድር የሚደረስበት ውል መሆኑን አምናለሁ። ይህ መባል ያለበት የተናጠል ተኩስ ማቆም እርምጃ ነው። መንግስት መሰል እርምጃዎችን የሚወስደው ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ቅድመ ሁኔታዎችን በመገምገም ነው። ምናልባት የፌደራል መንግስት ተቻኩሎ የወሰደው እርምጃ ነው የሚሉ አሉ። ግን ይህ በጥንቃቄ መታየት አለበት።

ጦርነቱ ረጅም ጊዜ ወስዷል። ማወቅ ያለብን ሕወሓት ጦርነቱን የጀመረው ለራሱ የገዘፈ ምስል በመስጠት ነው። መንግስት ጊዜ ሲሰጥ አሸባሪ ቡድን መልሶ ተደራጀ የሚለው አንደኛው ምክንያት ሊሆን ይችላል። መንግስት ግን የወሰደው እርምጃ በተጠና መንገድ እንደሆነ ዘርዘር ያለ ምክንያት ሊሰጥ ይችላል። መታወቅ ያለበት ትግራይ ክልል ያለውም ህዝብ የእኛው ህዝብ ነው። አሁንም የትግራይ ህዝብ ከሕወሓት አመራር ጋር ያለውን ሁኔታ ግንኙነት ለማወቅም ይረዳዋል የሚል እሳቤም ያግዛል። ነገር ግን መጨረሻ ላይ የታየው ይህ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- ሰብዓዊ ዕርዳታ ሥም በአየርና በየብስ በገፍ እርዳታ ሲገባ አሸባሪውን ቡድን ስማገዝ የሚውሉ ቁሳዊና የሰነድ ድጋፎች የማድረግ ዕድል አይሰፋም?**

**አቶ መርሐጽቅ፡-** ውስጥ ለውስጥ የሚካሄድ ጦርነት በጣም አስቸጋሪ ነው። በሁለት አገራት መካከል ቢሆን ከፍተኛ የሆነ የጎራ መደበላለቅ ይቀንሳል። ውስጣዊ ጦርነት ሚዛኑን ለመረዳት አስቸጋሪ ሁኔታዎች የመፈጠር ዕድል አላቸው። በጦርነት በመሬት ላይ ኃይል ሲገኝ በዲፕሎማሲውም ከፍተኛ የሆነ ዕድል ይገኛል። አሸባሪ ሕወሓት መሰሪ ነው። ሰላማዊ ድርድርና ውይይት እንዲህ በቀላሉ አይገባውም። ሕወሓት መሰሪ ድርጅት በመሆኑ በስልጣን ዘመኑ ቀብሮ ያቆያቸውን መሳሪያዎችንም ሲጠቀም ነበር። ለህዝብ የሚሰጥ ሰብዓዊ ድጋፍ እንኳ ሳይቀር የሕወሓት ታጣቂዎች ዘርፈው ሲጠቀሙ ነበር። ነገር ግን የፌደራል መንግስት የወሰደው የተኩስ አቁም እርምጃው የትግራይ ህዝብን ያሉበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚሆን ነው።

በእርግጥ አሸባሪው ሕወሓት ከሰሜን ሸዋ የተመለስኩት ፈልጌና አፈግፍጌ እንጂ ተሸንፌ አይደለም ሲል ይዋሻል። ዞሮ ዞሮ ግን የሕወሓት መሰሪነት ገና ብዙ መከራ ያመጣብናል። ከዚህ የምንማረው ነገር አለ። የጥምር ኃይሉ ሆነ የፌደራል መንግስት ከፍተኛ መሥዕዋትነት ከፍለዋል ለ17 ወራት የተካሄደ ጦርነት ነው። እስካሁን የደረሰውን ውድመት እንኳ ታሳቢ አድርገን ከአሁን በኋላ በእያንዳንዱ ሂደት የምንወስደው እርምጃ የከፋ ኪሳራ እንዳንከፍል ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ያስተምረናል። ነገር ግን ምን ትርፍ ተገኘ ምንስ ጉዳት አስከተለ የሚለውን ግን በጥልቅ ጥናት የሚመለስ ነው። የሚወሰደው እርምጃ በብሄራዊ ሉዓላዊነት ጋር የተያያዘ መሆኑን ማሰብ አስፈላጊ ነው። ይህ ውስጣዊ ጦርነት በመሆኑም የተወሳሰበ በመሆኑ እያንዳንዱ የሚወሰደው እርምጃ ጥንቃቄ ይፈልጋል።

አሸባሪ ሕወሓትም ጦርነቱን ብቻውን የተዋጋው ሳይሆን ከውስጥና ከውጭ የሚደገፍ ነው። ሸኔ፣ ጉሙዝ ታጣቂ ቡድኖችንና የመሳሰሉትም በየፊናቸው የሚያግዙት ቡድን ነው። የፌደራል መንግስት የተወሰደው የተኩስ ማቆም እርምጃ መልካም ቢሆንም ከሕወሓት መሰሪ ባህሪ አኳያ ወደ ሠላም ይመጣል ወይ የሚለውን በሚገባ ማጤን ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ አሸባሪው ሕወሓት አዕምሮ የሚገዛ ከሆነ እና ወደ ሠላም ከመጣ ህዝቡን ለሌላ ቀውስ እንዳይዳረግ ያግዛል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ጉዳይ በቀጣናው ላይም ትልቅ ትርጉም ያለው በመሆኑ ተጨማሪ ችግር ሳይኖር ችግሩን እንዴት ማቆም ይቻላል የሚሉ ኃይሎችም ተበራክተዋል። ጫናው ደግሞ የሚበዛው ፌደራል መንግስት ላይ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ጫናው የኢትዮጵያን ሠላም የማፈይልጉ እና በትርምስ ውስጥ እንድትኖር በሚፈልጉ ብሎም የቀጣናው ሠላም የሚጠቅማቸው ወዳጅ አገራት ጭምርም የሚሳተፉበት መሆኑንም ማጤን ያስፈልጋል። ከመሃል አገር ተነስተውም አሸባሪን ቡድን የሚደግፉ አሉ። ጦርነቱ ካልቆመ መተላለቁ ይቀጥላል። ሌላው ይህን ቡድን የሚያግዙ አካላትን በጥናት ላይ ተመስርቶ ዕርምጃ መውሰድ እና ከጨዋታው ውጭ ማድረግም ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- አገር በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ ሆና ሰሞኑን አማራና ኦሮሚያ ክልል ብልጽግናዎች የሚያወጡት መግለጫ አግባብ ነውን? እንደአገራዊና በአንድ ርዕዮተ ዓለም ለሚመራ ፓርቲስ ይህ አካሄድ አደጋ የለውም?**

**አቶ መርሐፅድቅ መኮንን፡-** እውነት ለመናገር አገር ከሚመራ አንድ የተደራጀ ፓርቲ አይጠበቅም። ብልፅግና ፓርቲ ከተባለ በኋላ የራሳቸው ምክንያት ሊኖር ይችላል ካዛ በኋላ የብልፅግና ፓርቲ አንድ ፓርቲ ከሆነ በየመንደሩስ ሲደርስ የሆነ ብሄር ጠርተህ መልሰህ ብልፅግና የምትልበት ምክንያት ሊኖር አይችልም። የብልፅግና ፓርቲ የአማራ፣ የሶማሌ፣ የኦሮሚያ ቅርንጫፍ እያልክ የአገሪቱን የቆዳ ስፋት ተከትለህ የፓርቲውን መዋቅር ልታስፋፋ ትችላለህ። ይህን ማድረግ ሲገባ መልሶ ያንኑ ብሄር ወለድ የነበሩትን ተቋማት ፓርቲዎች ምንም እንኳን ህጋዊ ሰውነት የላቸውም ቢባልም አሁንም ህጋዊ ሰውነት ያላቸው በሚያስመስል መንገድ ነው ሲንቀሳቀሱ የምናያቸው። ይህ የመጀመሪያው ችግር ይመስለኛል።

ከዚህ ባሻገር ደግሞ ቢያንስ መሪዎች ናቸው። በተለያየ ደረጃ ኦሮሚያን የሚመሩትም ሆነ አማራን የሚመሩት ትልቅ ህዝብ እንመራለን ብለው በምርጫ ተወዳድረው አሸንፋችኋል ተብለው በቦርድ ተመስክሮላቸው መንግስታዊ ስልጣን የያዙና እንደፖሊት ቢሮ በጋራ አገር ለመምራት የሚገናኙ ኃይሎች ናቸው። ወደየመንደራቸው ሲመለሱ አንዷትን መንደር ወስደው ለምሳሌ ምንጃር ሸንኮራ ውስጥ ነው ያለችው ወይስ ፈንታሌ ናት የተባለችው መንደር አንደኛው አሞራ ቤት ናት ሲል ሌላኛው ቆርኬ ናት ይላል። ቦታዋ የተለያየ ሥም ሊኖራት ይችላል።

የብሄር ፖለቲካ እጅግ በጦዘበት በዚህ ወቅት ጠላቶች ከሚያጦዙት በላይ እርስበርስ በብሄር በመፋከት በትንሽ መሬት ይህ የኔ ነው ያ ደግሞ ያንተ ነው የሚለው አካሄድ ብዙ ለውጥ አያመጣም። ይህ ብቻ አይደለም በጣም ብዙ መታረም ያለብን ጉዳዮችም አሉ። በኢፌዴሪ ህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የከተማም ሆነ የገጠር መሬት በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ሀብትና ንብረት እንደመሆኑ አይሸጥም አይለወጥም። ይህ ማለት መሬት የሁሉም ነው ማለት ነው።

ህገመንግስቱ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም ከነችግሩ መሬትና የተፈጥሮ ሃብቶችን የመላው ኢትዮጵያውያን ሃብት ነው የሚያደርገው። ኃላፊነት የሚገባቸው አካላት ይህን ጠንቅቀው የሚያውቁ ቢሆን ኖሮ የሰሞኑ ክስተት ባልተፈጠረ ነበር። ከዚህ አንፃር ሁለቱም ፓርቲዎች በይፋ ወጥተው ይቅርታ ማለት አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- መሰል ችግሮችን ጨምሮ የእርቀ ሠላም ኮሚሽኑ በአገሪቱ የሚታዩ ግጭቶችን የማስቆምና የኢትዮጵያን ችግሮች የማቃለል ዕድሉ ምን ያህል ነው?**

**አቶ መርሐፅድቅ መኮንን፡-** ይህ የፖለቲካ ፈቃደኝነት ጉዳይ ነው። ከዚህ በላይ ሌላ እድል ያለን አይመስለኝም። ወደውጪ እንኳን ብናንጋጥጥ እከሌ ይደግፈናል ወይም እነዚህ ግጭቶች ይዘን እንደአገርና መንግስት ለመቀጠል የሚያስችለን እድል ከባህር ማዶ ይመጣል ለማለት የሚያስችል አይደለም። ስለዚህ እኛ በመጋጨታችን በከፍተኛ ደረጃ እንጎዳለን እንጂ የሚያዳምጠን እንኳን የለም። ትልልቆቹ ግጭቶች በመጡ ቁጥር ከነጭራሹ ከታሪክ ገፅም ልንዘነጋ እንችላለን።

ያልፀዳ ብዙ ነገር አለ። በርካታ የፖለቲካ ቡድኖችም አሁን እየተካሄደ ያለውን ጥረትና አገራዊ ምክክሩን በሥራ ላይ ለማዋል እየተደረገ ያለው ጥረት ግልፅነት የለውም፤ የስልጣን ማስቀጠያ ነው መንግስት የራሱን ፕሮጀክት ነው እየሰራብን ያለው ብለው የሚያምኑ አሉ። ከዚህ አኳያ ምክንያታቸውን በደምብ ማዳመጥና ይህ ለምን እንደሆነና እንዳልሆነ ማየት ይገባል። በሠላማዊ መንገድ ማነጋገር፣ መወያየት መግባባትና ልዩነቶችን ማጥበብ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር ሰላማዊ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ምን መሰራት አለበት?**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** ተፈናቃይ እና ዕርዳታ ፈላጊ ዜጎቻችን ወደ 20 ሚሊዮን ደርሰዋል። ይህን ማቆምና መፍትሄ ማፈላለግ ይገባል። ይህን እንደ አገር የገጠመንን ችግር መፍታት አለብን። የሽግግር ፍትህ ያስፈልጋል። አገራዊ ምክክሩ ላይ በርካቶች የተለያየ እሳቤ አላቸው። አገሪቱ አሁን ባለችበት ሁኔታ ከውጭ ማምጣት አንችልም። ትክክለኛው መፍትሄ መመካከር ነው። ጦርነቱን አብርዶ ለዘላቂ ሠላም መነጋገር ብቻ ሳይሆን የጦርነቱ ሰላባ የሆኑ ተጎጂዎች እውቅና መስጠትና ካሳ መስጠት ተገቢ ነው። ተጠያቂዎችም በዓደባባይ መለየት አለባቸው። ብሄራዊ ምክክር ውስጥ ጎልቶ ያልወጣው ይህ የሽግግር ፍትህ ነው። በዚህ ከታገዘ የአገሪቱ ችግሮች ሊፈቱ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ። ለጦርነቱ መቀስቀስ ምክንያት የሆኑ ዋና ዋና አካላት የሚጠየቁበትም ሥርዓት መኖር አለበት። ይህ ሳይሆን የይስሙላ ዕርቅ መካሄድ አለበት ከተባለ አጥጋቢ አይሆንም።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ሳደረጉት ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ መርሐፅድቅ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ



## በአፍጋኒስታን መስጊድ ውስጥ በተፈጸመ ጥቃት 33 ሰዎች ተገደሉ

በአፍጋኒስታን ኩንዱዝ በተሰኘችው ከተማ በሚገኝ የሱኒ መስጊድ ላይ በተሰነዘረ የቦንብ ጥቃት 33 ሰዎች ሲገደሉ ህጻናትን ጨምሮ 43 ሰዎች ላይ ደግሞ ጉዳት እንደደረሰ ባለስልጣናት አስታወቁ።

ጥቃቱ በከተማዋ ምሥራቃዊ ከተማ የሱፊ መስጊድ ላይ ሲፈጸም ለሁለተኛ ጊዜ ነው። ከዚህ ጥቃት አንድ ቀን ቀደም ብሎ በአፍጋኒስታን አራት የተለያዩ ከተሞች ላይ ጥቃት የተፈጸመ ሲሆን ለሁሉም ጥቃት አይኤስ ኃላፊነቱን ወስዷል።

የታሊባን አስተዳደር እስላማዊ ታጣቂውን አይኤስ ቢያሸንፈውም፤ ቡድኑ ለአፍጋኒስታን አዲስ መሪዎች ትልቅ የደህንነት ፈተና እንደሆነ አስታውቋል።

ትናንት በጁመአ ጸሎት ላይ በኩንዱዝ የተፈጸመውን ጥቃት ፈጽሜያለሁ ብሎ ኃላፊነት የወሰደ ቡድን እስካሁን አልተገኘም።

በመስጊዱ አቅራቢያ የሚሰራ አንድ ነጋዴ ክስተቱ እጅግ አሰቃቂ እንደነበር ለኤፍፒ የዜና ወኪል ተናግሯል።

ለጥቃቱ ጥቅም ላይ የዋለው ቦንብ እና ፍንዳታው ሐሙስ ዕለት በማዛሪ ሻሪፍ በሺያ ሙስሊም መስጊድ ላይ ከተፈጸመው እና ቢያንስ 31 ሰዎች ከሞቱበት እና 87 ሰዎች ከተጎዱበት ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።



## ቻይና የአውሮፓ ኅብረት እና አሜሪካ በሉዓላዊነት እና በግዛት አንድነት ላይ ያሳቸውን ያልጠራ አቋም ወቀሰች

ቻይና በሉዓላዊነት እና በግዛት አንድነት ላይ እንደ ሁኔታው የሚቀያየረውን የአሜሪካ እና የአውሮፓ ኅብረት አቋም አጥብቃ ተቃወመች፡፡

ቻይና ተቃውሞ ያሰማችው ሁለቱ አካላት በጉዳዮቹ ላይ በጋራ የሰጡትን ጋዜጣዊ መግለጫ ተከትሎ ነው፡፡

ስማቸው ያልተገለጸ አንድ በአውሮፓ ኅብረት የቻይና ተልዕኮ ቃል አቀባይ እንደተናገሩት፤ " አሜሪካ እና የአውሮፓ ኅብረት በጥምረት የሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ የሚያሳየው ሀገራቱ እና በውስጣቸው የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ድርጅቶች ጭምር ለሌሎች ሀገራት ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ግድ እንደሌላቸው ነው፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫው የቀረቡት ሃሳቦች የሚያመላክቱት፤ ሀገራቱ ያልተጠና ጭፍን ፖለቲካ እና ማስፈራራት እንደተያያዙ የሚያሳይ ነው ሲሉም ቃል አቀባዩ ኮንነዋል፡፡

ባሳለፍነው ሐሙስ እና አርብ የአሜሪካ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዌንዲ ሼርማን በቤልጂየም ተገኝተው የአውሮፓ የውጭ ጉዳይ ዋና ፀሃፊ ስቴፋኖ ሳኒኖን ማነጋገራቸው ተመላክቷል።

ሁለቱ ወገኖች በሰብዓዊ መብት አያያዝ እና ቻይና በዩክሬን ላይ ያላት አቋም እንዳሳሰባቸው በመግለጫቸው ማመላከታቸውን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል፡፡

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የ2013 የብሄራዊ ፈተና ሂደቶችና ውሳኔዎች

ትምህርት ሚኒስቴር ከክልልና ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ጋር በመወያየት በ2013 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ፈተና እርማት እና ውጤት ላይ ባስተላለፈ ውሳኔ መሠረት፤ በጦርነትና ግጭት ውስጥ ሆነው የ2013 ብሄራዊ ፈተና የተፈተኑና የማለፊያ ነጥብ ያላመጡ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከ2014 ዓ.ም መደበኛ ተፈታኞች ጋር እንዲፈተኑ መወሰኑ ይታወቃል። የውሳኔውን አጠቃላይ መግለጫ በተመለከተ ክፍል አንድን ማቅረባችን የሚታወስ ሲሆን፣ የመጨረሻው ክፍል በዚህ መልኩ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፤ መልካም ንባብ።

መንግሥት ባሉት መደበኛ ዩኒቨርሲቲዎች ማስተናገድ የሚችለውን ያህል ተማሪዎች ነጻ ሊባል የሚችል ስኮላርሽፕ ይሰጣል። ይህ የሚወሰነው በዋናነት በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የማስተናገድ አቅም ሲሆን፣ የተወሰነ ጭማሪ ማሳየቱንም ሚኒስቴሩ በመግለጫው ይፋ አድጓል። የተመዘገበው ጭማሪ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲ መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ተወስኖ ከተፈተኑት አምስት መቶ 98 ሺ ስድስት መቶ 79 ተማሪዎች ውስጥ በመንግሥት ዩኒቨርሲቲ ቅበላ የሚያገኙት 25 በመቶ ገደማ ናቸው።

መጋቢት 5 ቀን 2014 ዓ.ም የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ቅበላ አቅምና ምደባ ለማግኘት መመዝገብ ያለበትን ነጥብ አስመልክቶ ውሳኔና መግለጫ ከተሰጠ ቀን በኋላ የተለያዩ አካላት ከመቁረጫ ነጥብና አጠቃላይ ከፈተና እርማትና ውጤት ማሳወቅ ተያይዞ ባሉ ጉዳዮች ላይ ጥያቄ በማንሳታቸው የማወያየት እና ተጨማሪ መግለጫ የመስጠት እንዲሁም ጉዳዮችን ይበልጥ መረዳትና መገንዘብ ለፈለጉ አካላት ማብራሪያ ሲሰጥ መቆየቱን ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

በተሠራው ሥራም ተፈጥረው የነበሩ ብዥታዎችንና ቅሬታዎችን በተመለከተ በመጨረሻ የተደረሰበት፡-

- የፈተና እርማት በተመለከተ ያጋጠመ ችግር አለመኖር፣
- ውጤት ማሳወቅን በተመለከተ በሁለት ዙር ፈተና በመሰጠቱ አጋጥሞ የነበረው ችግር መታረሙ፣
- በመጀመሪያው ዙር ተፈታኞች በሥነ ዜጋ ትምህርት ካጋጠመው በስተቀር ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ውጤት ውድቅ ለማድረግ አሳማኝ የውጤት ትንተና አለመኖሩ እና
- በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ቅበላ የሚያገኙትን በተመለከተ በቀደሙት ዓመታት ከመሰናዶ ትምህርት በኋላ ከሚፈተኑት ጋር በማነጻጸር የተፈጠረ መረዳት አለመኖሩ ዋና ዋና ናቸው።

ይህ እንዳለ ሆኖ በአብዛኞቹ ክልሎች ያጋጠመው የውጤት መቀነስ ቢኖርም በጦርነትና በፀጥታ መጓደል ምክንያት አንዳንድ አካባቢዎች በተለየ ሁኔታ በተለይም አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ላይ በልዩነት ማየት የሚቻልበት እድል ካለ ቢታይ የሚሉ አስተያየቶች ቀርበው ትምህርት ሚኒስቴር አማራጮች እንዲቀርብ ስምምነት ተደርሶ አማራጮችን የማየት ሥራ ተሰርቷል።

ትምህርት ሚኒስቴርም በሥራ ላይ ያሉ 43 ዩኒቨርሲቲዎች ይህን ችግር ለመፍታት የመጨረሻ አቅማቸውን አሟጠው በመጠቀምና ትግራይ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች መጥተው በጊዜያዊነት ከተመደቡበት ውስጥ በቅርቡ ጨርሰው የሚመረቁትን ታሳቢ በማድረግ ተጨማሪ የቅበላ አቅም ማግኘት ተችሏል።

በተጨማሪም አራቱም ክልሎች አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ በፈተና ወቅት ተማሪዎች ‹በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ተፈትነዋል› ብለው የሚያስቧቸውን ዞኖች ወይም ወረዳዎች፣ ትምህርት ቤቶች እና የተፈተኑትን ተማሪዎች ለይተው እንዲያሳውቁ ተደርጓል።

በመሆኑም የሚመለከታቸውን በማሳተፍና በማማከር የሚከተሉትን ሁለት ውሳኔዎች በሁሉም ክልሎች ስምምነት በጋራ የተወሰነ ሲሆን፣ አንደኛው የተገኘው ተጨማሪ የቅበላ አቅም በፍትሃዊነት ለአራቱም ክልሎች በጦርነቱ ምክንያት በተጎዱ ተፈታኞች መጠን ማከፋፈል ነው። ሁለተኛ ውሳኔ በጦርነት ግጭት ውስጥ ሆነው ተፈትነዋል ተብሎ በተላኩት አካባቢዎች ውስጥ የተፈተኑትና በዚህ ዓመት የማለፊያና ወደ መንግሥት ዩኒቨርሲቲ መግባት ያልቻሉት ተማሪዎች በ2014 ዓ.ም በሚሰጠው የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና መደበኛ ተማሪ ሆነው መፈተን እንዲችሉ የሚሉ ናቸው።

በተያያዘም የ12ኛ ክፍል ፈተና ውጤትን በተመለከተ ከእንግዲህ ወዲያ ላለፉት ተከታታይ ዓመታት የተደረሰበትን የፈተና አስተዳደር ተዓማኒነት ጉድለቶችን ከትምህርት ማህበረሰቡ ጋር በመተባበር መፍትሄ በማስቀመጥ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረትና እውቀት ልክ ተወዳድረው የሚያልፉበትን ሥርዓት በማረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ሚኒስቴሩ አሳስቧል።

የፈተና አስተዳደር ተዓማኒነት እንዲጓደል በማድረግ ሂደት ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያልተሳተፉ የትምህርት ባድርሻ በጣም ጥቂት ናቸው ያለው ሚኒስቴሩ፤ በመሆኑም ለመፍትሄው ከፖለቲካ አመራሩ እስከ ተማሪዎችና ወላጆች ድረስ ቁርጠኝነትና ሀቀኝነትን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ከስምምነት ላይ መደረሱን አስታውቋል።


ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ከብሄራዊ ፈተና አስተዳደር ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመቅረፍ ከፈተና ዝግጅት ጀምሮ እስከ ውጤት ማሳወቅ ድረስ ያሉት ተግባራት በከፍተኛ ጥንቃቄ እና በጋራ ኃላፊነት እንዲከናወኑ፡-

ፈተናዎች በዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደግፎ መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚል ነው። ይህም እውን እስከሚሆን ድረስ የሚሰጡ ፈተናዎች እንደ ቀድሞው በየክልል ትምህርት ቤቶች መሆን ቀርቶ የፈተና ጣቢያዎች በፌደራል ተቋማት ውስጥ ብቻ ሊሆኑ የሚችሉበት መንገድ ከአሁኑ እንዲዘጋጅ ማድረግ ተገቢ ነው።

ማህበረሰቡ ለረዥም ጊዜ ሲጠይቅ የነበረውንና መንግሥት ግልጽ አቋም የያዘበትን የትምህርት ሥርዓቱን የጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ማሳኪያ መሳሪያ አድርጎ መጠቀም ማንንም የማይጠቅም ሲሆን፣ በተለይ የልጆቻችን ትምህርት የሚጎዳ መሆኑ ታውቆ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ከእንዲህ አይነት ጎጂ አሉታዊ እንቅስቃሴ ራሱን ማቀብ ይኖርበታል።

በየደረጃው ያለው የፖለቲካና የመንግሥት አመራር የትምህርት ባለድርሻ አካላት መላው ህብረተሰቡን ጨምሮ በጉዳዩ ዙሪያ ማነጋገርና ለመፍትሄው በከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እንዲደረግ ለማስቻል ከፍተኛ ርብርብ እንደሚደረግ ከወዲሁ ስምምነት ላይ መደረሱን ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

# ስፖርት



## ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ በስቴድየሞች ዙሪያ ምን ታስቧል?

ቦጋለ አበበ

በቀጣይ የፈረንጆች አመት 2023 ምእራብ አፍሪካዊቷ አገር ኮትዲቯር በምታዘጋጀው 34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ለመሳተፍ የአገራቱ የምድብ ማጣሪያ ድልድል ባለፈው ሳምንት ይፋ መደረጉ ይታወቃል። ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋልያዎቹ) ጠንካራ በሆነው ምድብ አራት ከግብጽ፣ ጊኒ እና ማላዊ ጋር መደልደላቸው ይታወሳል።

የአፍሪካ ዋንጫው ማጣሪያ ጨዋታዎቹም ከመጪው ግንቦት መጨረሻ አንስቶ ይካሄዳሉ። ኢትዮጵያም በአህጉሪቱ ታላቅ የእግር ኳስ መድረክ ተሳታፊ ለመሆን በቅርቡ ዝግጅት እንደምትጀምር ይጠበቃል።

ይሁንና ባለፈው የካሜሩን የአፍሪካ ዋንጫ ከስምንት አመት በኋላ ተሳታፊ የነበሩት ዋልያዎቹ ዳግም በመድረኩ ለመታየት ከተጋጣሚዎቻቸው ጥንካሬ ባሻገር ሌላ ፈተና እንደተደቀነባቸው የስፖርት ቤተሰቡ ስጋት አድሮበታል። ይህም ስጋት የኢትዮጵያ ስቴድየሞች ካለፈው አመት ጀምሮ የካፍን መመዘኛ ባለማሟላታቸው ዋልያዎቹ በሜዳቸው አለም አቀፍ ውድድሮችን እንዳያከናውኑ ታግደው መቆየታቸው ሲሆን፣ ይህም የስቴድየሞች ጉዳይ መፍትሔ ሳይበጅለት የአፍሪካ ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታዎች መቅረባቸው ነው።

የአፍሪካን እግር ኳስ በበላይነት የሚያስተዳድረው ካፍ ከቀናት በፊት ለየአገራቱ አባል ፌዴሬሽኖች በአንድ ሳምንት ውስጥ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎችን የሚያስተናግዱ ስቴድየሞችን እንዲያሳውቁ ደብዳቤ መጻፉ መረጃዎች ወጥተዋል።

ካፍ እያንዳንዱ አገር የማጣሪያ ጨዋታዎችን የሚያስተናግዱ ስቴድየሞችን እንዲያሳውቅ የሚያስቀምጠው ቀነ ገደብ የቱንም ያህል ቢራዘም ከወር የዘለለ እድሜ እንደማይሰጥ የማጣሪያ ጨዋታዎቹ የወጣላቸው መርሃግብር አስረጂ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንም ይሁን የተለያዩ ስቴድየሞችን የሚያስተዳድረው የመንግስት አካል ባለፉት ጊዜያት ስቴድየሞች በካፍ ይሁንታ ማግኘት በሚችሉበት ደረጃ ስራዎችን ማከናወን እንዳልቻሉ ሚስጥር አይደለም።

ሁሉም የኢትዮጵያ ስቴድየሞች በካፍ ከመታገዳቸው በፊት በብቸኝነት አለም አቀፍ ጨዋታዎችን ሲያስተናግድ የቆየው የባህርዳር ስቴድየም በመጨረሻም በጥቃቅን ነገር ግን ትኩረት በሚፈልጉ ክፍተቶች ከእገዳ እንዳልዳነ ይታወቃል። አሁንም ይህ ስቴድየም ጥቃቅን ክፍተቶቹን በመሙላት ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች ይደርሳል የሚል ተስፋ በብዙዎች ዘንድ ቢኖርም፣ ስቴድየሙ አሁን ያለበት ሁኔታ ከካፍ እገዳ እንደማያድነው የብዙዎች ስጋት ነው። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የባህርዳር ስቴድየም እስካሁን የምሽት መብራት አልተገጠመለትም። ከዚህ በተጨማሪ ቀድሞም ሜዳውን የሚንከባከበው ቋሚ ድርጅት አለመኖሩ ለእገዳው ዋና መነሻ ቢሆንም ይህ ችግርም አሁንም ድረስ አልተቀረፈም።

አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ስታዲየሞችም ከመብራት ውጪ የመጫወቻ ሜዳቸው እና የመልበሻ ክፍሎቻቸው በጣም በአሳፋሪ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በቤትኪንግ ፕርሚየር ሊግ ጨዋታዎች እንዲሁም በሃምሳ አንደኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ወቅት ለመታዘብ ተችሏል። ትንሽ ተስፋ ሊጣልበት የሚችለው የባህርዳር ስቴድየም ቀጣዩን የቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ ጨዋታዎች የሚያስተናግድ ከመሆኑና ጨዋታዎቹንም ዲኤስ ቲቪ በቀጥታ የሚያስተላልፍ በመሆኑ የመብራት ጉዳይ ሊስተካከል ይችል ይሆናል። ነገር ግን ካፍ የግምገማ ቡድኑን ከመላኩ አስቀድሞ የሜዳውም ይሁን የመብራቱና ሌሎች መስተካከል ይገባቸዋል የተባሉ ክፍተቶች ባሉት ጥቂት ቀናት እስካልተስተካከሉ እገዳው የማይቀር ነው።



የባህርዳር ስቴድየም ዋልያዎቹ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎችን በሜዳቸው እንዲያከናውኑ ብቸኛ ተስፋ ነው፣

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ዋልያዎቹ በመጪው ሰኔ ያለፈው አፍሪካ ዋንጫ የፍጻሜ ተፋላሚና ጠንካራ የሆነችውን ግብጽን በሜዳቸው እንደሚገጥሙ ይጠበቃል። ዋልያዎቹ ወደ አፍሪካ ዋንጫው ለማቅናት በሜዳቸው የሚያከናውኗቸው ጨዋታዎች ወሳኝ ነጥቦችን ለማሳካት ትልቅ እድል እንዳላቸው ካለፉት ተሞክሮዎች መረዳት ይቻላል።

ይሁን እንጂ ዋልያዎቹ በሜዳቸው መጫወት የሚገባቸውን ወሳኝ ፍልሚያ በሌላ አገር ለማድረግ ከተገደዱ ትንሹን የማሸነፍ እድላቸውን ለተጋጣሚያቸው አሳልፈው እንደመስጠት እንደሚቆጠር ግልጽ ነው። በበርካታ አጋጣሚዎች ለመታዘብ እንደተቻለው የምእራብና ሰሜን አፍሪካ ቡድኖች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሲጫወቱ አየር ንብረቱ ይከብዳቸዋል። ባለፈው የአፍሪካ ዋንጫ ዋልያዎቹ ኮትዲቯርን የመሳሰሉ ትልልቅ ቡድኖች ጭምር አሸንፈው ወሳኝ ነጥቦችን በመሰብሰብ መሳተፍ የቻሉትም በእንዲህ አይነት ምክንያቶች ጭምር ነው።

አሁንም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ጋር በመሆን የስቴድየሞችን ችግር ካልቀረፉ የዋልያዎቹ የአፍሪካ ዋንጫ የማለፍ ጉዳይ እግር ኳሳዊ ባልሆኑ ችግሮች ጭምር ሊከሸፍ የሚችልበት እድል ሰፊ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።


## ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች የጨረታ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን ባሉበት ቦታና ሁኔታ በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል:: ስለሆነም ተጫራቾች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ነጥቦች በማሟላት ቀርበው መወዳደር ይችላሉ::

1. በጨረታው የሚወዳደሩት ተጫራቾች ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ሆኖ ሠነድ ለመግዛት ሲመጡ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ ወይም መታወቂያ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል::
2. በኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን ንፋስ ስልክ ቁጥር 3 ግቢ ከቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ቢሮ ቁጥር 27 በመምጣት የተሽከርካሪዎቹን ዝርዝር መረጃ የያዘ የተጫራቾች መመሪያ እና የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ ከፍለው መውሰድ ይችላሉ::
3. ተጫራቾች ሰነድ ገዝተው ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በሥራ ቀናት ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 10፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪዎቹን በሚገኙበት ዋናው መ/ቤትና የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን አዳማ ቅ/ጽ/ቤት መመልከት ይችላሉ፣
4. ተሽከርካሪው ቀደም ሲል ያልተከፈለ የቦሎ እና የጉምሩክ ቀረጥ ግብር ወጪ ካለው ባለንብረቱ መሥሪያ ቤት የሚሸፍን ሲሆን የስም ማዛወሪያ፣ የትራንዚት እና ሌሎች ወጪዎች ግን በገዥው ይሸፈናል፣
5. ተጫራቾች የሚገዙትን ተሽከርካሪ ለእያንዳንዱ የጨረታ መነሻ ዋጋ 20 በመቶ (20%) የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ከጨረታ ሰነዱ ጋር በማያያዝ ሣጥኑ ውስጥ ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ማስገባት ይኖርባቸዋል:: የጨረታ የመገምገሚያ መስፈርት ዋጋና የተሟላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ሲፒኦ) እንዲሁም በሰነዱ የተገለጹትን አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል:: የተሽከርካሪውን የመነሻ ዋጋ 20 በመቶ(20%) ያላስያዘ እና በሠነዱ የተቀመጡ ሌሎች ነጥቦችን ያላሟላ ተጫራች ከጨረታው ውድቅ ይደረጋል:: የሚዘጋጀው የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ከሆነ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ብቻ መሆን ይኖርበታል፣
6. የጨረታ ሳጥኑ ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ኛው ቀን ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚያኑ ቀን በ4፡15 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመንግሥት ግዥ አገልግሎት ይከፈታል:: ሆኖም የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓላት ቀን ከዋለ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ይሆናል:: እንዲሁም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ሳይገኝ ቢቀር የጨረታውን መከፈት አያስተጓጉልም፣
7. በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች አሸናፊነታቸው በተገለፀላቸው ከ 7 የስራ ቀናት በኋላ ባሉት 5 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ያሸነፉበትን ዋጋ በሙሉ መክፈል ይኖርባቸዋል::

ሆኖም ሙሉ ክፍያውን በተጠቀሰው ጊዜ ገደብ መክፈል ካልቻሉ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል::

8. በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን ተሽከርካሪዎች ሙሉ ክፍያ ከፍለው እስከሚወስዱ ድረስ ለውል አተገባበር ዋስትና የሚሆን የጠቅላላ ዋጋውን 10 በመቶ በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ አለባቸው::
9. ኮሚሽኑ ያወጣውን ጨረታ ሰነድ በስሙ ሳይገዛ የተወዳደረ ማንኛውም ተጫራች ከውድድር ውድቅ ይደረጋል::
10. አሸናፊ ተጫራች ያሸነፈበትን ገንዘብ አጠቃሎ በመክፈል ተሽከርካሪውን በ10 ቀናት ውስጥ የማንሳት ግዴታ አለበት፣
11. ለተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ በስልክ ቁጥር 011-4 42 34 72 መጠየቅ ይቻላል፣
12. ኮሚሽኑ ጨረታውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል የሚችል ሲሆን በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን ለመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፣

**የኢትዮጲያ አደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን**

**አዲስ አበባ**

## የንግድ ምልክት ዕድሳት ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የባለቤቱ ስምና አድራሻ | ኪምፕተን ሆቴል ኤንድ ሬስቶራንት ግሩፕ, ኤልኤልሲ (Kimpton Hotel & Restaurant Group, LLC) |
| | | 222 Kearny Street, California, Suite 200, United State of America |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር | FTM5938/2015 |
| 3 | የዕድሳት ጊዜ | ከ09/03/2022 እስከ 09/03/2029 |
| 4 | የንግድ ምልክቱ | **HOTEL MONACO** |
| 5 | ባለቤቱ ይህንን የንግድ ምልክት የሚጠቀመው በዓለም-አቀፍ ምድቦች 35, 36, 41 እና 43 በ19/08/2009 ዓ.ም. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ Vol. LXXVI No.229 በወጣው ማስታወቂያ ከተዘረዘሩት አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ነው:: | |
| 6 | ማንኛውም ግለሰብ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ከባለቤቱ ሳያስፈቅድ በዚህ የንግድ ምልክት በሚገለገል ወይም አስመስሎ በሚሠራ ላይ በሕግ ክስ ይመሠረትበታል:: የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን | |

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-227 -17/8/2014 (25/4/2022)